# ላንዳፍታ

በፍቅር፥በሰላም፥በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፥
መቻቻል

ግንቦት ፲፱፻፹፮
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩

$2.75

የአማርኛ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በየሁለት ወር የሚታተም




ውውቅ ፍቅር

ጋብቻ

## በዚህኛው እትም

❖ በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች
 የአጋዴን የመገንጠል አዝማሚያ
 የአየር መንገድ አዲሱ መዋቅር በተግባር ዋለ

❖ ኑሮ በአሜሪካ

❖ ልብ ወለድ
 ነዳማ
 የዴብራ ጦስ

❖ አዳምና ሔዋን
 አላለልኝ ይሆን
 ዕጣዬ

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Bi-monthly Amharic Magazine

(Amharic is the official language of Ethiopia)

May, 1994 Vol. 3. No. 1






# ETHIO VILLAGE

## CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ው ጫ

# CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

3 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት
ደብዳቤዎች

6 እንዲህ ሆነ
ዜናዎች ከኢትዮጵያ (ከኢትዮጵያ ወኪል)
የኦጋዴን መገንጠል ስጋት
ድርቅ በኢትዮጵያ
ታላቅ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ
ስለ አዲሱ የአየር መንገድ መዋቅር

15 ልብ ወለድ
"ነዳማ" (ግርማ ዘገየ)
"የዴብራ ጦስ" (ገረሱ)

26 ኑሮ በአሜሪካ
የሴንት ሉስ ኢትዮጵያውያን ተመክሮ
የአትላንታ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን

32 አዳምና ሔዋን
"ጓደኛ ለሚፈልጉ"
"አሳለልኝ ይሆን!" (ትዝታ አለብኝ)
"ዕጣዬ" (አብረኸት)
"ላንዳፍታን በሞቅታ" (ጣጤው)

41 የአበው ቅርስ
"ዋሽቶ የሚያስታርቅ ሽማግሌ" (አብዬ)
ታላላቅ ጥቅሶች

43 የግጥም ጉባኤ
"የጉላግ አርችፔላጐ" (መሪጌታ ልሳኑ)
"አዝናለሁ፣ እኔ ለእኔና ለአንቺ" (ጌታቸው አድማሱ)


45 ስፖርት
የአትላንታው የኢትዮጵያውያን እ.ኳ. ቡድን

46 ቢስቁም ባይስቁም

47 ጨዋታና ሰንጠረዥ




ድርቅ በኢትዮጵያ (10)




ኦጋዴንን ለመገንጠል (7)



የአትላንታ ቤ ክ መዘምራን (30)

---

የሽፋን ፎቶ - "በሞቴ ጉረሺልኝ" የመተሳሰብ አኩሪ ባህላችንን የሚያንጸባርቅ በመሆኑ አውጥተነዋል። በሴንት ሉስ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በዓል ላይ (ምስጋናችን ይድረሳችሁ)

---


"ላንዳፍታ" የግል መጽሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።
©COPYRIGHT LANDAFTA 1994

ላንዳፍታ
ግንቦት ፲፱፻፹፮
፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩
LANDAFTA
May, 1994 V. III - No. 1

*Publisher/Editor*
*Mekonnen Gessesse*
*Contributing Editors*
*Girma Zegeye*
*Abera Sisay*
*Editorial Advisors*
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
*Editorial Assistant*
Woinishet Bekele

**Distribution**

Atlanta, GA
- California Mart
- Sweet Auburn Grocery

Chicago, IL
- Ethio-Village Rest.
- Tesfaye B. (Hoddo)
- Yeshi Gessesse

Dayton, OH
- Rainbow Cafe

Denver, CO
- Tibeb Taye

Dallas, TX
- E.T. Beauty Supply

L.A., CA
- K RAH Market

Oak Land, CA
- Albo-African Shop

San Jose, CA
- St. Claire news Stand

Seatle, WA
- Addis Cafe

St. Louis, MO
- A & Z Liquor

St. Paul, MN
- Merkato

Tampa, FL
- Ibex Ethiopian restaurant

Washington D.C.
- Addisu Gebeya
- Family Food Market
- Merkato Market
- Nini Market
- Indian Super Market

Windsor, Ontario
- Tewodros Zewdu

*Landafta*
*P.O.Box 49301*
*Atlanta, GA 30359*
Phone/Fax *(404)728-9122*

# ከአዘጋጁ

እንደምን ከርማችኋል፤ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ። የላንዳፍታ መጽሔት ይኸው ሁለተኛ ዓመቷን አገባድዳ ሶስተኛውን መጀመሯ ነው። ጊዜው እንዴት ይሮጣል እባካችሁ። በዚህ የሁለት ዓመት ጥረቷ ብዙ መልዕክቶች ለማስተላለፍ፣ ብዙ ሰዎችን ለማስተዋወቅና ለማወያየት በቅታለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከማህበራዊ ጉዳይ ባሻገር አገር ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ማነሳሳት ጀምራለች። ዜናዎችን በቀጥታ አገር ቤት ባለ ወኪላችን አማካይነት በፎቶግራፍ አስደግፈን ማቀራረብ ጀምረናል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ከሁለት ወር ወደ አንድ ወር ለመምጣት እየተዘጋጀን ነው። ለዚህ ሁሉ ከጐናችን በመሰለፍ ላበረታቱን ውድ አንባብያንን፣ ለመጽሔቷ ድጋፍ በመሆን ማስታወቂያዎቻቸውን በማውጣት ለረዱን የንግድ ድርጅቶች ሁሉ ልባዊ ምስጋና እናቀርብላቸዋለን።

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበራት በየቦታው እንዲያድጉና የአህጉር አቀፍ የኢትዮጵያውያን ማህበር እንዲቋቋም "ላንዳፍታ" ሙሉ በሙሉ የምትደግፍ ሲሆን ይህንኑ በተግባር ለማዋል በቅስቀሳ በኩል የምታደርገውን ጥረት ትቀጥልበታለች። በመካከላችን ሊፈጠር ለሚችለው መግባባት፣ ፍቅርና ሰላም የዚህ ዓይነቶቹ ማህበራት ትልቅ አስዋጽዖ አላቸው። ሰብሰብ ስንል እንከበራለን፤ አድማጭም እናገኛለን።

የመጽሔታችንን ይዘት አድማሱን ሰፋ ከማድረግ በቀር ቀደም ሲል የነበሩ አምዶቻችን እንደተጠበቁ ናቸው።

"በፍቅር፣ በሰላም፤ በአንድነት ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥና መቻቻል!" የሚለው መርሆአችን ሁሌም እንደተጠበቀ ነው፤ የዕድገት መሠረቱ እሱ ነውና።





**እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!**

*We regret that we haven't included English pages in this issue.*

*Landafta is an independent magazine published in Amharic bi-monthly. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## እንደምን አላችሁ?

እንደምን ከርማችኋል? ይሄ በሰው አገር ኑሮ እንዴት ይዞአችኋል? ኑሮና ብልሃቱስ ተገጣጠመላችሁ ይሆን? እግዚአብሄር ይመስገን እኛ ደህና ነን። ደህና ነን እንላለን። ሠሞኑን አዲስ አበባ ዝናብ እየጣለ ስለሆነ እናት የሚበሳው የአዲስ አበባ ፀሐይ በረድ ብሎአል። ተጋግለው ሲያጋግሉን የሠነበቱት የሕገ-መንግስት ሹሞቻችን ናቸው። ስለአዲሱ ሕገ-መንግስት ብዙ ብዙ ነገሩን፤ ስለሚሰጠን ዲሞክራሲ፣ ምልቶ ስለሚተርፈን መብት ሰበኩን። ከፈረንጅ አገር የመጡ እንቱ የተባሉ አዋቂዎች አስነገሩን። አስመከሩን። እኛ ደግሞ እባብ ያየ በልጥ ይደነግጣል ሆነና ነገሩ ሁሉ ቅም አልል ብሎን በጥርጣሬ ተሞልተን ተቸግረን ስናስቸግራቸው ሰነበትን። ቀንቶት ቤተመንግስት የገባ ፖለቲከኛ ከሕዝቡ ጋር ያለውን ዝምድና ልቡ እያወቀው ሕገ-መንግስት እያለ ሲደክምና ሲያደክመን በመካከሉ የድሃ ጎጆ ተዘንግታ ተዛዝበናል።

ቀን የሰጠው ባለጊዜ የሆነለት ሲመስለው በአንደበተ ትንታግ ካድሬዎቹ ሲያነቃን፣ ሳይሆንለት ደግሞ በባለ ነፍጥ ወታደሩ ሲያንቀን በዚህ ትንቅንቅ መሃል የተናቀች ድሃ ሀገር፣ ልጅ የማያድግበት፣ ዘር የማይበቅልበት የእርግማን ምድር ሆነን መቅረታችን አይተነዋል። ሲሆን ሲሆን ይህን ሕገ-መንግስት የሚሉትን ለትውልድ የሚተርፍን ረጅም መንገድ ጉዞ ከመጀመራችን በፊት የየልባችንን ቁስል ተገላልጠን የሌላውን ሳይሆን የየራሳችንን ዓይኖች ጉድፍ ጠርገን፣ ጊዜ ቆጥሮ እያመረቀዘ የሚያመንን የቂምና ቁርሾ ሕመማችንን በይቅርታና በፍቅር ፍቀን ከሁሉ በፊት ተደጋግፈን መቆም ብንችል ደግ ነበር። ሳያሽ የበላ ጅንጀሮ ሲያስለው ያድራል ነውና!

ልብ ሳንለው ቀርተን ይሁን ወይ ሳናውቀው ትውልድ እየቀረጠፈ የሚበላ አዙሪት ውስጥ የገባን ይመስለኛል። ... ድርቅ ረሃብ ዕልቂትና ፍጅት፤ የተበደለ የተገፋ ህዝብ ብሶት፣ አመጽና ቱማታ ...አዲስ መንግስት (ምናልባትም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ) ጊዜያዊ ነኝ የሚል... ዲሞክራሲ፣ መብት፣ ግዴታ ምንትስ... የፖለቲካ ሆያሆዬ ፈንጠዚያ ድስኩር፣ ለቅሶና ጩኸት ...ሕገ መንግስት፣ ብዙ ብዙ መግለጫ፣ ውይይት፣ ምርጫ መሰል ነገር፣ እንደራሴነት፣ የሹመት ጋጋታ... ድርቅ ረሃብ ዕልቂት ጦርነትና ፍጅት ደግሞ የተበደለ የተገፋ ሕዝብ ቁጣ ...ደግሞ አዲስ መንግስት ጊዜያዊ ቢጤ... እንዲህ እንዲህ እያለ በዚህ አዙሪት ስንት ትውልድ በገዛ ወገኑ እጅ በግፍ እያለቀ፤ ሀገር ከድህነት ወለል በታች የድሆች ድሃ ሁና መቀመቅ ወረደች። በዘንድሮው የዘር ፖለቲካ አበሳውን ሲቆጥር የሰነበተ ድሃ ኢትዮጵያዊ እነሆ ደግሞ ረሃብ የሞት አፎቹን ከፍቶበታል። ረሃብ ሲባል እዚህ እኛ ዘንድ ትርጉሙ ለየት ይላል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ካልተራቡና በሺዎች የሚቆጠሩ መሞት ካልጀመሩ ብዙም ቁምነገር የሚለው የለም።

ስንት ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከውሻ እንኳ ለአፍንጫ በሚሰነፍጥ ግማት መሀል ከየሰፈሩ ቆሻሻ መድፊያ ኮሲ ላይ ለወስፋት ማስታገሻ ፍለጋ ሲጭር ረሃብ ነው የሚለው የለም። በቁሙ እየሞተ ያለን ተፈናቃይ ተራብ ያለው አልነበረም።

የዘንዶሮው ረሃብና ድርቅ ካለፉት ሁሉ የከፋ ነው ይባላል። በእርግጥም ብዙ ምክንያቶች አሉ ይህን ለማለት! ....ባለፉት ጥቂት ወራት በመንግስት ሹሞች 4 ሚሊዮን ነው የተባለው ረሃብተኛ ብዙም ሳይቆይ 7 ሚሊዮን ደርሷል። ድርቅና ረሃብ መሸፋፈን የሚወዱት ፖለቲከኞቻችን ይህን ያህል ካሙኑ ያለአንዳች ጥርጥር የረሃብተኛው ቁጥር ከተነገረን ብዙ ብዙ እንደሚበልጥ ልቦናችን ያውቀዋል። ለወገን ደራሽ ወገን ነውና እጃችሁን ዘርጉ ተብለናል። በእጅ የያዙትን ቀርቶ የጎረሱትን እንኳ በጉጠት (በፒንሳ) ፈልቅቆ የመንጠቅ ያህል በጨከነው የኑሮ ውድነት የስንቶቻችን እጅ ሊዘረጋ መቻሉ ያጠያይቃል። ደግሞስ የወገን ትርጉም ተጣሞና ተዛብቶ "ወገኔ" ለማለት የዘር፣ የጎሳ፣ የቋንቋ ቁርኝት በሚቆጠርበት በአሁኑ ወቅት በእርግጥም ለተራበው ሕዝብ ያለአድልዎ ግድ የሚለን ስንቶች ነን? ጥላሁን ገሠሠ "ዋይ ዋይ ሲሉ የረሃብን ጉንፋን ሲስሉ" እያለ እያነባ የሚዘፍነው ዘፈኑ ዛሬም እንደያኔው ብዙዎቻችንን በጅምላ የሚያስለቅሰን መሆኑ በእጅጉ ያጠራጥራል።

ድፍን ምስራቅ አፍሪካ በተጎዳበት በአሁኑ ድርቅና ረሃብ እንዳለፉት የረሃብ ዓመታት ኢትዮጵያ ብቸኛዋ የዓለም ረሃብተኛ የመሆን "ዕድሉ" privilege የላትም። በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ እንደያኔው ትኩረትና ሀዘኔታ ማግኘቷም ቢሆን ያጠራጥራል። ....በዘንድሮው የዘር ፖለቲካ ወዲህ ዘር እንደአውሬ ሲያሳድን፣ ለዕልቂት ለስደት ሲዳርግ፤ ወዲህ ደግሞ ያለችሎታ ሲያሾም ሲያሸልም በሚገኘውም ዕርዳታ ላይ ቢሆን ዘርና ጎሳ የማይቆጠርበት፣ አድልዎና ተንኮል የማይፈፀምበት ስለመሆኑ በእጅጉ ያጠያይቃል።.....

እንግዲህ ይህ አዙሪት ዳግመኛ የሚሊዮን ዜጎች ሕይወት ሊቀጥፍ ነው። ብቻ! ሁሉ የሚቻለው የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ይሁነን። እናንተስ ይህ አዙሪት እንዴት ይሆን የሚያደርጋችሁ? ....አበሻ ሬስቶራንት ስትገናኙ የምታወሩት ጨዋታ ነው የሚሆናችሁ? ወይስ ሀሊናን የሚያቆስል አንገት የሚያስደፋ?


....እኛ እንግዲህ ሰሞኑን ገሚሶቻችን ስጋ ለመብላት ተዘጋጅተናል። ሙክቱን ዶሮውን ቅቤውን ልንሞክረው ተሰናድተናል። ሕይወት እንዲህ ናት! .... "አንዱ ስጋ አጥቶ ይሞታል ሌላው ስጋ አንቆት ይሞታል" ይባላል።

በሉ ደህና ክረሙልኝ! መልካም ፋሲካ!

የእናንተው ወርቃየሁ ከአዲሳባ



# የአንባብያን ደብዳቤዎች



ይድረስ ላንዳፍታ አዘጋጅና አቅራቢዎች በሙሉ በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬን አቀርብላችዋለሁ። ከዚቹ መጽሔት ከምትታተምበት ከተማ። በእውነቱ መጽሔቷ ምንም እንከን የማይወጣለት መጽሔት ናት። መጽሔቷ መታተም ከጀመረችበት ጀምሮ አንድ እትም ሲያመልጠኝ ሌላውን እየገዛሁ እያነበብኩ ይህው ሁለተኛ እትም ላይ ደርሻለሁ። ታድያ የመጽሔቷን አምድ ማለትም ገፁን በዛ ብታደርጉትና በአለማችን ላይ ከሚፃፉት ሳይንስ ነክ አዳዲስ የሳይንስ ውጤቶችን ከተለያዩ መጽሔቶችና ጋዜጦች በዚቹ በላንዳፍታ መጽሔት ብታቀርቡ የበለጠ ተወዳጅነትን ታተርፋለች ብዬ አምናለሁ። ይህ እንግዲህ ስለመጽሔቷ ያለኝ አስተያየትና ጥቆማ ሲሆን ወደ መጣሁበት አላማ ደግሞ ስመለስ የሀገር ጉዳይ ነው። የሀገር ጉዳይ ከተነሳ የሀገራችን የኑሮ ሁኔታና የፖለቲካ ችግሮች ሀገራችን ከፍተኛ ችግር ገብታለች። ይህ እያንዳንዱ ቁርጠኛ ዜጋ የሚያውቀው ነውና ከዚሁ ውስጥም አንዱ እራሴ ነኝ። ሀገሬን እወዳለሁ፣ አፈቅራታለሁ። በእውነቱ ከሆነ ከብዙ የሀገሬ ሰዎች ጋር ባልገናኝም ከማነባቸው መጽሔቶችና ጋዜጦች የሀገራችን ሁኔታ በጣም የሚያሳስብ ነው። የሕዝባችን የኑሮ ውድነት፣ የፖለቲካ አለመጣጣም፣ ተራውን ንፁውን ወገናችንን ችግር ውስጥ አስገብቶታል። ታድያ ወሬ አበዛህ አትበሉኝና አሁን በቅርቡ ኢትዮጲያ ሪቪው መጽሔት ላይ ያነበብኩት አንድ ወገኔ የጻፈውን አስተያየት አንብቤ በጣም ደገፍኩት። ወገናችንን የምንረዳበት መንገድ ነው እሱ የጻፍው። በጣም ጥሩ ሀሳብ ነበር። ታድያ ተግባር ላይ የመዋሉ ጉዳይ የኛ የራሳችን ነው። ታድያ እሱ የጻፈው በሀገራችን ያሙን የሚውለውና ቤት የለሹ ወገናችን በቀላሉ የሚገመት ቁጥር አይደለም። በአንፃርም ደግሞ በውጭ አገር የሚኖረው የሕዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም። ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ይኖራል ይባላል። ኢትዮጲያ ሪቪው መጽሔት ላይ የጻፈው ወገኔ ሁሉም ይተባበራል ማለት በጣም ያስቸግራል። ግን 50% ቢተባበር ቀላል አይደለም አሁን በኮሚኒቲ መሰብሰብ እየመጣ ነው በጣም ቆንጆ ሀሳብ ነው። እኔ እንኳ የዚህ አባል ባልሆንም ወደፊት አባል እሆናለሁ ብዬ አምናለሁ። ታድያ ሁላችንም ባለንበት አካባቢ ተሰብስበን ከተቻለ በ3ወር አንድ ግዜ የገንዘብ መዋጮ አድርገን አቅማችን የሚፈቅደውን ያህል ብንረዳ ቀላል አይደለም አሜሪካንና ሌላም አገር የውጭ እርዳታ ሰጪዎች ስላሉ በኮሚኒቲ የማህበር መሪዎች አማካኝነት ጠይቀን ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ ችግራችን እናቃልላለን ብለን ባናምንም በመጠኑም ቢሆን ሕዝባችንን፣ ወገናችንን መርዳቱ ቀላል አይደለም። ታድያ ላንዳፍታ መጽሔት ከፍተኛ ሚና ስለምትጫወት ይህንን ያለኝን አስተያየት በጉ አላማ ልኬሃለሁ አመሰግናለሁ።

የናንተው በለጠ ካሣዬ (ከአትላንታ

---

ይድረስ ላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጆች፤

በቅድሚያ ወገናዊ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ። ላንዳፍታን ለመጀመሪያ ጊዜ ማንበቤ ነው። መልካም ጅምር ነው። በርቱ እላለሁ። በተለይ በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥ መቻል" የመለው አባባላችሁ ወሽኒና ቅንነት የተሞላበት ነው። በእኩልነትና በዲሞክራሲ የሚያምኑ ሰዎች አባባል ብቻ ሳይሆን የጤነኛ አዕምሮ አመለካከትና በራስ የመተማመን ሥነ ልቦና ያላቸው ግለሰቦች ዕምነት ጭምር ነው።

ችግሩ ግን እንደነኢሳያስና መለስ ያሉት በአፋቸው (የዓለምን ኅብርተሰብ ለማወናበድ) ሰላም እያወሩ የዕለት ዕለት ተግባራቸው ግን አገርን በጦርነት (በጉልበት) ማፍረስ መሆኑ እየታወቀ፤ የሚተማመኑት በአዕምሮአቸውና በሕዝባዊ ድጋፋቸው ሳይሆን በካላሽናቸው (በጦራቸው) ብቻ መሆኑ ዕለት በዕለት በማያደርጉት የዕብሪት ጦር እያየነው "ሰላም" እያሉ ማላዘኑ "ላም በሌለበት ኩበት ለቀማ" አይሆንም ይሆን? አንዳንዴም እኮ ጦረኞችን በራሳቸው ቋንቋ ብቻ በማናገር እንዲገባቸው ማድረግና አልፎም ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ማግኘት እንደሚቻል ማወቁ ብልህነት ነው እላለሁ። ማለትም ትክክለኛና ለነፃነት የሚያበቃ ጦርነት በማድረግ አምባገነንችን ለአንዴም ለሁሌም በመጣል በእነሱ መቃብር ላይ እውነተኛ ሰላም ማግኘቱ የተሻለ ነው ባይ ነኝ።ስለሆነም ሕዝቡ ተደራጅቶ እነዚህን በትዕቢት የተወጠሩ ጠላቶቻችንን ታግለው እንዲያሸንፉ መቀስቀሱ አማራጭ የሌለው የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነውና እናንተም ከነባራዊው ሁኔታ በመነሳት ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚገባው ማስተማሩ ለነገ የማይባል የዛሬው ታሪካዊ ግዴታችሁ ነው።

በመጨረሻም እባካችሁ እነዚህ የEPDRF/EPLF ትቃዋሚ ነን የሚሉትን ግለሰቦችና ድርጅቶች ኢትዮጵያን ካፈራረሱት ጠላቶች ጋርና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የነኢሳያስና መለስ ደጋፊዎች ከሆኑት ድርጅቶችና አገሮች እንደገና ተበደልን፣ አገር ጠፋ፣ እርዱን እባካችሁ እያሉ ኢትዮጵያዊነት በጐደለው ወኔ ከባዕዳን ጋር ደግመው እንዳይቆሙ ምክር ስጡልን። ከእንግዲህ ወዲያ ችግራችንን እኛው ተባብረን እንወጣዋለን እንጂ ከጠላት ደጅ እየጠናን መሳለቂያና መሳቂያ አንሁን።

ምነው ጃል!ቀደ ም ብሎ አሜሪካ በካርተር ገላጋይነት አይሁዶች (የU.S. State Departmentን ተጠቅመው) በሄርማን ኮሄን ጣልቃ ገብነት እንደገና አይሁዶችና ግብጾች (United Nations በመጠቀም) ግማሽ የአይሁድ ዘር፣ ግማሽ ግብጽ የሆነውን ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊን በመጠቀም (የአባይን ወንዝ ለመውሰድ ሲሉ) በ UN አማካይነት ተረባርበው ኤርትራን ማስገንጠላቸው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በነሱ መዳፍ እንድትገባ ማድረጋቸው ከመቼው ተረሳና ነው እንደገና " የአትላንታ እርቅ ጉባኤ" ቅብጥርጥር የሚሉት። ድንቄም እርቅ ይሁን! "ሞኝን እባብ ሁለት ጊዜ ይነድፈዋል" ዓይነት ነው። አሁን ደግሞ ኦጋዴንንና ኦሮሞውን ለማስገንጠል ነው እርቅ እያሉ የአዞ እንባ የሚያነቡልን። ምነው አቦ ቢተውን፤ ቀን የጣለው ጊዜ የወደቀበት ጊዜአዊ ሽንፈት የደረሰበት ሕዝብ አያውቁም። "የወደቀን ግንድ ምሳር ይበዛበታል፤" እንዲሉ ምነው ደግመው ደጋግመው ባያሞኙንና ባያጠቁን!!

ኧረ ባካችሁ አንድ በሉን እነዚህን ሰዎች! ሰላም በሌለበት ሰላም እያሉ አያላዝኑ! መፈክራቸው አደገኛና ትጥቅ አስፈች ነው። አልፎም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘላለም ባርነት የሚዳርግ ነው። ስለሆነም ሕዝቡ ተደራጅቶ እንዲታገል ማስተማርና መቀስቀስ እንጂ ያለ ጦርነት ብቻ ምንም ለማይገባቸው እምባገነኖች "ሰላም" እያሉ መጮሁ የማይቀረውን የትግል ውጣ ውረድ (መራራነት) አስቀድሞ ከመፍራት መለማመጥ ማብዛት ይመስላል።

ወንድማችሁ ዋለልኝ አዲስ (ከአትላንታ)

---

## ለአንባብያን

በደብዳቤም መልክ ሆነ ረዘም ያለ ጽሑፍ የምትልኩ ውድ አንባብያን እባካችሁ ስማችሁ፤ አድራሻችሁንና የስልክ ቁጥራችሁን ከምትልኩልን ጽሑፍ ግርጌ ወይም ራስጌ አድርጉልን። ጽሑፉ በብዕር ስም እንዲወጣላችሁ ከፈለጋችሁ "ስሜ አይጠቀስ" በማለት የብዕር ስማችሁን ላኩልን። እኛም ትክክለኛ ስምና አድራሻ በጥያቄያችሁ መሠረት አናወጣውም። አንባብያንን ይቅርታ እየጠየቅን ስምና አድራሻ እንዲሁም የስልክ ቁጥር አብረው ያልደረሱንን ደብዳቤዎች ሆነ ጽሑፎች የማናወጣ መሆኑን በትህትና እንገልጻለን። ስለ ጽሑፋቸው አንዳንድ ጥያቄ ቢኖረን ለማነጋገር ይመቸናል።

---

## ማሳሰቢያ

በላንዳፍታ መጽሔት ላይ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉት መጣጥፍ፤ ደብዳቤ፣ ማስታወቂያና የመሳሰሉት ሁሉ ለዝግጅታችን ክፍል የሚደርሱበትንና መታተም የሚችሉበትን ጊዜ በማስመልከት ይህን እናሳስባለን።

ለSept እትም በ August መጀመሪያ ሳምንት
ለNov እትም በ Oct መጀመሪያ ሳምንት
ለJan እትም በ Dec መጀመሪያ ሳምንት
ለMarch እትም በ Feb መጀመሪያ ሳምንት
ለMay እትም በApril መጀመሪያ ሳምንት
ለJuly እትም በ June መጀመሪያ ሳምንት

---

በመጽሔቱ ላይ እንዲወጣ ለምትፈልጉት የግል ዜናዎች የሚቀጥሉትን ይመልከቱ።

**ዜና ዕረፍት -**
የሟቹን ጉርድ ፎቶ ከአራት መስመር ባለበለጠ አጭር የሕይወትረ ታሪክ ጋር
የአገልግሎት ዋጋ - $30.00 ብቻ

**ዜና ሠርግ -**
የተጋቡትን ሰዎች ፎቶ (አንድ ላይ) ከሶስት መስመር ካለበለጠ ዜና ጋር
የአገልግሎት ዋጋ - $30.00 ብቻ

**ዜና ልደት -**
የተወለደውን ሕፃን ፎቶ ከሁለት መስመር ካልበለጠ ዜና ጋር (የአባትና የእናት ስም ተጨምሮ)
የአገልግሎት ዋጋ - $25.00

**ዜና ምረቃ -**
ትምህርቱን የጨረሰው/ችው ግለሰብ ፎቶ ከመመረቂያ ልብስ ጋር፣ የተመረቀበትን ትምህርትና ት. ቤት ከሚገልጽ 2 መስመር አጭር ዜና ጋር
የአገልግሎት ዋጋ - $25.00

---

ደብዳቤ አስተያየትም ሆነ ጽሑፎች የምትልኩልን ትክክለኛ ስማችሁንና አድራሻችሁን እንዲሁም የስልክ ቁጥራችሁን እንድትልኩልን በትህትና እንጠይቃለን። በጽሑፉም ሆነ በደብዳቤው ስማችሁ እንዳይጠቀስ ከፈለጋችሁ ይህንኑ ከጽሑፉ ግርጌ ጥቀሱና የብዕር ስማችሁን ላኩልን። ትክክለኛ ስምና አድራሻችሁ ግን እኛ ጋ መኖር ስላለበት አደራ እንላለን።

አድራሻችን ፤- Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
ስልክ/ፋክስ፤ (404)728-9122

### እንዲህ ሆነ

## አየር መንገድ ለየለት፤ የመዋቅር ለውጡ በአዲስ ማኔጅሜንት እየተሞከረ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
ETHIOPIAN AIRLINES

በአፍሪካ የአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ የተሳካለት የሚባለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ እስካሁን ባለው ክንዋኔው ተተችቶና ተነቅፎ ሽግግር መንግስቱ አዲስ መዋቅር ተዘርግቶለት አዲስ ማኔጅመንትም ተመድቦለታል። የሽግግር መንግስቱ የመከላከያ ሚኒስትር፣ የሕወኃት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የማኔጅመንት ቦርድ ሊቀመንበር ለአየር መንገዱ ሠራተኞች ባደረጉት ንግግር "300 ሚሊዮን ዶላር ዕዳ ያለበት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተወዳድሮ የሚሠራው በአለም አቀፍ ገበያ በመሆኑ አዲስ መዋቅርና ማኔጅመንት ያስፈልገዋል ካሉ በኋላ የገቢና የወጪ ሚዛኑ የተዛባ፣ መዋቅሩም የተንዛዛ ብቁ የሆኑ መሪዎች የለሉት ድርጅት" ሲሉ አየር መንገዱን ነቅፈውታል። ሚኒስትሩ በዚህ ንግግራቸው አየር መንገዱን "ጄነራልና ኮሌኔል የበዛበት እግረኛ የሌለው ሠራዊት ይመስላል" ብለውታል። እንደማኔጅመንት ቦርዱ መግለጫ የአዲሱ መዋቅር አስፈላጊነት የአየር መንገዱን ሕልውና ለመጠበቅ ነው ቢባልም በአየር መንገዱ ላይ የተወሰደው የመዋቅር ለውጥና ሹም ሽር ኢትዮጵያን የማፍረሱ ዘመቻ አካል ነው ሲሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሥልጣን ላይ ያለውን የሽግግር መንግስት ይኮንናሉ። በተለይም ከኤርትራና ከጂቡቲ ጋር የታቀደው ጆይንት ቬንቸር የማንን ጥቅም ያስከብራል? ለማንስ ይበጃል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት የመዋቅር ለውጡን በምሬት ይነቅፉታል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሠራተኛ ማህበር፣ የአብራሪዎች ማህበር እና ማኔጅመንቱ በህብረት በመቆም አየር መንገዱ አክሳሪ አለመሆኑና በመንግስት በኩል የቀረበው የመዋቅር ለውጥ ለአየር መንገዱ ዕድገት እንደማይበጅ ለማሳመን በአቶ ስዩ አብርሃ ከሚመራው ማኔጅመንት ቦርድ ጋር ተነታርከውበታል። የመዋቅር ለውጡ ቢደረግ ሊከተል የሚችለውን ችግር በመዘርዝር ለቦርዱ ሊቀመንበር የአቤቱታ ደበዳቤ አቀርበዋል። (የደብዳቤው ሙሉ ቃል በገጽ ላይ ይመልከቱ።) ይህ በእንዲህ እንዳለ የማኔጅመንት ቦርዱ ከዋና ሥራአስኪያጁ ጀምሮ 6 ም/ሥራአስኪያጆችንና ከ30 በላይ ባለስልጣኖችን አግዷል። የረጅም ጊዜ የአቪዬሽን ልምድ ያላቸው ካፕቴን ዘለቀ ደምሴ በዶ/ር አህመድ ኬሎ ተተክተዋል። አዲሱ ተሿሚ ዶ/ር አህመድ ኬሎ በአንድ ወቅት በብርጭቆ ፋብሪካ ፕሮጀክት ውስጥ ከመስራታቸውና በውጭ አገር በማስተማር ሙያ ከመስራታቸው በቀር የአቪዬሽን ዕውቅትና ልምድ እንደሌላቸው ይነገራል። በታገዱትና በተሻሩት የአየር መንገድ ኃላፊዎች ምትክ በአብዛኛው የተሾሙት አዲሱን መዋቅር አጥንተው ያቀረቡት ለአየር መንገዱ እንግዳ የሆኑ ግለሰቦች ሲሆኑ ከ14 ዓመታት በፊት በቅንሳ ወጥተው የነበሩ አንድ የኤርትራ ተወላጅ የአየር መንገዱ የፕላኒግ ዲቪዥን ም/ዋና ሥራአስኪያጅ ሆነው ተሹመዋል። የአዲሶቹ ተሿሚዎች ስለአቪዬሽን ያላቸው ሙያና ልምድ ከቀድሞዎቹ ኃላፊዎች ያነሰ ሆኖ መገኘት በአየር መንገዱ ላይ የተጀመረ ሳይሆን ብቃት የሌላቸውን ግለሰቦች በማይመጥኑት ኃላፊነትና ሥልጣን ላይ በማስቀመጥ ሁኔታዎችን ከጀርባ ሆኖ በራሱ መንገድ ለመምራት ኢህአዴግ ከመነሻውም ሲጠቀምበት የቆየ ዘዴ ነው ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ለአየር መንገዱ ይበጃል የተባለውን ጥናት እንዲያካሂድ በመንግስት የተሠየመው አጥኚ ቡድን ራሱ ስለ አቪዬሽኑ ጥበብም ሆነ የንግድ ሁኔታ እንዳችም ዕውቀት የሌለው ሲሆን ይህን ለአቪዬሽን መሃይም የሆነ ቡድን በማሠማራት ብሄራዊ ጥቅምን በሚያሳጣ መልኩ በአየር መንገዱና በሀገሪቱ ላይ ደባ ተፈጽሞአል የሚሉ ወገኖችም አልጠፉም።

በተያያዘ ዜና በአየር መንገዱ የማሠልጠኛ ክፍል ውስጥ ይሠሩ የነበሩ 13 መምህራኖችና ቴክኒሺያኖች ቦርዱ በወሰደው ሁለተኛ ዙር ዘመቻ ከስራ ተወግደው በቁጥጥር ሥር ውለዋል። እነዚህ መምህራኖችና ቴክኒሽያኖች አብዛኞቹ በአየር ኃይል የብዙ ዓመት የበረራና የሥልጠና ዕውቀት ያላቸው መኮንኖች ሲሆኑ የመታሠራቸውም ምክንያት በኮ/ል መንግስቱ የስልጣን ዘመን የአየር ድብደባ ፈጽመዋል በሚል ውንጀላ እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይጠቁማሉ። ከመንግስት የተሰጠ መግለጫ ግን የለም።

በርካታ ኤርትራውያን በሚገኙበት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ በመዋቅራዊ ለውጡ ምክንያት የሚደረገው የሠራተኛ ቅነሳ በቅድሚያ የሚመለከተው እነዚህን የውጭ አገር ዜጎች ወይስ ኢትዮጵያውያኖችን የሚለው ጥያቄ መልስ በብዙ ወገኖች ዘንድ በጉጉት እየተጠበቀ ነው። የአየር መንገዱ ሠራተኛ ማህበር የመዋቅር ለውጡ ተግባራዊነት እንዲታገድ አሁንም ጥረት እያደረገ መሆኑን ከአንዳንድ የዜና ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአየር መንገዱ አበዳሪ ባንኮች ማናቸውም የመዋቅር ለውጥ ሲደረግ የማወቅና የመስማማት መብት ያላቸው በመሆኑ ለውጡ እጅግ አሳስቦአቸዋል ተብሏል። በዚህም ምክንያት የአበዳሪዎቹ የልዑካን ቡድኖች ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ለመነጋገር ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል።


እ ን ዴ ህ ሆ ነ

## የኦጋዴን የመገንጠል ስጋት እያየለ መጥቷል።

የዜና ወኪል

የምስራቅ ኢትዮጵያ የሀገራችን አካል የሆነውን የኦጋዴንን አካባቢ ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የኦጋዴን ነጻ መንግስት ለመመስረት የሚደረገው እንቅስቃሴ እያየለና እየተጋጋለ መምጣቱን ከአካባቢው የሚደርሱ ዜናዎች ይጠቁማሉ። ይህን የመገንጠል ጥያቄ በተጠናከረ ሁኔታ በማራመድ (በመግፋት) ላይ ያለው የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ኦጋዴን በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት የተያዘች ናት በሚል አቋም ክልሉን ከኢትዮጵያ በመገንጠል "የኦጋዴን ነፃ መንግሥት" ለማቋቋም ትግሉን በማጧጧፍ ላይ ነው። ኦጋዴን ቀድሞም ከኢትዮጵያ ጋር አንድ አልነበረችም በማለት የኢትዮጵያ አካልነታቸውን እርሰው እንደማይቀበሉ ያስታወቀው የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦ. ብ. ነግ/ONLF) ነፃ የኦጋዴንን ሪፑብሊክ ለመመስረት ያለውን አቋሙን በግልጽ አስቀምጧል። በዚህም መሠረት የምትመሠርተውን የአዲስቷን ኦጋዴን ካርታ ነድፏል። በካርታው ላይ የተመለከተው የኦጋዴን ክልል ከኢትዮጵያ ከሶማሊያና ከጂቡቲ የሚዋሰን ሲሆን ሐረርና ጅጅጋን ጨምሮ ብዙውን የኢትዮጵያ ምስራቃዊ ክፍል የሚያጠቃልል ነው። የኦጋዴንን መገንጠል ግንባር ቀደም ዓላማው አድርጎ የተነሳው ይህ ግንባር የራሱን መንግስት ለመመስረት የሚያደርገውን ትግል ማንም ሊገድበው እንደማይችል አቋሙን ለሽግግር መንግስቱና በአ. አ ለሚገኙ የውጭሀገር አምባሳደሮች፣ ለተባበሩት መንግስታትና ለተለያዩ ድርጅቶች ማሳወቁን ገልጾ ይህን ዓላማውንም የሚያራምደው ቻርተሩ ባስቀመጠው "የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል" በሚፈቅደው መርሆ መሠረት መሆኑን አስታውቋል።

በአዲስ አበባ የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር ከአንድ የግል ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ በአካባቢው ወታደራዊ ግጭቶች መኖራቸውን ተጠይቀው ሲመልሱ በጎዴ፣ በቀብርድሀርና በዋርዴር ብዙ ሰዎች የሞቱበት ግጭቶች እንደነበሩ ጠቅሰው ግጭቱ የተካሄደው በኢሕአዴግና በኦጋዴን ሰላማዊ ሕዝብ መካከል ነው ብለዋል። ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ነፃ አድርጎ ከሶማሊያ ጋር የመቀላቀል ዓላማ እንዳለላቸው የገለጹት እኚህ የግንባሩ ባለሥልጣን የኦጋዴን ነፃ ሪፐብሊክ መመስረት ለድርድር እንደማይቀርብና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በአንድነት መኖርን እንደ አማራጭ እንደማይቀበሉት ፍርጥ አድርገው ተናግረዋል። በተያያዘ ዜና የግንባሩ ሰራዊት ጥቃት ሰንዝሮ ከ106 በላይ መግደሉን፣ በርካታ የጦር መሣሪያና ምርኮዎችን መያዙን አስታውቋል። በሌላ በኩል የኦጋዴንን ሕዝብ የመገንጠል ጥያቄ በመጎትጎት ላይ ያለው የኦጋዴን ነፃነት ግንባር እንቅስቃሴ የእስልምና አራማጅ የሆነ ኢስላምክ ዩኒቲ ፓርቲ (Islamic



OGADEN NATIONAL LIBERATION FRONT

unity party) በሚባል ድርጅት ግፊት የሚመራ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ሶማሌዎች ዲሞክራቲክ ሊግ ሊቀመንበርና የውጭ ኢኮኖሚ ሚኒስትር ዶ/ር አብዱል መጅድ ሁሴን አስታውቀዋል።እያይዘውም በኦጋዴን ሴራ የገቡት ግብጾች በግጭቱ ወይ ተማርከው ወይም ተገድለው መገኘታቸው ወደፊት ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን ጠቅሰው ግንባሩ ኦጋዴንን ለመገንጠል በኢስላሚክ ዩኒቲ ፓርቲና፣ በኢራቅ በሶሪያ፣ በሊቢያና በግብጽ አዝማችነት የሚንቀሳቀስ ነው ብለዋል።

በሌላ ዜና ደግሞ በስዊድን የሚገኙ የኦጋዴን ኮሚኒቲ አባላት ኢትዮጵያ ለኦጋዴን ሠላማዊ መፍትሄ እንድትሰጥ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሀገሮችና የአረብ ሀገሮችን ማህበራት ድጋፍ ጠይቀዋል። የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባርን ብቸኛ የኦጋዴን ሕዝብ ተጠሪም ሲሉ ድጋፋቸውን ገልፀዋል።ፕሬዝዳንት መለስ ዜናዊ በሐረር ከተማ በተካሄደ የኦጋዴን ክልል የፖለቲካ ባለሥልጣኖችና የሀገር ሽማግሌዎች ኮንፈረንስ ላይ ባደረጉት ንግግር "ከእንግዲህ ወዲህ እግራችሁን ጎትቶ አንገታችሁን ደፍቶ አስገድዶ ኢትዮጵያውያን የሚያደርጋችሁ ኃይል የለም" ሲሉ መናገራቸውን በመንግስት ሚዲያ የተዘገበ ሲሆን ስለኢትዮጵያ አንድነት የሚቆጩ ወገኖች ይህን የፕሬዝዳንቱን ንግግር ከአንድ የሀገር መሪ የማይጠበቅ ኃላፊነት የጎደለው በማለት ይተቻሉ።

መጪው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት "የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል" የሚለውን አንቀጽ መያዝ እንዳለበት ሁሉም የሶማሌ ብሔረሰብ ድርጅቶች ያምኑበታል። ሰሞኑንም የአካባቢው ሠላም አስጊ እየሆነ መምጣቱንና በየመንገዱ ላይ በተጠመዱ ፈንጂዎች ተሽከርካሪዎች መመታቸውን አንድ የዜና ምንጭ የዘገበ ሲሆን አንዳንድ አለምአቀፍ ድርጅቶች አባላቱ ወደዚህ አካባቢ እንዳይጓዙ ማስጠንቀቁን ዜና ምንጩ ጨምሮ ገልጿል። የኦጋዴን ክልል በኮሌራ ወረርሽኝ መጠቃት እንደደረሰበትና የረሃብ ደመና እያንዣበበት ያለ ሥፍራ መሆኑም ይታወቃል። ■

## ኢህአዴግና የተቃዋሚዎቹ ፍጥጫ በሕገመንግሥት ላይ!

በአቶ ክፍሌ ወዳጆ የሚመራው የሕገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ረቂቅ ሕገ-መንግስቱን የማርቀቅ ተግባሩን አጠናቆ ለተወካዮች ም/ቤት ማስረከቡን መንግስታዊ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። በረቂቅ ሕገ-መንግስቱም ላይ የተወካዮች ም/ቤት ውይይት እያካሄደ ሲሆን በአንዳንድ ጉዳዮችም ላይ ከስምምነት መድረሱም ታውቋል።

የተወካዮች ም/ቤትን ውይይት እንደዘገበው መንግስታዊ የዜና ምንጭ ከሆነ ወደፊት የሚመሠረተው የኢትዮጵያ መንግስት ስያሜ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ እንዲባል፣ የኢትዮጵያ የግዛት ወሰንም የፌዴራሉ አባላት ወሰኖችን የሚያጠቃልል ሆኖ በአለምአቀፍ ስምምነቶች መሠረት እንዲሆን፣ አማርኛ የፌዴራሉ መንግስት የሥራ ቋንቋ እንዲሆንና የአሁኑ የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ የፌዴራሉ ሰንደቅዓላማ እንዲሆን ም/ቤቱ ተስማምቶበታል ተብሏል። ሕገ-መንግስት የማጽደቁን ሂደት "በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በውይይት የተሳተፉበት በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ነፃና ዲሞክራሲያዊ ልምምድ" ሲሉ የሽግግር መንግስቱ ባለስልጣኖች ቢያወድሱትም ተቃዋሚ ኃይሎች ደግሞ ከደርግ ጊዜ ሕገ-መንግስት ቀረጻ ጋር የተመሳሰለ የኢህአዴግ ካድሬዎችና ደጋፊዎች ብቻ የተሳተፉበት ፋይዳቢስ የፖለቲካ ጨዋታ ሲሉ ያጥላሉታል። መንግስታዊው ጋዜጣ አዲስ ዘመን በሕገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ሊቀመንበሩ በአቶ ክፍሌ ወዳጆና በፕሬዚዳንት መለስ መካከል የተደረገውን የሰነድ ርክክብ ዜናና ፎቶግራፍ ይዞ በወጣ ማግስት የአንድ የግል ጋዜጣ ደግሞ ሕዝብ ጆርባውን የሰጠው በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የሕገ-መንግስት ሠነድ ርክክብ ካርቱን አትሟል። የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንት መጋቢት 28 የተከበረውን የድል በዓል አስመርኩዘው ባደረጉት ንግግር "እልፍ አእላፍ የህዝብ ልጆች የተሰዉለትን የዲሞክራሲ ሂደት በምንም ምክንያት በማንኛውም አኳኋን እንዲደናቀፍ አንፈቅድም። የዲሞክራሲ ሂደቱን በትክክል ለማስፈፀም የሽግግር መንግስቱን ቁርጠኝነት ማንም ሊጠራጠር አይገባውም" ሲሉ አስጠንቅቀው ነበር። ይሁን እንጂ በርካታ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕገ-መንግስት ማርቀቁን ሂደት በመቃወም መግለጫ አውጥተዋል። የኢዲኃቅ ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ከስዊዘርላንድ በላከው መግለጫ "በጥቂቶች የሚዘጋጅ ሕገ-መንግስት የሕዝብ መተዳደሪያ አይሆንም" ሲል ሕገመንግስቱን "እዋከቦና አደናግሮ ኢትዮጵያን ለመግዛት ወያኔ ያዘጋጀው ዳግማዊ ሴራ" ብሎታል። የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ባወጣው መግለጫም አምባገነናዊ ሥልጣኑን ለማጠናከር ኢህአዴግ ሽርጉድ የሚልበት ሕገመንግስት የኦሮሞን ሕዝብ አይመለከትም ሲል አቋሙን ገልጿል። የኦሮሞ ነፃነት እስላማዊ ግንባር (ኦነእግ) ከፍተኛ ባለስልጣን ሠሞኑን ለአንድ ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ ኢህአዴግ የኦሮሞንሕዝብ ፍላጎት አክብሮ ጦሩን ወደ ትግራይ



ካልመለሰ ይዋል ይደር እንጂ የከፋ አደጋና ውርደት እንደማይቀርለት አስጠንቅቀዋል። አያይዘውም ሕዝብ በጠመንጃ አፈሙዝ በሚገዛበት አገር በሕዝብ ተሳትፎ ሕገመንግስት እየረቀቀ ነው ብሎ ማለት ሕዝብን መናቅና በመብቱም ላይ ማፌዝ ነው ብለዋል። ከሕገ-መንግስቱ በፊት በአንድነት ወይም በነፃነት ምርጫ ላይ ለኦሮሞ ሕዝብ የሬፈረንደም መብቱ ሊረጋገጥለት ይገባል ሲሉም የድርጅታቸውን አቋም ገልፀዋል። የሠላምና የዲሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ም/ቤት መጋቢት 16 ቀን ባወጣው መግለጫ አማራጭ በሌለበት በአንድ ድርጅት ተፅዕኖ ሥር የሚዘጋጀው ሕገመንግስትም ሆነ የሚካሄድ ምርጫ "ባዶ የፖለቲካ ጨዋታ ነው" በማለት ኢህአዴግን ኮንኗል። የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት ሊቀመንበር ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ለአንድ የግል ጋዜጣ በሰጡት ቃለምልልስ የደርግ ሕገመንግስት እንደፈረሰ ሁሉ ኢህአዴግ የሚደክምለት ሕገመንግስትም ተመሳሳይ ዕጣ እንደሚገጥመው ተናግረዋል። የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአህድ) በሕገመንግስቱ ዝግጅት ላይ ሃሳቡን እንዲያካፍል ለተደረገለት ጥሪ "የሕዝብ ነፃ አስተያየት በአንድ ቡድን በሚካሄድ ፖለቲካዊ ውሸንብር እንዲደናገር ተደርጎ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በታገደበት ሁኔታ ተዘጋጀ የተባለው ሕገ-መንግስት የኢትዮጵያ ጠላቶች ሀገሪቷን ለመበታተን በየዘመኑ ያወጠነጥኑላት የነበረውን ስልት ዕውን ማድረጊያ ፖለቲካዊ ቅንብር ነው" ሲል ኢህአዴግንና በአምሳሉ የቀረጻቸው ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ኮንኗል። የተወካዮች ም/ቤትንም አስገራሚ ስያሜ ለራሳቸው የሰጡ ህዝብ ያልመረጣቸው ግለሰቦች ስብስብ ሲል ነቅፏል። በሌላ በኩል በሂደቱ በመግፋት የሕገ-መንግስት ጉባዔ አባላትን ለመምረጥ ዕጩ የጉባዔው አባላት ራሳቸውን ለሕዝብ ማስተዋወቅ መጀመራቸውን የመንግስት ሚዲያዎች አስታውቀዋል። ለሕገ-መንግስት ጉባዔ አባላት የቀረቡት ብዙዎቹ የግል ተወዳዳሪዎች ናቸው ተብሏል። አንድ የግል ጋዜጣ ስለዚህ ሁኔታ ሲዘግብ "የድርጅት መለያ ልብሳቸውን (ማሊያቸውን) አውልቀው ወደ ውድድር የገቡ የፖለቲካ ተጫዋቾች" ሲል አፊዟል።

## ርግማን የተደረገባቸው ዶክተሮች አዲስ ፓርቲ አቋቋሙ።

በሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ም/ቤት ውስጥ የፖለቲካና የጎሳ ድርጅቶችን በመወከል በምክር ቤቱ ውስጥ የነበሩ አምስት ግለሰቦች ከወከሏቸው ድርጅቶች አንጃ በመፍጠር የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢብዲፓ) የተሰኘ ፓርቲ ማቋቋማቸውን ይፋ አደረጉ። ግለሰቦቹ በተወካዮች ም/ቤት ውስጥ የወከሏቸው ድርጅቶች በልዩ ልዩ ምክንያት ም/ቤቱን ለቀው በወጡበት ጊዜ ተወካይ ግለሰቦቹ የምክር ቤቱን ወንበር በድርጅቶቹ ስም ይዘው የቆዩ ናቸው።

የሽግግር መንግስት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፈቃደ ገዳሙ፣ የም/ቤት አባል ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል፣ የም/ቤት ፀሐፊ አቶ ተስፋዬ ሐብሶንና የሕገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ሰብሳቢ አቶ ክፍሌ ወዳጆን የያዘው ይህ አዲስ ፓርቲ "የመንግስት ተለጣፊ አይደለሁም። ከቻርተሩ የተለየ አቋም አራምዳለሁ። በመገንጠል ላይ ሃሳባችንን ቀይረናል" ቢልም በብዙ ኢትዮጵያውያኖችና የተቃዋሚ ኃይሎች ዘንድ በጥርጣሬ ዓይን እየታየ ነው። በተለይም የጉራጌ ድርጅትን ይወክሉ የነበሩት ዶ/ር ፈቃደ ገዳሙና ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል በድርጅቱ ሕልውና ላይ በፈፀሙት ጥፋት በጉራጌ ባህል መሠረት ከቤተ-ጉራጌ (ከጉራጌ ህዝብ) ተወክለው በመጡ ተወካዮች ተረግመዋል ተብሏል።

የፓርቲው መቋቋም ይፋ እንደሆነ የዘገቡት የግል ጋዜጦች "የተረገሙ ዶክተሮች ያቋቋሙት ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ" ሲሉ ተችተዋል። ከኢህአዴግ ጋር ተቃዋሚ መስሎ የተሰየመው ይህ ፓርቲ ወፊት በሚደረገው ምርጫ ኢህአዴግ ብቻውን ተወዳዳሪ እንዳይባል ለማደናገር ብቅ ያለ የዘመኑ ጉልበተኞች የፖለቲካ ብልጠት ነው ሲሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይገልፁታል።

## አቶ አበራ የማነአብ ተለቀቁ።

አዲስ አበባ ላይ በተካሄደው የሠላምና የዕርቅ ጉባዔ ላይ የኢድኃቅን የሠላም ልዑካን ቡድን በመምራት ወደ አገራቸው ሲመጡ ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ተይዘው በእስር ላይ የቆዩት አቶ አበራ የማነአብ ሚያዚያ 5 ቀን 1986 ዓ.ም የዋለው የወንጀል ችሎት በነፃ አሰናብቷቸዋል። አቶ አበራ የተከሰሱበት ወንጀል በሰሜን ኢትዮጵያ ክልሎች ከግንቦት ወር 1983 መጨረሻ ጀምሮ እስከመስከረም ወር 1984 ዓ.ም ድረስ በሽግግሩ መንግስት ላይ ጦርነት በማካሄድና በማነሳሳት፣ ሐሰተኛ ወሬ በመንዛት የመንግስትን አለምአቀፋዊና ብሄራዊ ክብር በሚነካና በሚጎዳ አኳኋን በመድፈርና የታጠቀ ኃይል አዲስ አበባ ማስገባት የሚሉ ናቸው። ቀደም ሲል ሌሎች የልዑካን አባላት ሲፈቱ በመገናኛ ሚዲያዎች የተገለፀው አቶ አበራ የማነአብ በቀይሽብር ወንጀል የሚፈለጉ በመሆናቸው ሊፈቱ አለመቻላቸው ነበር።

እንደ ፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት አቶ አበራ የማነአብን አስመልክቶ መንግስት ሁለት ኢላማዎች ነበሩት። አንደኛ ከሌሎች ልዑካን በመነጠል በሚደርስባቸው የሞራል ድቀትና የአዕምሮ ጭንቀት ወደራሱ ለማስጠጋት ወይም ተለጣፊ ድርጅት እንዲያቋቁሙ ለማድረግ የተለመደ የቆረጣ ስልት ሲሆን፤ ሁለተኛው ይህ ባይሳካ ደግሞ በፍ/ቤት ሥነስርዓት በነፃ ፈትቶ የዳኝነቱን አሠራር "ነፃ" መሆን ለማሳየት የተጠቀመበት የፕሮፓጋንዳ ስልት ነው ይሉታል። በችሎቱ የተገኘው ሕዝብ በፍ/ቤቱ ውሳኔ በመደሰት አድናቆቱን በእልልታና በጭብጨባ ገልጿል።

## የኮሌራ በሽታ ስጋት

በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎች በከፍተኛ ፍጥነት በመዛመት ላይ ባለ የደም ተቅማጥና የማጅራት ገትር በሽታዎች በርካታ ሰዎች መሞታቸው ተዘግቧል። በጋምቤላ አካባቢ በደም ተቅማጥ በሽታ ከተለከፉት 566 ሰዎች መካከል 85ቱ፣ በማጅራት ገትር ከተያዙት 38 ሰዎች መካከል 18ቱ፣ መሞታቸውን መንግስታዊ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። በአሰላ ከተማም በንጹህ የመጠጥ ውኃ እጥረት ሳቢያ እየተስፋፋ በመጣው የተቅማጥ ወረርሽኝ 9 ሰዎች ሲሞቱ 140 ሰዎች በበሽታው መለከፋቸው ታውቋል። ይህ የተቅማጥ ወረርሽኝ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ መከሰቱን ሕብረተሰቡ ዘንድ በስፋት የሚወራ ሲሆን ይህ ወረርሽኝ ኮሌራ ሳይሆን እንደማይቀር ከፍተኛ ስጋት አለ። ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ ዓለማቀፍ ድርጅቶች በሽታው ኮሌራ ነው በሚል ስጋት ሠራተኞቻቸው ለሽርሽርም ሆነ ለሥራ ጉዳይ ወደክፍለ ሀገር በሚዘዋወሩበት ወቅት ብርቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ምክር መስጠት መጀመራቸው ታውቋል። ከዚህ ቀደም በቢቢሲ የሬዲዮ ጣቢያ በአዲስ አበባና በሐረር ከተሞች በውኃ እጥረትና በመጨናነቅ የኮሌራ ወረርሽኝ ሊከሰት ይችላል የሚል የባለሙያ ግምት መኖሩን ጠቁሞ እንደነበር ይታወሳል። ስለዚህ ጉዳይ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሰጠው ማብራሪያ ግን በሽታው ንጽህናው ያልተረጋገጠ ውኃ በመጠጣት የተከሰተ የተቅማጥ በሽታ እንጂ ኮሌራ ለመሆኑ ምንም የደረሰኝ መረጃ የለም ሲል አስተባብሏል።

## አዲስ የትምህርት ፖሊሲ

ከመስከረም 1987 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የሚውል የትምህርት ፖሊሲ መውጣቱን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ። በዚህ ፖሊሲ መሠረት የአጠቃላይ ትምህርት መደምደሚያ 12ኛ ክፍል መሆኑ ቀርቶ 10ኛ ክፍል ይሆናል። እስከ 10ኛ ክፍል ያለው አጠቃላይ ትምህርትና ስልጠና በነፃ የሚሰጥ ሲሆን ከዚያ በላይ ለሚሰጠው ማናቸውም ትምህርትና ሥልጠና እንደደረጃው እያደገ የሚሄድ ክፍያ ይከፈልበታል።

ለከፍተኛ ትምህርት ሥልጠና ለመክፈል አቅም ለሌላቸው ወገኖች አመቺ የብድር ሁኔታ ወይም በስራ ለመክፈል የሚቻልበት ሁኔታ ይመቻቻልም ተብሏል። አሁን ከሚታየው ከኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሁኔታ ግን ይህን የመንግስት አባባል ተግባራዊነት ብዙዎች አይቀበሉትም። የትምህርት ፖሊሲው በሥራ እጦትና በኑሮ ውድነት ለሚንገላታው የኢትዮጵያ ድሃ ሕዝብ ዱብ ዕዳ መሆኑንና እንደ መርዶ የሚቆጠር ነው ሲል በዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት የሚመራው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የተቃውሞ መግለጫ አውጥቷል። [redacted]

## ሚ/ር ማርክ ባስ ተነሱ፤

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ሆነው የሠሩት ሚ/ር ማርክ ባስ የረጅም ዘመን የዲፕሎማሲ የሥራ ልምድ ባላቸው ካርየር ዲፕሎማት ሚ/ር ኢርቪንግ ሂክስ መተካታቸው ተገለጸ። አዲሱ አምባሳዳር ሚ/ር ኢርቪንግ ሂክስ የሜሪላንድ ዩንቨስቲ ምሩቅ ሲሆኑ በአሜሪካ ስቴት ዲፓርትሜንት ውስጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ መሥራታቸውን የአሜሪካ ኤምባሲ ገልጿል። የአሁኑ አምባሳደር ሚ/ር ማርክ ባስ በአምባሳደርነት በኢትዮጵያ በነበሩባቸው የሥራ ጊዜያት "ኢህአዴግን ይደግፋሉ፤ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ዕውነታ የአሜሪካ መንግስት በትክክል እንዳይረዳው አድርገዋል" የሚሉ ጠንከር ያሉ ስሞታዎች ሲቀርቡባቸው ቆይተዋል። በዚህም ምክንያት "አሜሪካዊው ወያኔ"፣ "የኢህአዴግ ካድሬ"፣ ታጋይ ተጋዳላይ ማርክ ባስ" እየተባሉም ተጠቅሰዋል። የአምባሳደሩን መነሳት የአንድ የፖለቲካ ወቅት ፍጻሜ ነው በማለት የፖለቲካ ታዛቢዎች ይገምታሉ። ዜናውን የሰሙ ብዙ ኢትዮጵያውያን "ግልግል" ሲሉ የአምባሳደሩን ከኢትዮጵያ መነሳት በደስታ ተቀብለውታል። አምባሳደር ማርክ ባስ ከዚህ በኋላ የሚመደቡበት የስራ ኃላፊነት አልተገለጠም። በሌላ በኩል ባለፉት ወራት የግድያ ሙከራ የተደረገባቸው አሜሪካዊ የአሜሪካ የዕርዳታ ድርጅት ባለስልጣን ስቲቭ ሞሪስ ሳይሆኑ አይቀሩም ሲሉ ከውስጥ አዋቂ የተሰሙ ጭምጭምታዎችን አንዳንድ የግል ጋዜጦች ዘግበዋል። በዚህም መነሻነት የአሜሪካ ኤምባሲ ባወጣው ከረር ያለ መግለጫ ምንም እንኳ በዜጎቿ ላይ የግድያ ሙከራ ቢደረግም አሜሪካ በኢትጵያ ላይ የምትከተለውን አቋም እንደማትለውጥ ገልጾ "ገና በምርመራ ላይ ያለ ጉዳይ" ሲል ወሬውን ያሰራጩትን የግል ጋዜጦች ወርፏል። [redacted]

## የነዳጅ ፍለጋው ተስፋ አሳየ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ ይገኝባቸዋል ተብሎ ተስፋ በተጣለባቸው አካባቢዎች በተቆፈሩት በርካታ ጉድጓዶች የጋዝና የነዳጅ ምልክቶች እንደታዩና ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ የመጀመሪያው ምርት ለገበያ ሊቀርብ እንደሚችል የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ ልማት ድርጅት አስታውቋል።

የኦጋዴን ቤዝን ተብሎ በሚጠራው ከ300,000 ካሬሜትር በላይ ስፋት ባለው አካባቢና በጋምቤላ 30,000 ካሬሜትር የቆዳ ስፋት ያለው አካባቢ በዋነኝነት ነዳጅ ይገኝባቸዋል ተብሎ ተስፋ የተጣለባቸው አካባቢዎች መሆናቸውንም በተጨማሪ ተገልጿል። [redacted]

## የሕወሃትን ሠራዊት ለማስፈር የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ተፈናቀሉ።

በወልቃይት ጠገዴና አካባቢው ከ15,000 የማያንሰውን የሕወሃት (የኢህአዴግ) ተሰናባች ሠራዊት ለማስፈር ሲባል ከታህሳስ ወር 1986 ዓ.ም ጀምሮ የአካባቢው ነዋሪዎች ከትውልድ ቀያቸውና ከእርሻቸው ተፈናቅለው ለችግርና ለስደት መዳረጋቸውን አንድ የዜና ምንጭ ዘግቧል። በኃይል እርምጃ ቀያቸውንና እርሻቸውን እንዲለቁ የተደረጉትን ነዋሪዎች በቦታው ተገኝቼ አነጋግሬአለሁ የሚለው ይህ የዜና ምንጭ ሰራዊቱ እንዲሰፍር ሲደረግ ከቀያቸው ለተፈናቀሉት ግን ምንም የተደረገ ነገር አለመኖሩን ጨምሮ ገልጿል።

የሠፈረው ጦር ትጥቁን ያልፈታ መሆኑን ነዋሪዎቹ ገልፀው ይህም የሆነበት ምክንያት ኢህአዴግ ካለው ስጋት አኳያ በረሃውን ለመቆጣጠር አስቦ ያደረገው ነው የሚል ግምት አላቸው። በሌላም በኩል ይህ እርምጃ የተወሰደው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ያለፈቃዱ ወደ ትግራይ ተከለልኩ እያለ የሚያሰማውን የመብት ጥያቄ ለመግታትና በኃይል ለማፈን ሊሆን እንደሚችል የዜና ምንጩ አብራርቶ ትጥቁን ያልፈታ ሠራዊት በአካባቢው ማስፈሩ ምንም ዓይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ቢኖር በቅርብ ለመቆጣጠር ያስችለዋል ሲል አትቷል። በአዲሱ የኢትዮጵያ የክልል አስተዳደር የጎንደር ክፍለሀገር አካል የነበረው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ "ያለአግባብ ወደ ትግራይ ክልል ተጠቃለናል" እያለ ለመንግስት ባለስልጣኖች ተደጋጋሚ አቤቱታዎችን ማሰማቱ ይታወሳል። [redacted]

## ዳግም ረሃብና ድርቅ በኢትዮጵያ

ከ6.7 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በላይ ለከፋ የረሃብ አደጋ መጋለጣቸውን የሽግግር መንግስቱ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ጠቅሶ በመጪዎቹ ጥቂት ወራት ዕርዳታ ካልደረሰ ረሃብተኛው ሕዝብ የመኖሪያ አካባቢውን ትቶ ወደ ከተማና ወደርዳታ ጣቢያዎች ሊፈልስ ስለሚችል ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ዕርዳታ ሰጪዎች እጃቸውን እንዲዘረጉ ተማፅኗል። እንደኮሚሽኑ ገለጻ የ6.7 ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወት ለማትረፍ በሚቀጥሉት ዘጠኝ ወራት ከ750 ሺ ቶን በላይ የምግብ እህል እንደሚያስፈልግ አስመልክቶ በሀገሪቱ ያለውና በወደብ የሚገኘው አጠቃላይ የምግብ ክምችት ከሚያስፈልገው 24% ብቻ እንደሆነ ጠቅሷል።



በአብዛኛው ድርቅ የተከሰተባቸው አካባቢዎች ደቡብና ምስራቅ ትግራይ፣ ሰሜንና ደቡብ ምስራቅ ጎንደር፣ ሰሜን ወሎና ሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ቦረና ሙሉ በሙሉ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሰሜንና ደቡብ ኦሞ መሆናቸውን የኮሚሽኑ ባለስልጣኖች ገልፀው በየጊዜው በሚደርሰው መረጃ መሠረት ችግሩ ከቀን ወደ ቀን እተባባሰ ስለሆነ የዓለም ህብረተሰብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብአዊ ዕርዳታውን እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል። የመንግስት ባለስልጣኖች ረሃቡ የተከሰተው የዘንድሮ የበልግ ዝናብ በከፍተኛ ደረጃ በመዛባቱ ቀደም ሲል የነበረውን የምግብ እህል እጥረት በአስከፊ ሁኔታ ስለአባባሰው ነው ቢሉም ረሃቡ የመጣው ከተፈጥሮ ሣይሆን ከሥርዓት ድርቅ ነው የሚሉ ወገኖችም አልታጡም። የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ህብረት ባወጣው መግለጫ የረሃቡን አደጋ ለመቋቋም እድል አለማግኘቱን ገልጾ ህብረተሰቡ እንዳይሰራ፣ ስብሰባ ውይይት፣ ግምገማ በሚሉ አዘናጊ ምክንያቶች ካስራው እንዲስተጓጉል እየተደረገ ለረሃብ መጋለጡን ጠቁሟል። ተያይዞ በደረ ዜና በምዕራብ ሸዋ ክልል በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ ሕዝቡ አካባቢውን በመልቀቅ ለስደት የተዳረገ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኘው ዘላን ሕዝብ በድርቁ ምክንያት የሚያረባቸውን የቀንድ ከብቶች ድንበር እሻገረ በቁማቸው እየሸጠ ስለመሆኑም ተዘግቧል። ከጎንደር፣ ከትግራይ ከጎጃምና ወሎ፣ ከፍላተሃገራት ብዙ ህዝብ ረሃብና ድርቁን በመሸሽ ወደመሀል አገር መሰደድ መጀመሩንና በደብረብርሃንና በአዲስ አበባ ሕጻናትና ሴቶችን የያዙ ስደተኞች መታየታቸው ታውቋል።

በተጨማሪም በአፋር ክልል ከ700 ሺ ሕዝብ በላይ በኦጋዴን 300 ሺ ሕዝብ በላይ ለአስከፊ ረሃብ መጋለጡንና በሞት አፋፍ ላይ የሚገኝ መሆኑ ተዘግቧል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የከፋ ነው የሚባለው ይህ የአሁኑ ረሃብና ድር አብዛኛውን የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የጎዳ መሆኑ ሲነገር አዲሲቷ ሀገር ኤርትራ 2/3ኛ የሚሆነው ህዝቧ ለዕለት ዕርዳታ ተዳርጓል ሲል የዓለም የምግብ ፕሮግራም ሪፖርት ይፋ አድርጓል።

በሌላ በኩል መንግስት መላ ኃይሉን አስተባብሮ በድርቅ የተጎዱ ዜጎችን ከማዳን ይልቅ ሥልጣኑን ለማደላደል ዲሞክራሲያዊ ባልሆነው ሕገመንግስት ዝግጅትና የጉባዔ አባላተ ምርጫ ላይ የሀገሪቱን ሀብትና የሰው ኃይል በማባከን ላይ ነው ሲሉ የተቃዋሚ ኃይሎች በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ይከሳሉ።



ድርቅና ረሃብ የጉዳቸው ወገኖቻችን

## ኮ/ል መንግሥቱ ፓርቲ ማቋቋማቸውን ለትግል መዘጋጀታቸውን ገለጹ።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም "የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ አድርጎልኛል። አገሬ ስትደማ፣ ስትሸጥና ስትከፋፈል ዳር ሆኜ የምመለከትበት ህሊና የለኝም" ሲሉ ለትግል መዘጋጀታቸውን አስታውቀዋል። የኢትዮጵያ አንድነት መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ማቋቋማቸውንና የኢትዮየጵያ አንድነት ጠባቂ የጥቁር አንበሳ ጦር ዋና አዛዥ መሆናቸውን የገለጹት ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ኢትዮጵያ በውድቀት አፋፍ ላይ ትገኛለች ካሉ በኋላ ለዚህም ውድቀት በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በምሬት ኮንነዋል።

በስደት ካሉት ዚምባቡዌ ያስተላለፉት መልዕክት ለአንድ ሰሞን አብይ ዜና ሆኖ ሰንብቶ ነበር። እንደፖለቲካ ታዛቢዎች ግምት በአሁኑ ጊዜ በስልጣን ላይ የሚገኘው የኢህአዴግ የሽግግር መንግስት በሕዝቡ ዘንድ ተቀን ወደቀን ጥላቻን እያተረፈ በመሆኑ በሕዝቡ ዘንድ መንግስትን የሚቃወም ጽሁፍ ከመወደዱ አንጻር የግል ፕሬሶች ለኮሌኔሉ በስፋት መድረክ ሰጥተው ታይተዋል።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት መግለጫ በግል ጋዜጦች እንደተሰራጨ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ዚምባቡዌ ኮሌኔሉን አሳልፋ እንድትሰጣቸውና ለፍርድ እንዲቀርቡ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል። በኮ/ል መንግስቱ የስልጣን ዘመን የተገደሉትን ሰዎች የሞቱበትን ሁኔታ የሚመረምር ቡድንም ከውጭ አገር አስመጥቶ አሰማርቷል።

ከዚህም ሌላ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በአገር ውስጥ ባሉ የግል ፕሬሶች ላይ የእስራት፣ የማዋከብ፣ ንብረት የመቀማትና የአፈና ዘመቻም አካሂዷል። በቁጥር ከ20 የማያንሱ የግል ሚዲያ አባላት (ጋዜጠኞችና አሳታሚዎች) የታሠሩ ሲሆን የአንድ የግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና ም/አዘጋጅም እስካሁን የደረሱበት አለመታወቁ ተዘግቧል። በርካታ የግል ጋዜጦችና መጽሄቶችም በዚሁ ምክንያት ሥራቸውን ለማቆም ተገደዋል። የሽግግር መንግስቱ ይህን መሰሉን እርምጃዎች መውሰዱ ለኮሌኔሉ እንቅስቃሴ የላቀ ግምት ከመስጠት የመነጨ እንደሆነ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ። ኮ/ል መንግስቱን ለፍርድ ለማቅረብ የሽግግር መንግስቱ ያቀረበው ጥያቄ ከዚምባቡዌ መንግስት በኩል ተቀባይነት አለማግኘቱን ከዚምባቡዌ ባለስልጣኖች አቋም መረዳት የተቻለ ሲሆን፤ ሉአላዊና ዲሞክራሲያዊ መንግስት እንጂ አምባገነኖች አምባገነንን ሊዳኙ አይችሉም ሲል ኮ/ሉ ተገደው ለፍርድ እንዲቀርቡ የሚያደርገውን ግፊት የኢትዮጵያውያን መብት ማህበር ከሮም ባወጣው መግለጫው ተቃውሞአል።

በሌላ በኩል የሱዳን ሕዝቦች ነጻ አውጪ መሪ የሆኑት ኮ/ል ጆን ጋራንግ "የዚምባቡዌ መንግስት አሳልፎ የሚሰጣቸው ከሆነ እኛ አገር እንዲኖሩ ጥገኝነት እንሰጣቸዋለን" ማለታቸውን የአማጽያኑ ሬዲዮ ጣቢያ ማስታወቁ ተዘግቧል።



ኮ/ል መንግሥቱ ኃ/ማርያም

በእስከፊ ጦርነት ውስጥ ተዘፍቃ በምትገኘ የሱዳን ደቡባዊ ክፍል የሚንቀሳቀሰው ቡድን ለስደተኛው የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ጥገኝነት እሰጣለሁ ማለቱ ስውር የፖለቲካ ተልዕኮ ይኖረዋል ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

## የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት የጠራው ታላቅ ሕዝባዊ ሠልፍ በአዲስ አበባ ተካሄደ።

የኢትዮጵያ የሠላምና የዲሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ም/ቤት የጠራው ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ቅዳሜ ሚያዝያ 8 ቀን 1986 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂዷል። ቁጥር ከ70 ሺ እስከ 80.ሺ ይደርሳል ተብሎ የተገመተው የአዲስ አበባና አካባቢው ነዋሪ የኢትዮጵያን ባንዲራ አንግቦ ከማለዳው በአደባባዩ የተገኘው ምክርቤቱ በየፌርማታው በለጠፋቸው የጥሪ ማስታወቂያዎችና አርብ በወጡ የግል ጋዜጦች ላይ የቀረበለትን ጥሪ አንብቦ ነው።

የስብሰባው ዓላማ በስልጣን ላይ ያለው አካል ወሳኝ የሀገሪቱን ጉዳዮች ከህዝቡ ፍላጎትና ተሳትፎ ውጭ በብቸኝነት እየወሰነና የዲሞክራሲን ጎዳና እያጨለመ በመሆኑ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ሆነው የከፋ መስዋዕትነት ከመጠየቃቸው በፊት ይህን የባለ ጠመንጃዎችን የተሳሰተ ጎዳና ለማስለወጥ እንደሆነ የም/ቤቱ መግለጫ አስታውቋል። በዕለቱ የተለያዩ መፈክሮች የተሰሙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ባንዲራችን ክብራችን ነው። መገንጠል የሕዝባችን ጥያቄ አይደለም፣ አምባገነኖች እጃችሁን ከሕዝቡ ላይ አንሡ፣ ጠመንጃ የሕዝብ ፍላጎትን ሊገታ አይችልም፣ ለገዛ መሬታችን ኪራይ አንከፍልም፣ የሽግግር መንግስቱን አዲስ የትምህርት ፖሊሲ እንቃወማለን። ከስራቸው የተባረሩ በአስቸኳይ ወደ ስራቸው ይመለሱ፣ ለተራቡ ዜጎቻችን ሕይወት ቅድሚያ ይሰጥ የሚሉ ይገኙበታል።

በዚህ ስብሰባ ላይ የም/ቤቱ ሊቀመንበር ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ግለሰቦች ንግግር አድርገዋል።



## ዶ/ር በየነ ጴጥሮስና ሰላማዊ ሰልፈኞቹ

ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ባደረጉት በዚህ ንግግር የኢትዮጵያን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት መወሰድ አለባቸው ተብሎ የታመነባቸውን የም/ቤቱን አቋም በዝርዝር አቅርበዋል።

እነዚህም፡-

1. በዲሞክራሲያዊ አግባብ ሕዝቡና ተቃዋሚ ኃይሎች ያልተሳተፉበት ሕገ-መንግስት የማርቀቅና የማጽደቅ ሂደት እንዲቆምና በድርቅ ምክንያት የተከሰተውን የዜጎች እልቂት ለመግታት መንግስት ሙሉ ኃይሉን ያለ እድልዎ ሥራ ላይ እንዲያተኩር፤ ዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶችም ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ነጻ አካሎች አማካይነት ዕርዳታቸውን እንዲለግሱ።

2. በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚሉ ኢትዮጵያውያን ኃይሎችን ሁሉ የሚያሳትፍ ብሔራዊ ጉባዔ ትካሂዶ ወደዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትሸጋገርበት ስልት እንዲቀየስ።

3 ድርጅቶች በነጻ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ እንዲመቻች

4. በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት በየእስር ቤቱ የሚማቅቁ ወገኖቻችን በአስቸኳይ እንዲፈቱና የሰብዓዊ መብት ረገጣውም እንዲቆም።

5. ነጻ ፕሬሱን ለማፈንና የሕዝቡን የመናገርና የመጻፍ ነጻነት ለመገፈፍ የሚደረገው ሩጫ እንዲገታና የታሰሩትም ጋዜጠኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ።

6. የኢኮኖሚ ተቋማትን ያለበቂ ጥናት በማናጋትና በማፈራረስ ሠራተኛውን በፖለቲካ እምነቱ የተነሳ ከሥራ ማፈናቀሉ እንዲቆም።

7. የንግድ ህብረተሰቡን መብቶች የሚጋፋና ከአለምአቀፍ የንግድ ሥርዓቶችና ግንኙነቶች ውጭ የሚፈፀሙ አድሎአዊ እርምጃዎች እንዲቆሙ የሚሉ ናቸው።

የአማራጭ ኃይሎች ም/ቤት አባል ድርጅቶች የፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ በሚያዘው መሠረት በግልም ሆነ ቅንጅት በመፍጠር ለፓርቲ ምዝገባ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸው ተገልጾ ሕዝቡ ይህንን አውቆ በመሥራች አባልነት እንደሚዘገብና ድጋፉን እንዲሰጥ ጥሪ ተደርጎል።

በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በሚ/ር ጂሚ ካርተር ሸምጋይነት የተካሄደው የእስታራቂነት ጥረት ስልጣን ላይ ባለው የኢህአዴግ መንግስት እንቢተኝነት ቢከሽፍም ለምክር ቤቱ ዲፕሎማሲያዊ ድል እንዳስገኘም ለሕዝቡ ይፋ ተደርጓል። ■

# ልብወለድ

## "ነዳማ"

ከግርማ ዘገየ ይግለጡ

(በእውነተኛ የገጠመኝ ሕይወት ላይ
የተመሠረተ ልብወለድ)

የምሽት ክበቡ የዳንስ ወለል በታዳሚዎች ተሞልቷል። ወጣቶች ጥንድ ጥንድ እየሆኑ በለስላሳው ሙዚቃ ወገብ ለወገብ ተያይዘው ይፈሳሉ። አዛውንቶችም የወጣትነት ዘመናቸውን ለማስታወስ ከአቻዎቻቸው ጋር ይወዛወዛሉ። ከሙዚቃው ባሻገር በዳንሱ ወለል ላይ ሁሉም ስለራሱ ህይወት፣ ስለራሱ ፍቅር፣ ስለራሱ መጨረሻ፣ ስለእሱነቱ ማንነት፣ ስለቀሪዋ ህይወት ያስባል። ፍቅሩ የሆለት፣ ኩከቡ የገጠመለት፣ የተመኘው የተሳካለት "ምነው እንዲሁ እንዳማረብን መጨረሻችን በሠመረ" ይላል በልቡ ፍቅረኛውን ከደረቱ ላይ አጣብቆ። የወረት ፍቅር ዕጣ ክፍሉ የሆነውም አብራው ከምትጫወተው የሠሞኑ ፍቅረኛው አንገት ሥር ተሸጉጦ እያሙለቀ ሌላ ይማትራል። ለነገ የሚያስባትን ይቃኛል። የሱ ህይወት ወረት ነው። አፍቅሮ መዝለቅን ተፈቅሮ ማስጨረስን አያውቅም የወረት ሃድራ ሲሞላለት አፍንጫው አዲስ ጠረን ይፈልጋል። አዲስ ተፈጥሮ ይመኛል።

የድምፀ መረዋዋ የበዛወርቅ "ትዝታ" ከሠገነቱ ወደዳንሡ ወልለ ይነጥራል። ዜማ ብቻ ሳይሆን መልዕክቱና ግጥሙ ሁሉንም እየቆነጠጠ፣ ልብን ሠርስሮ በሚገባ ቅላፄ ታዳሚውን ሁሉ ጭጭ እርጭ አድርጉ በቁጥጥሩ ስር አድርጓል።

የማንነሽ ይሉኛል የማን ልበላቸው
ብቻዬን መሆኔን ምን አስጨነቃቸው
ዘመድ ወዳጅ ሁሉ ልቤን አቆሠለው
አይሆንም ወይ መኖር የማንም ሳይሆኑ
ልብ የፈቀደውን እስኪያመጣው ቀኑ

"ይቅርታ" ብንጫወት ቅር ይልሻል?
ከተቀመጠችበት ወንበር በስተቀኝ በኩል ድምፁ ወደሰማችበት ዞር ብላ ተመለከተች። በሁለት እጆቹ የተደገፈችበትን ወንበር ግራና ቀኝ ይዞ ቆሟል።
"ምን አልከኝ? ጥያቄዋ ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው ነበር። ወደጆሮዋ ጠጋ ብሎ "ሌሎቹን እንምሰል"
አላት አቋሙን ትክ ብላ ተመለከተች። በዕድሜ ብዙ አይበልጣትም አቋሙም አይነግቡ ነው። አለባበሱና ቀለም አሰካኩ ይስባል። ግን አለዛሬ አይታውም አታውቅ። ቶሎ ማስቀየም አልፈለገችም "ሙዚቃው የቧልስ ነው ደግሞ በደንብ ለሚተዋወቁና ለሚቀራረቡ እንጂ ማንም እንደፈለገው የሚጫወትበት አልመሠለኝም። ለምን የሚቀጥለውን አንጠብቅም" አለችው አምርሮ እንዳይጠፋ ድምጿን የልመና አስመስላ።
"እንዳልሽ ይሁን"ልቧ እንደፈቀደው ገብቶታል።
እንዲያውም እስከሚቀጥለው ሙዚቃ ድረስ ለመተዋወቂያ የሚሆን ግዜ በማግኘቱ አስደስቶታል።
"ይሂ ወንበር ተይዟል?" አላት አጠገቧ ወዳሉት ወንበሮች እያመለከተ ሁለቱ የጓደኞቼ ነው። አንዱ ሰው የለውም፤ ባይሆን ሲመጡ ትለቃለህ አለችው ፈገግ እያለች፤ አላመነታም። ከሷ ቀጥሎ ያለውን ወንበር ወደሷ በጣም አስጠግቶ ተቀመጠ። ግዜ ካገኘን ለምን እስከዚያ አንተዋወቅም? ደረጀ እባላለሁ እጁን ፈጥኖ ወደ እሷ እየዘረጋ፤
"ማርታ ገበየሁ" አላመነታችም እጇን ከእጁ አገናኘች፤ ተጨባበጡ።
"እህስ ኑሮ እንዴት ይዞሻል?"
"ምንም አይል፤"
"ግን አይቼሽ አላውቅም አዲስ ነሽ?"
"አዘውትረህ እዚህ ትመጣለህ?"
"አንዳንዴ በመጠኑ ብቅ እላለሁ፤ ለነገሩ "አላጋጠምሺኝም ብዬ ነው።"
"እኔ አለዛሬም መጥቼ አላውቅም ..ላገሩም አዲስ ነኝ።"
"ወደድሺው?"
"ምኑን?"
"አገሩንም ..ከተማውንም.".
"ምንም አይል.."
"ብዙ ግዜ ሆነሽ ከመጣሽ?"
"የት?"
"አሜሪካ"
"ምነው አንተ በጥያቄ አጣደፍከኝ ሠርቃለች አሉህ እንዴ የምትመረምረኝ።" ራሱን ታዘበና ሊጠይቃት የፈለገውን ሁሉ አንጠልጥሎ ተወው።
ሁለቱም ትንሽ ዝም አሉ። ምነው ቆማ ባየኋት አለ በልቡ፤ በመልኳ የአገር ቤት ጓደኛውን ገነትን ትመስላለች። ዓይኗን ዘግታ ስትከፍት የገላመጠችው መስሎት ዓይኑን ከሷ ላይ ነቀለ።
"እህ ታዲያስ?"
"አለና..."
ጨቀጨቀኝ እንዳትለው ፈርቶ እንጂ በደንብ ሊያጫውታት ፈልጓል።
"ማን አልሺኝ ስምሽን?"
"ምን ጉድ ነህ? አውቀህ ነው ወይስ ካሁኑ ረስተሽው?"
"አይ እንዲያው ለነገሩ ብዬ እንጂ ስምሽ ገነት መሆኑን አልረሣሁም፤"
"ደሞ የማን ገነት?"
"ራስሽ ነሻ"
ሣቋ መጣባት። ረስቶ ነው እንዳትል ሰም ከተለዋወጡ ደቂቃም አልቆጠረም።
"የማነህ ኮሚክ አውቀህ ነው አይደል?"
"አይ እንዲህ ላስቅሽ ብዬ እንጂ እንኳን ስምሽን ቀርቶ በእሁኑ ሰዓት ምን እንደምታስቢ አውቃለሁ።"

"የማነህ ደረቅ..የምን ማወናበድ ነው..የጠየኩህን ንገረኝ"

"ምኑን?"

"ስሜን ካልረሣሽው?"

"የምርሽን ነው እንዴ?"

ፊቷን ትክ ብሎ እያየ መሣቅ ጀመረ። በራሱ መርሳት፤ በራሱ መፍዘዝ ተገርሟል።

ሙዚቃው በማለቁ ሁሉም ወደመቀመጫው መመለስ ጀመረ። "ማርታ! እጫዋች አገኘሽ እንዴ?" ጓደኛዋ ሶስና ነበረች ወንበሯ ላይ እየተመቻቸች የጠየቀቻት።

"ቀደመችኝ.. እንጂ አንቺ ግን ስምሽን የረሳሁ መስሎሽ ነበር።" እጋጣሚውን አመሠገነ።

በዚህ ምሽት ደረጀና ማርታ በተደጋጋሚ እየተነሱ ተጫውተዋል። የማርታ ጓደኞች ሶስናና አበበች ከደረጀ ጋር አስተዋዋቂም አልፈለጉም ራሣቸውን በተራ አስተዋውቀው የከረመ ጓደኛቸው አስመስለውታል አልፎ አልፎ ሁለቱም ማርታን በዐይናቸው ገርመም እያረጉ ፈገግ ይላሉ "ቀልጣፊት" በሚል ዓይነት።

ደረጀ አሜሪካ ከመጣ 14ኛ ዓመቱን ይያዝ እንጂ ተቀማጭነቱን ዋሽንግተን ዲሲ ካደረገ ገና ሁለተኛ ዓመቱ ነው። ሁለቱን ዓመት ካሊፎርኒያና አትላንታ አሣልፏል። ግን አሁንም መሄድ.. መሄድ አገር መቀየር ይከጅለዋል። ለምን እንደሆነ ግን ለራሱም አይገባውም። ወረተኛ ልቡ ሁሌ አዲስ ነገር ፈላጊ ነው። ለፍቅርም ለመኖርያም ሁሌ አዲስ ነገር ያምረዋል።

ምሽቱ እየተገባደደ በሄደ ቁጥር ታዳሚዎች ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል። አሜሪካ እንቅልፍ የለ። ሲሄዱ ውሎ ሲሄዱ ማደር ነው። ቀን መሄድ ..ቀን መሥራት.. ማታ መሮጥ..ሌሊት በሥራ ማንጋት፤ ለሞላለት ሌሊቱም የቀን ያህል ነው። ያውም ባይበልጥ ከቀኑ ይልቅ የማታው መዝናኛ በኤሌክትሪክ ምክንያት ቀለማት እየታጀበ ውበቱ ይጐላል። ከአዳራሹ በአንዱ ጥግ በቡድን "ትዝታ" እንዲደገም ተጠየቀ። ድምፃዊቷ አላመነታችም። የደንበኞቿንና ያድናቂዎቿን ፍላጐት አለሟሟላት ዲ.ሲ.ን እንደወፈ ሠማይ ለወረረው የአዲስአባ አዝማሪ እሣልፎ መስጠት ይመስላታል። ልትጫወተው የፈለገችውን ዘፈን እሣጥራ "ትዝታን" ታወርደው ጀመር። ትዝታን ብዙ ድምፃውያን ተጫውተውታል። በክራር፣ በማሲንቆ.. በዋሽንትና በዘመናዊ መሣሪያ ወርደውታል። የሷ ግን ከሁሉ የሚለይበት ጣዕም አለው። ከጉሮሮዋ የምታፈልቀው ድምፅ ቀና ቀና ባሉት ጥርሶቿ መሃል ስለት እያወጣ ጠልጠል ባለው ስስ ከንፈሮቿ እየተላገ ወደሰሚ ጆሮ ሲንቆረቆር "ትዝታ" ህይወት ዘርቶ ህይወት ያድሳል። የጥርሷና የከንፈሯ ቅርፅ ለድምጿ ማማር አስተዋፅዖ ሳያደርግ እንዳልቀረ ብዙ አድናቂዎቿ ይገምታሉ። ከትዝታ ዜማ ጋር የምታፈሳቸው ግጥሞች የአካልን ህዋሳት የሚረግጡና የህሊና ሰመመን የሚፈጥሩ ናቸው።

ሁሉም ጥንድ ጥንድ እየሆነ ከመቅፅበት የዳንሱን ወለል ሲሞላው "መቆሚያ ቦታ እንዳያልቅ ተሽቀዳደሙ" የተባለ ይመስላል።

ደረጀ ይህን እጋጣሚ ሊጠቀም ፈለገ። እስካሁን ከእሷና ከጓድኞቿ ጋር በግልና በቡድን እየተነሣ ተጫውቷል። ግን ማርታን በግል ከደረቱ ላይ አጣብቆ ለመጫወትና ስሜቱን በጆሮዋ ለማንሾካሾክ ዕድል አላገኘም። እንቢ ብትለኝስ አለ በልቡ። ገና ከጅምሩ "ሿልስ" በደንብ ለሚቀራረቡ ፍቅረኞች ብቻ የተፈቀደ መሆኑን ስትናገር ሰምቷል። ጠይቄ ከማፈር ቢቀርብኝስ ...አይሆንም ልሞክር...ከራሱ ጋር ሙግት ያዘ። ሲፈራ ሲቸር "ማርታ ለምን እኛስ አንጫወትም?" አላት እየተቅለሰቀሰ።

"ምነው ቅድም ነግሬህ፤ ይሄ ለኛ አይሆንም፤" አለችው እንደመሽኮርመም እያለች።

ደረጀ አንዴ ከጀመርኩ አላፈገፍግም ያለ ይመስላል። ጓደኞቿ እንዲገፋፉለት በዓይኑ እየተማፀነ እሺ እንድትለው ይጐተጉት ጀመር።

"ቅድም አንተዋወቅም ነበር። አሁን ግን ትውውቅ ብቻ ሳይሆን ብዙ ተጫውተናል። ታዲያ ተነስቶ ለመጫወት ምን አስፈራሽ፤" አላት።

"መተዋወቅ ሌላ መቀራረብ ሌላ፤" ይልቅስ ይመርብህና እንደቅድሙ የአገር ቤት ጨዋታ አምጣና ትንሽ እንሳቅ። አለችው ለማስረሳት ፈልጋ።

ደረጀ ከወንበሩ ተነስቶ ቆመ። አነሣሱ አዳራሹን ጥሎ የሚሄድ ይመስላል። ግን ዕቅዱ ሌላ ነበር። ወደ ጆሮዋ ጠጋ አለና "ሽረ ባዣፒቷ ቆሜ ስለምንሽ ሰው ፊት አታሣፍሪኝ፤" አላት። ድርቅናው ገርሟት ተነሳችለት።

እጇን ይዞ እየመራ ወለል ወስዶ ቀላቀላት። የሱንም ደረት ከጡቶቿ ጋር አገናኝቶ ቀላቀለው። ለማንገራገር ዕድል አላገኘችም። እሱ የተሰማውን አካሏን ሁሉ ቢዳብስ አልተከላከለችም። ጀርባዋን ላብ ላብ አላት።

"እጉል ስትሚገቺ ጨዋታውን ከተጋመሠ ተነሣን እንጂ እንዲህ ተቀራርበን ብዙ ብንጫወት ደስ ይለኝ ነበር። ግን በደንብ እንድንተዋወቅ ሌላ ቀን ብቻችንን ብንገባበዝ?" አላት ረዥም አንገቷ ስር ሹል አገጩን አመቻችቶ።

"አይመቸኝም"

"የምን በአጭር መልስ መዝጋት ነው.. እንዴት አይመችሽም?"

"ገና መቀመጫዬን አላረጋገጥኩም፤"

"አሁን ያለሺው የት ነው?"

"ቅድም የተዋወቅካቸው ጓደኞቼ ጋ ነው ያለሁት እነሱ ናቸው የተቀበሉኝ፤"

"ከመጣሽ ምን ያህል ሆነሽ?"

"ሁለት ወሬ የነገው ሕሁድ መሰለኝ"

"እሺ ለሁሉም ስልክ ቁጥርሽን ስጪኝ"

ማርታ የጓደኞቿን ስልክ ቁጥር መስጠት አልፈለገችም። ብዙ ግዜ ከማይተዋወቅ ሰው የሚደረግ የስልክ ጥሪ ጓደኞቿን ሲያጨቃጭቅ ሰምታለች።

"እሱ እንኳን አይሆንም፤ ቁጥሩንም በደንብ አላውቀውም፤ ከፈለክ ያንተን ስጠኝ።" አለችው አምርሮ እንዳይጠፋ እየሰጋች። ሙዚቃው በማለቁ ከዚህ በላይ መነጋገር አልቻሉም። ወደቦታቸው ሲመለሱ እንደአነሳሳቸው እሱ እየመራ እሷን

እስቀደመና እሱም ከጉንዋ ቦታውን ያዘ። ሴት አክባሪነቱን በጓደኞቿ ፊት ለማስመስከር የፈጠረው ዘዴ ነበር። የምሽቱ ዝግጅት ተጠናቆ ሁሉም ወደመጣበት ለመሄድ አዳራሹን ሲለቅ ደረጀ የስልክ ቁጥሩን በትንሽ ወረቀት ላይ ፃፈና ቀስ ብሎ ለማርታ አስጨበጣት። "አደራሽን ደውይልኝ" በሚል የልመና ዓይን እየተቁለጨለጨ፤ መውጫው በር ድረስ አንድ ላይ ወጡና ተሰነባብተው ተለያዩ።

ደረጀ በገጠመው ድንገተኛ ሁኔታ ልቡ ክፉኛ በደስታ ተነክቷል። ቤቱ እስኪደርስ ማርታን እያሰላሰለና እሷን በእጁ ለማስገባት ማድረግ ያለበትን ዘዴ ሁሉ እያወጣና እያወረደ ነበር ከቤቱ የደረሰው። "ገና ፍሬሽ" አለ ጮኽ ብሎ ገና የቤቱ በር ከፍቶ ሲገባ፤ ያለእርሱ በስተቀር ቤቱ ውስጥ ማንም የለም። ጓደኛውና ደባሉ የሆነው ጥላሁን እንኳን በዚህ ምሽት ሲሰራ ስለሚያድር የተናገረውን ሰምቶ የታዘበው አልነበረም። "ምነው እንደቁመናዋ ጠባይዋም ባማረ" ይላል ማርታን ባሰበ ቁጥር። "ምነው ገና እጇ ሳላገባት ጣዕር አበዛሁ።" ራሱን መልሶ ይታዘባል። ደረጀ የአሜሪካን ምድር ከረገጠበት ግዜ አንስቶ ለመዝናናት የመረጣቸውን የሴቶች ብዛት በውል አያውቅም። እስትንፋሱን ለመርገም... ነፍሱን ለማሸነፍ ...ወንድነቱን ለመፈተን የተገኘበትና የሞቀበት መጠጋት ያውቅበታል። ዓይኑ የደነገጠባትን ...አካሉ የተመኛትን ...ወንድነቱ የመዘናትን ሴት የወረት ልቡ እስከሚንቃት ድረስ እጁ ለማስገባት ቀልጣፋ ምላሱንና ቃላት አፍላቂ አንደበቱ እኩል የማሰራት ትልቅ ተሰጥዖ አለው። በዚህ ችሎታው ቀድሞ በኖረባቸው ሁለት ከተሞች አያሌ ሴቶችን በፍቅር አክንፏል። እሱ ግን ሲያልፍም አይነካውም። የሱ ማፍቀር ካልጋ ሲወርድ ፍቅሩም አብሮ የእግር ጥፍሩ ውስጥ ይገባል።ከአንድ ሴት መርጋት ለምን እንደማይችል ራሱን ጠይቆ መልስ አላገኘለትም። ቢቸግረው የአገር ቤት ጓደኛውን ገነትን ለማስመጣት የግብዣ ወረቀር ልኮላት ለግዜው ሊሣካላት ባለመቻሏ በላከላት ወረቀት በሌላ ጊዜ ሌላ ሙከራ እንደምታደርግ ገልፃለት ግንኙነታቸው በዚሁ ተንጠልጥሏል። እሷንም ቢሆን ለብዙ ጊዜ አያውቃትም። ያንድ ሠፈር ልጆች በመሆናቸው ብቻ ለጥቂት ወራት ባደረጉት መገባበዝ በተለመደው ጥበቡ አግባብቶ የልጃገረድነት መለያዋን...የሴትነት መቀነቷን ፈትቶባታል። ይህን ካደረገ በኋላ ግን ቤተሰቦቿ በሱ ላይ ባላቸው ጥላቻ ምክንያት አዘውትረው መገናኘት ባለመቻላቸው እግሩ ካገር ሊወጣ ሲል ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ደግሞ ያገኛት። ብዙም አልተጫዋወቱም። ካገር ሊወጣ ሲል እንደጨረሰ ነግሮአት አድራሻዋን ተቀብሎ ውበቷን እያደነቀና የማትበላ ፍሬ ሆናበት ነበር የተለያት። ታዲያ አሜሪካ ከመጣ ወዲህም ስለአገር ቤት ህይወቱ ሲያሰላስል ገነትን ሳያስብ አያልፍም። "ምነው ገነት መጥታ በገላገለችኝ" ይላል አንዳንዴ ማርታን ከመተዋወቁ በፊት። አሁን ማርታ የድንገተኛ ፍቅር ዱብ ዕዳና የልቡን ምት እንዲጨምር አድርጉታል።

ሦስት ሳምንታት አለፉ። ደረጀ ከማርታ የስልክ ጥሪ ባለማግኘቱ ድንገት ናገኛት ብሎ በሥራ ቀን ሳይቀር የተዋወቁበት መዝናኛ ስፍራ ተመላልሷል። እንኳን እሷን ጓደኞቿን እንኳን ማግኘት አልቻለም "ምናለ ሳታየኝ ተከትዬ አድራሻዋን ባወቅሁ ኖሮ" ይላል በወቅቱ ሳልመጣለት ዘዴ እየተቆጨ።

አንድ አርብ ከሰዓት በኋላ ከሥራ የደከመ ሰውነቱን አሳርፎ ለረጅሙ ሳምንት ዕረፍት ለማዘጋጀት አግዳሚው ሶፋ ላይ ዘና ብሎ እንደተጋደመ ለማንሳት እንዲያመቸው አስጠግቶ ያስቀመጠው ስልክ ደጋግሞ ጮኸበት።

"ሀሎ ማን ልበል?

"እባክዎ ደረጀን አገኛለሁ?

"ደረጀ ነኝ ማን ልበል?

"እንኳን ስምሽን የምታስቢውን አውቃለሁ ስትል ከነድምጼም ጠፋህ!" የቀልድ ሳቅ በስልኩ አንባረቀበት።

"ማነሽ አንቺ?"

"ለካ ቶሎ ማግባባት ብቻ ሳይሆን ቶሎ መርሳትም ትችላለህ።"

"ኸረ በፈጠረሽ ማን ልበል?"

"እሺ ማርታ ነኝ።"

"ማር..ታ፤ እ..ሺ ቆይ አንዴ" በዱላ ጭንቅላቱን እንደተመታ ያህል ከተጋደመበት ዘሎ ቀጥ ብሎ ቆመ። ምን እንደሚመልስ አላወቀም። ያልተዘጋጁበት የስልክ ጥሪ ሆነበት። ለወትሮው መናገር የሚፈልጋቸው ቃላቶች ሁሉ ከንፈሩ ላይ ይሰበሰቡለት ነበር። ዛሬ ጠፉ... ድርቅ...ዝም አለ።

"አንተ ስልኩ ተቋረጠ ወይስ እንግዳ አለብህ?"

"ኸረ አለሁ እንቅልፍ ቢጤ ጀምሮኝ ነበር፤" አላት እንደምንም የመናገር ኃይሉን አሰባስቦ።

"ይቅርታ ረበሽኩህ፤ በል ሌላ ግዜ እደውላለሁ።"

"ኖ..ኖ ማርታ ጥሩ ግዜ ነው የደወልሽው። ታዲያ ደህና ነሽ ወይ?..ምነው ጠፋሽ? ...የት ከረምሽ?... ጓደኞችሽ እንዴት ናቸው?" አፉ ላይ የመጣለትን እያከታተለ እንደተተቀባበለ መሣሪያ ይለቀው ጀመር።

"ደህና፤" አለች ማርታ ፍጥነቱና ግራ መጋባቱ ቢደንቃት ...ሰውዬው "የጤናም ብቅል" አልቀመሰም ብላለች በሆዷ።

"ስልክ ቁጥሬ ጠፍቶብሽ ወይስ ስልክ አጥተሽ እስከዛሬ ያልደወልሺው?"

"ሁለቱም አይደል፤"

"ታዲያ ምነው?"

"አልተመቸኝም ነበር። ለዚያውም ቢሆን ይሄው ደወልኩ አይደል ...አልቆየሁም ..."

"እንዴት አልቆየሁም ትያለሽ ዛሬ እኮ ልክ ሦስት ሳምንታችን ነው።"

"ታዲያ ቢሆንስ ...አሁን የምታወራው አጥተህ ነው የምትወቅሰኝ?"

"በይ ለሁሉም እንኳን ብቻ ያልረሳሽኝ.."

"ኸረ አንተ የምትረሳ ሰው አይደለህም፤"

"እንዴት?"

"ድርቅናህ ነዋ."

"የምን ድርቅና አመጣሽ?"

"አሁንም አታድርቀኝ ለራሴ ደክሞኛል።"

"ምነው ደከመሽ ...ሥራ ጀመርሽ እንዴ?"

"አይደለም እቤት መዋሉ ራሱ ይደክማል።"

ደረጀ እሷው ባመጣችው ቀዳዳ መጠቀም ፈለገ።

"ማርታ ብዙ የምንጨዋወተው ጉዳይ ስላለ ዛሬ ማታ ለምን አንገናኝም?"

"በስንት ሰዓት?" አላመነታችም።

"በአስራሁለት ተኩል ቢሆን ጥሩ መሰለኝ። አሊያም አንቺ የሚመችሽን ንገሪኝ"

"ማታ በሁለት ሰዓት ብናረገውስ?"

"አልራቀም?"

እሱንም ጓደኞቹ በጊዜ ከመጡ እንጂ ሊራዘምም ሊቀርም ይችላል። ጭራሽ ልትያዝ ወደወጥመዱ የተቃረበች ጅግራ እንዳታመልጠው እንደሚሳሳ አዳኝ የሆነ መሰለው። አደናግሮም ቢሆን የውሳኔዋን አቅጣጫ ማስቀየር ፈለገ።

"እሺ የት ድረስ ልምጣ?" አላት የምትመልስለትን እየፈራ የምትኖርበትን ክፍል ሳይሆን የህንፃውን አድራሻ ነገረችው።

"ታዲያ ሰዓት ቢከበር ደስ ይለኛል፤" አላት በልመና ዓይነት ድምፅ ተሰነባብተው የስልኩን መነጋገሪያ ወደስፍራው ሲያስቀምጥ። "የጠፋችው ወፍ ተያዘች፤" እያለ ክፍሉን ሁለቴ ዞረው።

ብዙ ጊዜ ሳይጠፋ ለምሽት የሚሆነውን ልብሶች መራረጠና ሰውነቱን ሊታጠብ ወደመፀዳጃ ቤት ገባ።

ለምሽቱ የመረጠው ሆቴል ከአቅሙ በላይ ይሁን እንጂ እንግዶችን እንደስሜታቸው ለማስተናገድ በቂ ዝግጅት ያለው "ርካሽ ወንድ" አለመሆኑን ለማሳየት ረድቶታል።

በዚህ ምሽት ማርታና ደረጀ ብዙ ተጨዋውተዋል። እንደማታውቀው ሰው ሳይሆን እንደለመደችው ጓደኛ ዘና ብላ ነው ያመሸችው። እሱም በተቻለ ያለፈ ታሪኩን ለሷ እንደሚስማማና እንዳያስገምተው አድርጐ አጫውቷታል። እሷ ግን ብዙ አላዋራችውም። ውስጡን የምትመረምር ይመስል ትክ ብላ እያየች ነው ያዳመጠችው።

ለምን እቤቴን አታይውም? አላት ምሽቱ በመግፋቱ ሰዓቱን እየተመለከተ።

ዛሬ እንኳን አይሆንም .. ባይሆን በሌላ ግዜ እየዋለሁ። አሁን መሽቷል ቤት አድርሰኝ ጓደኞቼም ይሰጋሉ አለችው። በግትርነት ለማግባባት አልከጀለም። ችኩልና ሰፍሳፋ መሆኑ የወደፊቱን ዕቅዱን ስለሚያበላሽበት "ካልመሰለሽ እንዳልሽ ይሁን" አላትና የምትኖርበት ሰፈር አድርሷት ተሰነባብተው ተለያዩ። ማርታ የዚህን ምሽት ግብዣ ከመቀበሏ በፊት ከጓደኞቿ ጋር ብዙ ተወያይታበታለች። ሁለቱም ጓደኞቿ ካላቸው ልምድ ብዙ መክረውበታል።

በየፊናቸው ስለ ደረጀ ከውጭ ምን እንደሚወራ አስጠንተዋል። በእጅ አዙር ከነማን ጋር እንደሚውልና በተለይም ከሴቶች ጋር ያለውን ግንኙነት መርምረዋል። ግን አውቀዋለሁ የሚልና የእገሊት ጓደኛ ነበረ የሚል ፍንጭ ስላጡ "ለግዜውም ቢሆን ይሞከር" የሚል መደምደሚያ ላይ ስለደረሱ ነበር የምሽቱን መስተንግዶ እንድትቀበል የገፋፉአት።

ወራቶች ተቆጠሩ። የማርታና የደረጀ ግንኙነት ከውጭ ግንኙነት አልፎ ይፋ መውጣት ጀመረ። ማርታ በደረጀ ላይ ለግዜው ምንም እንከን አላገኘችም። በሥርዓት ያስተናግዳታል። ከፍላጐቷ ውጭ አይሆንም። ብዙም ሳይቆዩ ሃሳቡን ሞላችለት።

"ከሴት ጓደኛና ከተመሣሣይ ፆታ ግንኙነት ይልቅ ከተቃራኒ ፆታ ጋር ይበልጥ ጣዕም አለው፤" የሚለውን የፈረንጆች አባባል አመነችበት። አዘውትራ እሱ ቤት ስለምታሳልፍ መቀራረባቸው ይበልጥ እየጠነከረ መጣ። አንዳንዴ ብቻዋን ታስባለች። "አሁን የመኖርያና የሥራ ፈቃድ አለኝ፤ ለምን ሕይወቴን አዋከበዋለሁ ለምን አንድ ቦታ አልቀመጥም?" ትላለች በሃሳቧ።

ደግሞም የአሜሪካ የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት የባልና የሚስት ያህል ነው አብሮ መኖር... ሲሆን ይሆናል። ካልዘለቀ ደግሞ ይቀራል... ዛሬ በእኔ አይጀመርም... ነገ ሊመጣ ከሚችለው መጥፎ ነገር ለመሠወር ራሷን ታፅናናለች። ግን አንድ ያልወደደችው ነገር አለ። የጓደኛው የጥላሁን በአንድ ክፍል ውስጥ አብሮ መኖር ሁሌ ይከነክናታል። ከመኝታ ቤት ውጪ እንደልቧ ከደረጀ ጋር እንደልቧ መጫወት ባለመቻሏና እንደምትሳቀቅ አማከራው ስለተሰማው ከጐኑ ያለውን ክፍል ተከራይተው እቃዋን ጠቅላ ከሱው ጋር መኖር ጀመሩ።

ደረጀ ጓደኛው ጥላሁንን በመለየቱ ለግዜው ቅር ቢለውም አንድ ቀን ይህ እንደሚሆን ሁለቱም ስለሚያውቁ ብዙም አላሳሰባቸውም። ያውም ግድግዳ ለሚለየው ክፍል። ማርታ ጓደኞቿን አበበችና ሶስናን የምታገኛቸው በስልክና አልፎ አልፎ በቀጠሮ ሲሆን ቀሪው ግዜዋ የሚያልፈው በሥራዋና ለወደፊት ተስፋ በጣለችበት ቤትዋ ሆነ።

ቀናት ወራትን እየወለዱ ደረጀና ማርታ የተዋወቁበት ዓመታዊ ልደት ደረሰ። ሁለቱም ተመካክረው የሚቀርቧቸውን ጓደኞቻቸውን በመጋበዝ አንደኛ ዓመታቸውን ለሌላው በሚያስቀና ሁኔታ አከበሩ። የምትናፍቀውን የቃል ኪዳን ቀለበት ባታገኝም ጥሩ የአንገት ሀብል ዘንካታው አንገቷ ላይ አጥልቆላታል። እንግዶቻቸው በሙሉ የደስታቸው ተካፋይነታቸውን በመግለጽ ፅዋቸውን አንስተውላቸዋል፤ "መጨረሻችሁ ይመር" በሚል ዓይነት።

ዓመታዊ መታሰቢያቸውን ባከበሩ በወሩ እሷ መደርደርያው ላይ እቃ እያስተካከለች እሱ ደግሞ ያፈላችለትን ቡና እየጠጣ ያልታሰበ ድንገተኛ ጥያቄ አቀረበችለት። ከሰሞኑ አዘውትሮ መደንዘዝ አብዝቷል።

"አንተ ደረጀ ለመሆኑ አገር ቤት ፍቅረኛ አልነበረህም?"

"ምነው ጠየቅሺኝ? ልቡ ከመጠን በላይ ሲነጥር እያዳመጠ"

"እንዲያው አፌ ላይ መጣ ..እኔ እንጃ..ግን ውነት አልነበረህም?"

"የሰማሽው ነገር ካለ ንገሪኝ፤ ምን ዳር ዳር ትያለሽ፤" ከሁለት ቀን በፊት በቀድሞ አድራሻ በኩል ከገነት የተጻፈ ደብዳቤ ከጥላሁን ተቀብሏል።

"ላለፈ ነገር ምን አሳሰበህ...አሁን እንደሁ ያንድ ሰው ነህ፤ ግን እንዲያው ለነገሩ አውራልኝ፤" አለችው ዓይኑን እየመረመረች።

ደረጀ ለትንሽ ግዜ ዝም አለ። ገና ለገና ስምታለች ብሎ ነገር ማበላሸት አልፈለገም።" ግን ለምን ጠየቅሺኝ፤ ለምንስ ማወቅ ፈለግሽ፤" አላት ኮስተር ብሎ። ለወትሮው ትንሽ ቆጣ ካለ የጀመረችውን ነገር ስለምትተው ዛሬም "እሺ ይቅር ተወው" እንድትለው ፈልጐ ነበር።እሷ ግን የሱን ልብ ያነበበች ይመስል በጅምሯ ገፋችበት። "እኔስ የጠየቅሁህ እንደኔ ትወድህ እንደሆን ለማወቅ ብዬ ነው፤" አለችው። እንዳያመር እየፈራች። ደረጀ ፍርሃት ፍርሃት አለው።

ገነት በላከችለት ደብዳቤ ውስጥ በመጨረሻው መሥመር ላይ ያሰፈረችው ቃል ደጋግሞ በአዕምሮው ተመላለሰበት፤ "በላክልኝ የግብዣ ወረቀት በብዙ ውጣ ውረድና ከሁለት ዓመት ድካም በኋላ ቪዛዬን አግኝቻለሁ። በቅርቡ ስለምመጣ የመነሻዬ ዕለት እንድትቀበለኝ እናቴ ስልክ ትደውልልሃለች። እስካሁንም የቆየሁት ዘመድ ለመሰናበትና ላንተ የምሥራቹን እስክነግርህ ነበር፤ፀሎታችን ሰምሮአል" ጭንቅላቱን ግራና ቀኝ አወዛወዘው።

ሃሣቡን ለመበተን "ላለፈ ታሪክ ምን አስጨነቀሽ፤ እሷ እንደሁ ተረስታለች።" አላት በሆዱ እያጉረመረመ።

"ስሟ ማነው? የለበጣ ዓይነት ጥያቄ አስከተለች።"

"ለኔም ስሟ ጠፍቶኛል።"

"አታሹፍ ስሟ እንዴት ይጠፋሃል?"

"ግዜው በጣም ሩቅ ስለሆነብኝ ነዋ"

"ግን ልታስመጣት ቃል ገብተህላት ነበር?..." እያመነታች ጠየቀችው ደረጀ ሊጠጣ ፉት ያለውን ቡና እንትፍ ብሎ ወደሲኒው መለሰው። ምን እንደሚመልስ ግራ ገብቶታል።

"ይሄ ሰላቢ ልጅ ሳምነው ከዳኝ እንዴቸ" አለ ጓደኛው ጥላሁንን በሆዱ እየኮነነ፤ "ፀሎታችን ሰምሮአል" የሚለው የገነት ደብዳቤ ደጋግሞ አንጐሉ ላይ ነጠረበት።

"አንቺ ምነው እንዲህ አስጨነቅሺኝ፤" አላት ጥያቄዋን እንድታቆም በዓይኑ እየተለማመጠ።

"አንተ ምነው እንዲህ አረገህ...ለምን ስሟን አትነግረኝም?"

"ገነት መብራቱ" ትባላለች አላት ፍርጥም ብሎ።

ይህንን ስም የሆነ ቦታ ሰምታዋለች ግን የትና መቼ እንደሆነ ሊመጣላት አልቻለም።

"ልታስመጣትስ አስበህ ነበር?"

"እንኳን ላስመጣት እዛው እያለሁ ካገር ሳልወጣ ነው የተቀያየምነው።"

"በቃ እሷ እንኳን አድራሻህን ፈልጋ ልትታረቅህ አልሞከረችም?"

"ካገር መውጣቴን ማን ነግሮአት.."

ከዚህ በላይ መቀጠል አልቻለችም። ጨዋታ ቀይራ ወደመኝታቸው ሄዱ። ሳምንቱን በሙሉ ደረጀ ካለወትሮው መነጫነጭ አብዝቷል። የምትለውን አይሰማትም፤ አዘውትሮ ለብቻው መሆን ይፈልጋል። ብዙም ትኩረት ስላልሰጠችው የደረጀ ለውጥ ለማርታ ለግዜው አልታወቃትም። እሷ ግን የምታስበው ሌላ ነው። በሥራ ቦታም ጭምር አዕምሮዋ ውስጥ የሚወራጭ አንድ ትልቅ ሕልም አላት። "ሕጋዊ ጋብቻ" ትዳር ሁለት ጉልቻ... ሠርግ...ጫጉላ ሽርሽር... ወላጆቿን ካገር ቤት አስመጥታ የልጅነት ወጓን ልታሳያቸው ትፈልጋለች፤ "ታዲያ መቼ?" ትላለች በሃሳቧ። ከዚህ የተሻለ ግዜና አማራጭ እንደሌለ ታውቃለች። ግን ከሁለቱ ማንኛቸው የጋብቻ ጥያቄ ያንሳ። "ለወጉማ ጥያቄው መምጣት ያለበት ከወንዱ ነው። ግን እሱ በፍርሃት ካላነሣው ለምን እኔ አልጠይቀውም። ያለነው በሰለጠነው ዓለም። ሴቱም ወንዱም እኩል ስሜቱን በሚገልጽበት ምድር፤" ትላለች ራሷን ስታደፋፍር። አንድ ቀን ለሊት ወደማንጊያው ላይ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰችውና ዋናውን ርዕስ ሳታነሳ የባጥ የቆጡን ማውራት ጀመረች። ለወትሮው ጠዋት ሥራ ከመሄዳቸው በፊት ማለድ ብለው በመነሣት ወሬና ልፊያ ስለሚይዙ ነገሩ እንግዳ አልሆነበትም። ፊቱን ወደሷ አዞሮ ጀርባዋን መዳበስ ሲጀምር እጇን አንገቷ ላይ ጠምጥማ በለሆሣሳ "ደረጅዬ" አለችው።

"ምነው!"

"ግን ለምን?". ብላ ሣትጨርስ ቁምነገሩን አንጠልጥላ ተወችው። "ምን ልትጠይቂኝ ፈለግሺ?" አላት እንዳታነሣበት የሚፈራውን አርዕስት እየፈራ።

"ግን ለምን ስለ ግብቻ አንድ ቀን እንኳ አውርተን አናውቅም?"

"እኔ እንጃ!"

"እንዴት እኔ እንጃ፤ ባንተ በኩል ሃሣብ የለህም?" አለችው አፍ አፉን እያየች።

"ትንሽ እንቆይ ብዬ ነው።"

"ዓመት እኮ አለፈን ሌላው ቢቀር ቀለበት እንኳን ብናስር፤"

"የት ይሄድብናል ብለሽ፤ እኛ እንደሆን ይኼው እስካሁን አለን፤"

"ቢሆንም።"

"በወረቀትና በፊርማ ታምኛለሽ?"

"ባላምንም ሁሉ ነገር በተገቢው ዕድሜና ግዜ ሲሆን ደስ ይላል።"

"እኛን ደስ ካለን ሌላው የራሱ ጉዳይ።"

"እስቲ አስብበት"

ልትመልስለት የፈለገችውን ሳትጀምር የበሩ ደወል ደጋግሞ አቃጨለ። ደረጀ ከአልጋው ተፈናጥሮ ተነሣና በሩን ሲከፍት ጓደኛው ጥላሁን በመኝታ ፒጃማ በሩ ላይ ቆሟል። ደረጀን ካገር ቤት ስልክ እንደሚፈልገው ቀስ ብሎ አንሾካሾኮለት ወደ ክፍሉ ገባ። ደረጀ ጥሪው ከየት እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልወሰደበትም። እየተርበተበተ ለማርታ ጓደኛው የገጠመው ችግር እንዳለበት ነግሯት ከቤት ለመውጣት ወደበሩ ሲያመራ "ልጠብቅህ ወይስ ብቻዬን ሻወር ልውሰድ" አለችው የወትሮ ልምዷ እንዳይቀርባት። "ጉዳዩ ከረዘመ ሊያስቆየኝ ስለሚችል አንቺ ጣጣሽን ጨርሰሽ ወደ ሥራሽ ሂጂ" ብሎ በሩን ከፍቶ ወደ ጥላሁን ክፍል አመራ።

"ኸረ ይቆጥርባቸዋል ቶሎ አንሳና አነጋግራቸው" አለው። የሚጠጣ ብጤ ሊያመጣ ወደማቀዝቀዣው እየሄደ። እጁ እየተንቀጠቀጠ ጠረጴዛ ላይ የተደፋውን የስልክ መነጋገሪያ አነሣ።

"ሃሎ ማን ልበል"

"ደረጀ ነህ?" የሠለለ የቀጭን ሴት ድምፅ

"አዎ ነኝ"

"እፀደ ነኝ... የገነት እናት ረሣኸኝ እንዴ?"

"ኸረ አልረሣሁም፣ ...ስማቸው ቢረሳውም ድምፃቸው አዲስ አልሆነበትም"

"ገነት የፃፈችው ደብዳቤ ደረሰህ?"

"አዎ ደረሶኛል።"

"ሂውልህ ልጄ ሆነላት። መችም ሰው ካሰበው የግዜር ይበልጣል"

"እንዴት ሆነላት? በማረጋገጥ ዓይነት። "ሂደች በቃ ትናንት ሸኘናት።"

"የት ሂደች?"

"ሎንደን ገብታለች፣ ዛሬ ማምሻውን አንተጋ እንደምትደርስ ደውላ ነግራኛለች፣ ለዚህ ነው የደወልኩልህ" አሉት።

"ግን ደህና ገባች? ለንደን" አለ ንግግሩ እየተሰባበረበት።

"አዎ ደህና ገባች፣ እንግዲህ አደራህን፣ አሁን ትልቅ ሰው ናችሁ ልጅነት የለም፣" አሉት።

"ኸረ ግዴለም እማማ" አላቸው ቃሉን እየደጋገመ።

"በል እንግዲህ እንደገባች ደውልልኝ" አሉት። ልጃቸው ገነት በፍርሃት ያልነገረችውን ስልክ ቁጥር ደጋግመው እየነገሩት። ስልኩን ወደመነጋገሪያው ሲያስቀምጥ ከእጁ ላይ ላቡ ጠብ ሲል ተሰማው። ሰውነቱ በሙሉ ትኩሳት ብሎታል። ጥላሁንን በጨረፍታ ቀስ ብሎ አየው። መልስ አልሰጠውም። "ምን ታስባለህ?" አለው ጠጋ ብሎ

"ስለምኑ? "ጥላሁን በነገሩ ግራ ተጋብቷል"

" መምጣቷ እኮ ነው።"

"ማናት እሷ?"

"ገነት"

"የማናት ገነት?"

"አንተ ደግሞ ትረሳለህ የአገር ቤቷ ጓደኛዬ ናታ"

"እና?"

"ምን ትመክረኛለህ?"

"ትምጣ ታዲያ አሜሪካ እንደሁ ሰፊ ነው"

"እኔ ጋ እኮ ነው የምትመጣው"

"ታዲያ መቀበል ነዋ"

"ከዚያስ?"

"ሜዳውም ፈረሱም ይኼው እንላታለና"

"እናቷ እኮ አደራ ነው የሚሉኝ"

"ታዲያ ተቀብለሃት ወደምትፈልግበት ሸኛት፣ ከዚያ በላይ ምን ታደርጋለህ"

"እዚህ አገር ሰው አታውቅም"

"እናስተዋውቃታለን"

"አንተ ደግሞ የሰው ችግር አይገባህም"

"ታዲያ ምን እንድልህ ፈለክ፣ ይልቅስ አሁን ሌላ ነገር እንዳይመስልብህ ቤት ግባና ማርታን ወደስራዋ አድርሳት፣ ቀሪውን በኋላ እንነጋገራለን።" አለው ፊቱን ከስክሶ"

እሱ ወደቤት ሊገባ በር ሲከፍት ማርታ ሰዓቱ በመርፈዱ ልትጠራው ልትወጣ ስትል ተገናኙ። ቃላት አልተለዋወጡም እንደተናደደች ገብቶታል። ቶሎ ልብሱን ለባብሶ እየተንደረደረ ደረጃውን ወርዶ መኪናውን ማሞቅ ጀመረ።

"አንተ ሳትታጠብ ነው እንዴ የምትወጣው?" እየተነፋነፈች ጠየቀችው።

"ቶሎ አድርሼስ ተመልሼ እታጠባለሁ"

"ለሥራ አይረፍድብህም?"

"ደውዬ እነግራቸዋለሁ"አላት። በጉዞአቸው ላይ እንደወትሮው ብዙ አላወሩም፣ መሥሪያ ቤቷ በራፍ ላይ አውርዷት እየተጣደፈ ተመለሰ። ወደቤቱ አልገባም በቀጥታ ያንኳኳው ጥላሁን በር ነበር። የጀመሩትን ንትርክ ቀጠሉ።

"እሺ ምን ወሰንክ?" አለው ጥላሁን። ለውይይታቸው መክፈቻ እንዲሆን።

"አንተ ከተባበርከኝ አንድ ሃሳብ አለኝ።"

"ልስማዋ!"

"እየህ ማርታን እንደምወዳት አንተም ታውቃለህ ግን..".

"ግን...ምን?"

"ግን..". ሊነገር የፈለገውን ፈራው

"ምን አስፈራህ ንገረኝና ልወቀው? አትወድህም?"

"ትወደኛለች ግን... የምንዘልቅ አይመስለኝም"

"የግል ችግር አለባት?"

"እሱ ብቻ አይደለም እየፈራኋት መጣሁ።"

"ለምን?"

"እኔ እንጃ።"

"እንዳው ገና ለገና አዲስ ለምትመጣው ብለህ ንፁኋን ልጅ ስም አታውጣባት"

"አልገባህም። ችግር አለብን ነው የምልህ!"

"በል ችግሩን ሌላ ጊዜ ትነግረኛለህ አሁን የወሰንከውን ንገረኝ።"

ደረጀ በቅርብ ጓደኛው ፊት ትዝብት ላይ መውደቅ አልፈለገም። ጨንቆታል። በአዕምሮው የገንትና የማርታ ምስል እየተመላለሰ ይመጣበታል። የወረት ልቡ ... አዲስ ፈላጊ ገላው፤ ወደ ገነት ያደላበታል። ሲፈራ ሲቸር "እሺ ልንገርህ" አለ በረዥሙ ተንፍሶ።

"ገነት ዛሬ ከጠዋቱ 5 ሰዓት ከለንደን ተነስታ ማታ እዚህ እንደምትገባ ነግሬሃለሁ። በቅድሚያ አውሮፕላን ማረፊያ ሄደን የምንቀበላት እኔና አንተ ነን።ለግዜው ሁኔታዎች እስኪመቻቹ አንተ ጋ ትቀመጣለች። ከዚያ በኋላ ያለውን እኔ እወጣዋለሁ።" አለው የጓደኛውን ዓይን በመፍራት ወደ ወለሉ አንገቱን ሰብሮ። ጥላሁን የደረጀ መጨረሻ ምን እንደሆነ ለማወቅ ባይችልም አዝማሚያው ገብቶታል።

"ማርታ ብትጠይቅ ምን ትመልሳለህ?

"ያንተ እህት አስመስለህ እናስተዋውቃታለን።"

"በግል ቢነጋገሩስ?"

እንዳይገናኙ ለአንድ ሳምንት ያህል መላ መፍጥር ይቻላል"

"እንዴት ላንድ ሳምንት... ከሳምንት በኋላ ምን ልታደርግ አስበሃል?"

"የዓመት ፈቃዴን ወስጄ አገር ላስጐበኛት ካሊፎርኒያ ገነትን ይዤ እሄዳለሁ"

"ከዚያስ?"

"ከዚያማ ቦታው ከተስማማኝ ... አሜሪካ እንደሁ ሰፊ ነው።"

"ላትመለስ?" የትዝብት ጥያቄ ነበር

"እኔም እሷም ከወደድነው ማለቴ ነው።"

ጥላሁን የደረጀን ዳርዳር ማለት ገብቶታል። የክፉ ቀን ባለውለታው ስለሆነ ተናግሮ ሊያስቀይመው አልፈለገም። ግን በዚህ የሰይጣን ተግባር ላይ መተባበሩ ነፍሱ በሲዖል አዳራሽ ውስጥ የምትንሳፈፍ መስሎ ታየው። ብዙ አልቆዩም ከሰዓት በኋላ ሊገናኙ ተቃጥረው ወደፈናቸው ተበታተኑ።

የቀኑ ብርሃን ለምሽቱ ተራውን በሚያስረክብበት ወደ አንድ ሰዓት ገደማ ማርታ የዕለቱ ረጅም ሥራዋን ጨርሳ በሃሳቧ የወሰነችውን ለመፈፀም ወደትልቅ ገበያ አዳራሽ አመራች። ገቢዋ መጠኑ እንዲጨምር ብዙ ሰዓት መስራት ከጀመረች ከረምረም ብላለች። የቤት ዕቃ ለመለወጥና የወደፊቱን ዕቅዷን ለማሟላት ገንዘብ ወሳኝ መሆኑን ስለምታውቅ የረጅም ግዜ ተስፋዋ እንጂ የጉልበት ድካሟ አይታያትም። የገበያ ዕቃ መኖሪያውን ጋሪ እየገፋች ወደ ውስጥ ዘለቀች። ለወትሮው የምትገዛቸውን ሸቀጦች ጫኝችና ወደመጠጥ መደርደሪያው ክፍል አመራች። አንድ የሻምፓኝ አንድ የወይን ጠርሙስ አነሳችና ወደሌላው መደብር አለፈች። አንድ ረጅም ሻማ ጨመረችበት። የገበያ ጣጣዋን ጨራርሳ ሂሣቧን ከፍላ ገበያውን ጥላ ወጣች። ሰውነቷን ግን አንድ የማታውቀው ነገር ያስጨንቃታል። ጠዋት አልጋ ላይ የጀመረችውን ቁም ነገር በዛሬ ምሽት ስለምትወጣ ተንፍላ እስክታራግፈው ድረስ አይምሮዋ ተረብሿል።

የሻማዎቹ አቀማመጥ ... ሁለት ወይን የተሞሉ መለኪያዎች... ጠረጴዛው መሃከል ትኩስ ቀይ አበባ ... ደረጀና እሷ ግራና ቀኝ ተቀምጠው... ቀለበት የሚያደርጉበት ቀን ሲወስኑ ... ዘሎ ሲጠመጠምባት በሃሳቧ ታያትና ፈገግ አለች። በጣም ካልተቸገረች በስተቀር ከሥራ ስትመለስ ደረጀ እንዲወስዳት አትደውልለትም። በአብዛኛው የሥራ ሰዓታቸው ስለሚለያይ የሚያደርሳት ካጣች በአውቶቢስ ስለምትጠቀም ወደ መጠበቂያው ተጠግታ ቆመች።

ግን የማታውቀው አንድ መጥፎ ስሜት ሰውነቷን ይወረዋል። አንጉሏን ያስጨንቀዋል። ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻለችም። እቤቷ ገብታ ለምሽቱ የሚሆን ዝግጅት ስትጀምርም ትከሻዋን ከፉኛ ከብዶታል። "ምነው ደረጀ በግዜ መጥቶ በገላገለኝ፤" አለች ለራሷ ብቻ በሚሰማ ድምፅ።

ጥላሁንና ደረጀ የተገናኙት ከተቃጠሩበት አንድ ሰዓት ዘግይተው ነው። ሲገናኙ ሁለቱም ተደናግጠዋል። ምንም አልተነጋገሩም። የጥላሁንን መኪና አቁመው ሁለቱም በደረጀ አሽከርካሪነት ወደ "ዳላስ አውሮፕላን ማረፊያ" በረሩ። ባለረጅም ሽንጡ የብርቲሽ አየር መንገድ ገነትን ከነኮተቷ አሳፍሮ በአሜሪካን ምድር ላይ ያንዣብባል፤ ለማረፍ ተራውን እየጠበቀ። ደረጀ የማርታን ምስል በመኪናው የኋላ መስታወት ውስጥ የተመለከተ መስሎት ዓይኑን አርገበገበ።

"ምነው ዝም አልክ" አለው ጥላሁንን። ዞር ብሎ።

"ከህሊናዬ የማይፋቅ ፀፀት ውስጥ ከተትከኝ፤" አለው እንባው ቅርር እያለ "ምስኪን ማርታ" አለ በሆዱ ከሳምንት በኋላ የሚሆነው የትርዒቱ መጨረሻ እየናፈቀው።

---

የዚህ ልብወለድ ደራሲ ግርማ ዘ[illegible]የ ይግለጡ የዲካልብ ኢሊኖይ ነዋሪ ሲሆኑ የላንዳፍታ መጽሔት የጽሑፍ ዝግጅት ተባባሪ ናቸው።

---

## ውድ አንባብያን፤

በገጠመኞች ላይ የተመሠረቱ ልብወለድ ታሪኮች ካላችሁ ላኩልን። በተለይ ጀማሪ ደራሲያንን ለማበረታታት ይህ አምድ ትልቅ አስተዋጽዖ አለው ብለን እናምናለን።

# Addisu Gebeya አዲሱ ገበያ

## We Carry Large Selection Of Ethiopian Foods & Spices

***We have everthing you need to prepare an Ethiopian Feast !***

| DESCRIPTION | QTY(lb) | Price |
|---|---|---|
| 1. Berbere | 1/2 | 3.99 |
| 2. Miten Shiro | 1/2 | 3.50 |
| 3. Aja | 1/2 | 3.50 |
| 4. Mitmita | 1/2 | 3.50 |
| 5. Awaze | 1/2 | 3.99 |
| 6. Butter Maker | 1 | 13.99 |
| 7. Tef | 1 | |
| 8. Mekelesha | 1 | 13.50 |
| 9. Kik | 1 | 0.49 |
| 10. Bakela | 1 | 1.79 |
| 11. Miser | 1 | 0.89 |
| 12. Kinche | 1 | 0.39 |
| 13. Telba | 1 | 1.25 |

NAME____________________
ADDRESS____________________
____________________
CITY____________________
STATE________ ZIP________
Tel. (   )________________

**WE DO MAIL ORDER**

Please Include $5.50 For Shipping And Make Your Check Or Money Order Payable To: Addisu Gebeya

- JEWELRY
- VIDEOS
- CASSETTES
- REKEBOTE (ረከቦት)
- COFFEE
- ETHIOPIAN ARTS
- ETHIOPIAN DRESS

AND MUCH MORE

2202 18th St. N.W.,
Washington, DC 20009
202 •986 •6013 / 23

# ሞዴት ~ ModEth

የኢትዮጵያ ቃላት ማተሚያ
Ethiopian Word Processor

ግዕዝ NAmi
ግዕዝ Pro
ግዕዝ in WordPerfect
for Windows
ግዕዝ

ኢትዮጵያ





Ethiopian Computers & Software
9781 W. Fremont Pl.
Littleton, Colorado 80123, USA

Tel: (303) 972-2186
Fax: (303) 973-4342

# የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብወለድ)

ከገረሱ

ካለፈው የቀጠለ

## ክፍል ሰባት

የፈጠነ ዕቅድ ጓደኛውን ካሣሁንን ከዴብራ አላቅቆ ከአበሻ ሴት ጋር ከማስተዋወቅ ቢሆንም ስለራሱ ቢሆን ከሰናይት ጋር አብሮ ለዘላቂነት መቆየቱን እርግጠኛ አይደለም። እና ሰናይትን እንጋገሮ ከጓድኛዋ ከራሔል ጋር እንደተዋወቀ በወጣው ዕቅድና በተያዘው ቀጠሮ መሠረት ሰናይትና ራሔል እንዲሁም ካሣሁንና ፈጠነ አንድ ምግብ ቤት ውስጥ ተገናኝተው ራት ከመቅረቡ በፊት ጨዋታ ጀምረው እንዳለ ነበር ያለፈው እትም ላይ ያቆምነው።

ካሣሁን የራሔል ብዙ አለመናገርና ለምትጠይቀው መልስ አጭር መልስ ብቻ መስጠቷ የማወቅ ጉጉቱን ጨመረበት። በጨዋታቸው መሃል ራሔል አጠር ያለ መልስ የምትሰጥበትን ሰናይት ተቀብላ እየተንጣጣች መመለሷ አናደደው። ሳትጠየቅ የምትለፈልፈውን ዴብራን የወደደው ካሣሁን ለምን አሁን ሰናይትን እንደጠመዳት ለራሱም ግራ ሳይገባው አልቀረም። ወይስ አበሻ ከሆነች ረጋ ያለች መሆን አለባት የሚል ስሜት ስላለው ይሆን ወይስ የሰናይት እንደዛ መሆን እንደፈረንጆች ልሁን ማለቷ ይሆን?

ሰናይት ስታወራ የሚንቀሳቀሰው ከንፈሯ ብቻ ሳይሆን ዓይኗ፣ አንገቷ፣ እጇ ሁሉም መስሎ ታየው። በሆዱ "የማናት በልጣጣ" አለ። "አሁን እኮ እንደፈረንጆቹ መሆኗ ነው"። መለስ ብሎ ራሔልን አየት አድርጎ ዝምታዋና ርጋታዋ የበለጠ እንዲያስባት ያደረገው እንጅ አንድ ነገር በሃሣቡ መጣበትና በሆዱ ሳቅ አፈነው። "እልጋ ውስጥም እንዲሁ ረጋ ያለች ከሆነች ምን ፋይዳ አላት" ዴብራ ትዝ አለችው። ጨዋታው ደርቶ፣ ራቱም ቀርቦ፣ ካሣሁንም በሃሣቡ ውጣ ውረድ ውስጥ እያለ ፈጠነ በዓይኑ ጠቀሰው። መጀመሪያ አልገባውም ነበር፣ ኋላም ወደ ሽንት ቤት እንሂድ ማለቱ ገባውና እሱ ቀድሞ ተነስቶ ይቅርታ ጠይቆ ሄደ። ትንሽ ቆይቶም ፈጠነ መጣ።

"ታድያስ" አለው ፈጠነ በመጓጓት

"ምነው ዝምታ ታበዛለች" አለው ካሣሁን እጁን እየታጠበ በመስታወት ፈጠነን እየቃኘ።

"ተፈጥሮዋ ሊሆን ይችላል፣ ግን እንዴት ናት? ቤሎ አይደለችም?"

"ደስማ ማለት ደስ ትላለች። የዚህ ዓይነቷን ሴት handle ማድረግ ትንሽ የሚያስቸግር አይመስልህም?"

"ምን ችግር አለበት?"

"ዝም ስትል በሆዷ ነገር የምታስብ ትመስላለች" አለው ካሣሁን።

"እንግዲህ ይቺን ፈልፍሎ ማውጣት ያንተን ቅልጥፍና ይጠይቃል፣ ግን ወድደሃታል አይደል?"

"እስቲ የመውደዱን ነገር እናቆየውና ደስ ብላኛለች ልበልህ፣"

"ጌታዬ ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም፣ እና እንግዲህ እወቅበት።"

እነፈጠነ ቀደሟት እንጂ ሰናይትም ራሔልን ይዛ ወደሽንት ቤት ለመሄድና ትንሽ ወሬ ለብቻቸው ለመቦጨቅ አቅዳ ነበር። የነሱ ቀድሞ መሄድና እነሱ ብቻቸው መሆናቸው አጋጣሚውን ፈጠረላቸው።

"ታድያስ ራሔል ምን ይመስልሻል?" አለች ሰናይት

"እኔ እንጃ እባክን፣"

"ጥሩ ሥራ፣ ጥሩ መኪና አለው።"

"ባክሽ የሱ መኪናና ሥራ ለራሱ ነው ዋናው ነገር ጠባዩ ነው" አለቻት።

"አንዳንዴ አንቺ ሞኝ ነሽ ልበል? ጠባይ እንዳያያዙ ነው። ጠባይ አለው ተብሎ ከማንም ችጋራም ጋር ጊዜ ከማጥፋት ጠባይ ባይኖረውም ጥሩ ኑሮ የሚያኖርን ሰው ይዞ ጠባዩን ለመቀየር መሞከር የሚቀል ይመስላል።"

"እኔ ጠባይ ከሌለው የሱ ገንዘብና ሀብት በአፍንጫዬ ይውጣ"

ቆይ እሺ እሱም ይሁን፤ አሁን ስታይው ጠባዩ ላይ ምን መጥፎ ነገር አየሽበት?"

"እንዴ በአንድ ቀን ይታወቃል እንዴ ጠባይ?"

"እሱስ አይታወቅም። ማለቴ አቀራረቡ፣ አነጋገሩ፣ ለሴት ልጅ ያለው ክብር መቼስ ይህን በአንድ ጊዜ መገመት ይቻላል "አለቻት ትክ ብላ እያየቻት።

"በዚህስ ሰው አክባሪ ይመስላል። ደግሞ በወንድ ልጆች ላይ የምጠላው ጉራ አላይበትም። ቁጥብ ይመስላል፤" የመፍቀዷ አዝማሚያ ነበር።

"እና የሚሄድ አይመስልሽም"

"እሞክራለሁዋ"

እነካሣሁን ተመለሱና መቀመጫቸውን ያዙ። አይነጋገሩ እንጂ እየፈጠኑ ወደ ሽንት ቤት የሄዱት ስለነሱ ለማውራት መሆኑን እነሰናይት ያውቃሉ። እነፈጠነም ቢሆን እነሱ ወደሽንት ቤት ሲሄዱ እነሰናይት ስለነሱ እንዳወሩ አውቀውታል። ሁለቱም በየልባቸው "ምን ተባብለው ይሆን ማለታቸው አልቀረም። ከራቱ ስነስርዓት በኋላ ሁሉም ተያይዘው

በሴቶቹ ውሳኔ ላይ ሄዱ። የሚኬድበትም ሲኒማ ቤት፣ የሚታየውም ፊልም ወሳኟ ሰናይት ነበረች። ካሣሁን ደስ አላለውም።

የዴብራን መንቀዥቀዥ የፈቀደው ካሣሁን የሰናይት መቅበዝበዝ አልዋጥለት አለው። ራሔልን እንዲፈቅድ ያደረገው ምናልባት በሰናይት የመንቀዥቀዥ ባህሪ መነጽር አይቷት ሳይሆን ይቀራል።

ፊልም መግቢያው ሰዓት እስኪደርስ ድረስ መኪና ውስጥ ቁጭ ብለው ጨዋታ ጀመሩ። አየሩ ነፋሻና ደስ የሚል በመሆኑ ሁሉም የመኪና መስኮታችውን ከፍተው ነበር። ሰናይት ከፈጠነ ጋር የኋላ ወንበር ላይ ራሔል ፊት ከካሣሁን ጋር ቁጭ ብለው ነበር። በፈጠነ ፕላን የተደረገ ነበር። ፈጠነና ሰናይት ከኋላ የራሳቸውን ወሬ ጀመሩ ካሣሁን ወሬ መጀመር እንዳለበት ገባው።

"ታድያስ ሥራ እንዴት ነው?" አለ ካሣሁን መለስ ብሎ እያያት።

"ደህና ነው ምንም አይል?" አለችው ራሔል።

ቀጥሎ ደግሞ ምን ይበል፤ ጠፋው። ሁለቱ ብቻ እንኳ ቢሆኑ የሚለው አይጠጸፋውም ነበር። ቀጥታ ወደቁምነገሩ ይገባ ነበር። አሁን ግን እነፈጠነ ባሉበት ቦታ ትንሽ ደስ የማይል መስሎ ታየውና ዝምታውን መረጠ። ቢያንስ ሲኒማ ቤት እስኪደርሱ ድረስ።

"ያንተስ ሥራ እንዴት ነው?" አለችና ራሔል ሳያስበው ጠየቀችው።

"ደህና ነው፣ ምን ይላል ብለሽ ነው፤" አላት

ቀጥሎ ለማውራት አርዕስቱ ደግሞ ጠፋ። የሚያወራው ጠፍቶት እንኳ አልነበረም። አሁን ሌላ ሰው አለ። በተለይ ሰናይት።

የሲኒማ ቤቱም ሰዓት ደረሰና ተሰልፈው ቲኬታቸውን ገዝተው ገቡ። ፈጠነ ለሰናይት፣ ካሣሁን ደግሞ ለራሔል ገዛ። የምሽት ፊልም ተመልካቾች ሁሉም ባይሆኑ ባብዛኛው ጥንድ ጥንድ ነበሩ። እጅ እጅ ተያይዘው ወንድና ሴቶች ይበዛሉ። አዳራሹ ሲገቡ በአንድ አካባቢ ለአራቱ የሚበቃ ቦታ ማግኘት ባለመቻላቸው በተለያየ አካባቢ ግን የተቀራረበ ቦታ አገኙና ካሣሁን ከራሔል ጋር፣ ፈጠነ ከሰናይት ጋር ቁጭ አሉ። አሁን ለወሬ ተመቻቸው።

"አሜሪካን እንዴት አገኘሽው ታድያ?" አለ ካሣሁን ቀስ ብሎ።

"ከልኩ አያልፍም ባክህ፤ እኔ አገር ቤት በጣም ይናፍቀኛል።" አለችው ራሔል፣ ከልቧ ነበር።

"ትዝታው ገና አልጠፋልሽም ማለት ነው?" ይላታል።

"ከመጣሁ ስንት ጊዜ እንደሆነኝ ለመጠየቅ ፈልገህ ነው አይደል? " አለችው ፈገግ ብላ፤

እንደማፈርም አለ መልስ ሳይሰጣት ትንሽ ቆየት አለና "ይገርምሻል እንዲህ ብዬ መጠየቅ ቀርቶ ሌላው ሲጠይቀኝ ያናድደኛል" አላት።

"እንዲህ ብሎ መጠየቁ እኮ ክፋት የለውም። የሚጠየቅበት አንዳንድ ምክንያት ነው የሚያናድደኝ እኔም። እዚህ አገር በተቆየበት ጊዜ የግለሰብን ችሎታ፣ አስተሳሰብና ማንነት ለመገመት ከተጠየቀ ያናድዳል። አይመስልህም?"

"ልክ ነሽ ራሔል፣" አላትና የቅድሙ የሰናይት አጠያየቅ ከየትኛው ይሆን ብዬ ልጠይቃት ብሎ ለአፍታ አሰብ አደረገና ተወው።

"እኔ ከመጣሁ ወደ አራት ዓመቴ ነው። እየተረጓጐምህ ረዥምም አጭርም ልትለው ትችላለህ፣ ግን እኔ ይበልጥ በቆየሁ ቁጥር የቤተሰብና የአገር ናፍቆት እየጠነከረብኝ እንጂ እየቀነሰ ሲምጣ አልተሰማኝም" አለችው ራሔል ከልቧ ነበር።

"እንዴት ነው ጓድኛ አለሽ?" አላት እየፈራ እየተባ፣ ዱብ ያደረገው ጥያቄ ነበር።

"ጓደኛ ስትል?" አለችው።

"ማለቴ ቦይ ፍሬንድ" አላት።

ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች ጓደኛ ቢኖረኝ ከሱ ጋር እዚህ ምን አደርጋለሁ? እንዴት ቢገምተኝ ነው? ምን ማለቱ ነው? ምን ዓይነት አቀራረብ ነው?" የተለያዩ ነገሮች በአዕምሮዋ ተመላለሱ፣ "ምን እንድለው ፈልጐ ነው?" እና ፈገግ ብላ ፊቱን ለአፍታ አየችና ዝም አለች።

"ምነው የማይገባ ጥያቄ ነው? አላትና እሱም ፈገግ አለ። "የጠየቅሁበት ምክንያት ቢኖረኝ ነው" አላት

"ምንድነውሱ?" አለችው

"ማለቴ አየሽ ብቸኝነት ሲበዛ የአገርና የቤተሰብ ናፍቆት ይበዛል የሚል ዕምነት ስላደረብኝ ነው?" አላትና የምትለውን በጉጉት ጠበቀ።

"አይምሰልህ! እኔ እንደሱ ታይቶኝ አያውቅም"

"ማለት ጓደኛ ኖሮሽ አይተሰዋል ማለት ነው?" አላት።

"ከዚህ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም ለምን በቀጥታ አትጠይቅም? አሁን ቦይፍሬንድ አለሽ ወይ ብለህ?" አለችውና ሳቅ አለች።

"እሺ፣ አለሽ?" አለና ሳቅ አለ።

"የለኝም፣ " አለችው።

ካሣሁን ቁና ተነፈሰ። "አለኝ!" ብትለው ኖሮ ምን ሊያደርግ ነበር። ግልጽ መሆኗ ደስ አለው። መለስ ብሎ ዙሪያውን ቢያይ ወንዱና ሴቱ ተቃቅፎ ቁጭ ብሏል። ሰናይትም ተንጠራርታ ፈጠነ አንገት ሥር ሽጉጥ ብላለች። ሳቅ አለ።

"ምነው ዝም አልክ?" አለችው ራሔል ድንገት፤ እሱ ሃሣብ ይዞት ጭልጥ ብሏል። ብዙ ነገር በሃሳቤ መጥቶ ይጉላላ ጀመር። ቦይፍሬድ አለሽ ወይ ብያት "የለኝም" ካለች እንግዲህ ፈቅዳኛለች ማለት ነው። የለኝም ማለቷ መፈለጓን

ለመግለጽ ነው? ወይስ እንደሌላት ለመናገር ብቻ ነው? አንድ የሰማው ነገር ትዝ አለው። አንዱ አንዷን ይቀርብና "ቦይ ፍሬንድ አለሽ?" ይለታል።

"የለኝም?" ትለዋለች

"እንግዲያውስ ቦይፍሬንድሽ ልሁን? ይላታል

"የማነው ገገማ" ብላ ጥላው ትሄዳለች።

አሁንም ሁኚኝ ብዬ ብላት እምቢ ብትለኝስ? "ገገማ" ብትለኝስ እያለ ከፊልሙ ባሻገር ከሕሊናው ጋር ይሟገት ጀመር።

ወሬው ከራሔል መልስ በኋላ መቋረጡ ራሷም ራሔልንም ሳይገርማት አልቀረም። "ቦይፍሬንድ አለሽ ወይ አለኝ፣ የለኝም አልኩት ታድያ ምነው ከዚያ በኋላ ዘጋው?" እሷም ሃሣብ ገባት።

እንደምንም እየፈራ እየተባ እጁን በወንበሯ ራስጌ አሻግሮ ትከሻዋ ላይ አሳረፈ።

በቃል ከማውራት በተግባር ማሳየት ይሻላል ብሎ በመወሰን። ጥቂት ቆይቶም ትከሻዋን ጫን አደረገው። መለስ ብላ አየችውና ፊቷን ወደ ፊልሙ መለስ አደረገች። ከፊት ለፊታቸው የተቀመጡት ሁለት ወንድና ሴት ጓደኞች ተጠማጥመው ፊልሙን ረስተው የሚያደርጉትን ለአፍታ አየችና ትከሻዋ ላይ ባረፈው ክንድ ሳቢያ የተሰማትን ስሜት ማስታመም ጀመረች። በዓይኗ የምታየው ፊልም ሌላ በውስጠ ሕሊናዋ የተቀረፀው ፊልም ሌላ ሆነባት "ራሔል" አለ ካሣሁን ትከሻዋን ጨበጥ አድርጐ

"እ...ቤት" ብላ ወደሱ ፊቷን መለስ ስታደርግ ከንፈሩ ተቀበላት። ከንፈሩ ከከንፈሯ ተገናኝተው ቀሩ። እሷም እሱም በዓይናቸውም በሕሊናቸውም የሚያዩት ፊልም አንድ ሆነ።

ካሣሁን የዚያን ምሽት ራሔልን በአዕምሮው እንዳረገዘ የስልክ ቁጥርዋ ተቀባብለው የሚገናኙበትን ቦታ ወስነው ተለዩዩ። እንደዲብራ ወደ ቤቱ አልወሰዳትም። ሲኒማ ቤቱ ውስጥ በመተሻሸት የተነሳ የጋለውን ስሜቱን ይዞ ቀረ። ሰናይትንና ራሔልን ከሸኙ በኋላ ካሣሁንና ፈጠነ ብቻቸውን ቀሩ።

"ምን ይመስልሃል?" አለው ፈጠነ።

"እንጃ ባክህ፣ ረጋ ያለች ትመስላለች፤"አለ ካሣሁን።

"ረጋ ማለቷን ነው የጠላሀው?"

"ዝምተኛ መሆኗ ያስፈራል።"

"እንዴብራ ቅዥቅዥ ስላላለች ነው?" አለው ፈጠነ በመገረም።

"ጥሩ ልጅ ትመስላለች።" አለ ካሣሁን።

"እንግዲህ እወቅበት፣ አሁን እንግዲህ የቀረን የነዴብራን ደግሞ ማየት ነው። ጉድ ልናይ ነው። ለመሆኑ መቼ ነው ቀኑ? የምንገናኘው ከሷ ጋር? " አለው ፈጠነ በጉጉት።

"የሚቀጥለው ሳምንት አልተባባልንም? አንተ ደግሞ ትረሳለህ መሰለኝ? "

"ከጓደኛዋ ጋር ነው የምትመጣው አይደል? የሚሆነውን በጉጉት እየጠበቅሁ ነኝ።" አለ ፈጠነ።

"አዎ ከጓደኛዋ ጋር ነው።" አለ ካሣሁን።

"እኔ መቼም ከእነሱ ጋር የምግባባ አልመሰለኝም።"

"ሃሳብ አይግባህ፣ እነሱ ያግባቡሃል። መቼ እንደኛ ሴቶች እንጀባ የሚያበዙ መሰለህ። ከወደዱህ ወደዱህ፣ ከጠሉህ ደግሞ ጠሉህ ነው። ያንን ወዲያው ነው በተግባር የሚያሳዩህ። እየወደዱህ መቅለስለስ፣ መግደርደር፣ Pretend ማድረግ የለም። ሁሉ ነገር ግልፅ ነው። " አለው ካሣሁን።

"ልናይ አይደል! "

"ታያለህ አይዞህ!" አለው ካሣሁን።

ፈጠነን እመኪናው አድርሶት ተሰነባብተው ተለያዩ። እሱም ወደቤቱ አዘቀዘቀ። ራሔልን በሃሣቡ ይዞ። እንደዴብራ ቢሆን ኖሮ እሱ ሳይጠይቅ ራሷ ይህንን ምሽት ሙሉውን የደስታ መጐናፀፊያ ባደረገችለት ነበር። ምን ያደርጋል ታዲያ "ተግደርዳሪ ጦም አዳሪ" ገጠመወና ትራሱን አቅፎ ሊተኛ ሆነ።

"ምን አለ ሴቶቻችን ሰልጠን ቢሉ?"

(በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል።)




# ኑሮ በአሜሪካ

## የሴንት ሉዊስ ኢትዮጵያውያን ተመክሮ

ከኢትዮጵያዊያን መረዳጃ ማኅበር በሚዙሪ የቦርድ አባላት።
ሴንትሉዊስ ሚዙሪ።

እኛም ከዚህ በፊት ስለእርስበርስ የመረዳጃ ማኅበራት ወይም የኮሚኒቲ አሶሲዬሽን አስፈላጊነታቸውን በመጥቀስ የዘገባቹሁትንና እንደዚሁም ጠቃሚ ምክርንና ተመክሮን በማሳየት በላንዳፍታ ላይ ያስፈራችሁትን በሚገባ መርምረን አንብበናል። ጽሑፉ እጅግ ወቅታዊና አንገብጋቢ በመሆኑ የማኅበሩ አባላት በሰፊው ተወያይተውበታል። ይህ ጽሑፍ ከአምስትና ስድስት ዓመታት በፊት ቢጻፍ ኖር በአሜሪካ የኮሚኒቲ ማኅበራት ምንኛ ባደጉ ነበር። ከዚህ በፊት ማኅበራትን ለመመሥረት በየእስቴቱ ከፍተኛ ተጋድሎ መደረጉ የሚታመን ነው፤ አንዳንዶቹ ዐቢይ እንቅስቃሴ በማድረግ በማስተማርና በመመካከር ሲያድጉ፣ ሌሎቹ ደግሞ በውዥንብር የኢትዮጲያውያን መደራጀትን በሚጠሉ ባለአጀንዳዎችና አሉባልታ አናፋሾች ፈርሰዋል ወይም ተዳክመዋል። ይህንንም ለማቃናት በርካታ የሕዝብ ልጆች ከሕይወት በመለስ ባለፉት አሥር ዓመታት ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነትን ከፍለዋል።



ታዋቂዋ የሴኔት ሉዊስ ከተማ Arch
(courtsey - Mr. Charles McCllum
Friend of Ethiopians St. Louis)

ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታና ፈተና በመመርመር በስደት ላይ የሚገኙ ኢትዮጲያውያን በመሰባሰባቸው፣ ማንነታቸውንም በማግኘት ("self-discovery")፣ የኢትዮጲያን አስተዋፅዖና ታሪካዊ ክብር ለማሳወቅ የአንድነት ስሜት በማደጉ ማኅበራት በየቦታው እየተመሠረቱና እየተጠናከሩ ነው። ይህንንም በማስተማርና በመቀስቀስ ላንዳፍታ የተጫወታቸው ሚና እጅግ የሚያኮራ ሰብዓዊ በረከት ነው።

የኮሚኒቲ ማኅበራት ትርፍ አልባ (Not-For Profit) ኢፖለቲካዊ (Non-Political) በመሆናቸው ርዳታንና መንግሥታዊ መስተዋፅዖን (donations) በሚመለከት ዕድገታችንን ለማራመድ በምንሠራበት ወቅት የኅብረተሰቡ አባላት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቻዋል። የማኅበራትን በሕግ የተደነገገ ኃላፊነት መረዳቱ ተገቢ ነው። ይህም ሲባል በሰብዓዊ መብት ላይ በሕግ የታወቁ ኢፖለቲካዊ ማኅበራት አቋም አይወስዱም ማለት አይደለም። ሰብዓዊ መብት አንዱ የጥብቅና (Advocacy) ዘርፍ ነው። ከዚህ በፊት የመንግሥቱ ኃ/ማርያም አስተዳደርን ሆነ የአሁኑ መንግሥት ያደረሱትን ሰብዓዊ በደል አጋጣሚዎችን በመጠቀም ለአሜሪካኖችና ለማኅበር አባላት አጋልጠናል።



ሕፃናት መዝሙር ሲያሰሙ

ዳግመኛም በአሜሪካ የኢትዮጲያውያን ማኅበራት የሰብዓዊ መብት ጥያቄን በሚያነሱበት ወቅት ነገሩን በማምታታት ያለውን መንግሥት የሚቃወም ሁሉ አማራ ወይም ነፍጠኛ ነው በማለት እያደናገሩ ቅስቀሳ የሚያደርጉ ግለሰቦች እንዳሉም ተረድተናል። ይህም ትምሳሌና ጭንጋፍ ቅስቀሳ እኛም አካባቢ ተንፀባርቆ ነበር፤ ሆኖም በግልፅ ሳይወጣ በጉምጉምታነቱ ከሽፏል። ይህን የመብት መረገጥ በሚመለከት ሕሊናዊ ድምፅን (conscience) በማሰማት ኢትዮጲያውያን የተቃወሙት ያለውን መንግሥት እንጂ የአንዱን ልዩ ብሔር ሕዝብ አይደለም። ወገን ሳይለዩ፣ የተወሰነ መስመር ሲያራምዱ ኢፖለቲካዊ ማኅበራት በሰው ልጆች መብት መረገጥ፣ በድንቁርና በበሽታና ማሀይምነት ላይ በመዝመት የተቻላቸውን ማድረግ ይኖርባቸዋል። መሽካከርና መጠራጠር እንዲጠፉ የእኛም ማኅበር ሁሉንም እርዳታ ፈላጊ በቅንነት በማገልገል እንደዚሁም ካለመድልዎ በእኩልነት በመርዳት ኢትዮጵያዊነቱን አስመስክሯል።

ማኅበራትን ለማጫጫት ከፋፋዮች የሚጠቀሙበት ዘዴ እጅግ የረቀቀ ነው። የኢትዮጲያዊያን ማኅበራት የትርፍ አልባልነትና ኢፖለቲካዊ ይዘት በውል በመረዳት ፖለቲካዊ ፍልሚያ ውስጥ ጠልፎ ለማስገባትና ሸርን በመጐንጐን በኋላም ለረዳት ድርጅቶች ይህ የፖለቲካ ማኅበር ነው በማሰኘት ጥላሸት በመቀባት (Blackmail) ያደረጉት ጥረት ኢትዮጲያዊያንን በበለጠ አስተምሮአቸዋል። ይህንን ደባ ማንኛውም ኢትዮጲያዊ ሳይታክት መታገል ይኖርበታል። በመካከላችንም የዚህ ብሔር ወገን፣ የከተማ / የገጠር ልጅ ሬፈውጂ / ሲትዝን፣ ተማሪ /ጐብኝ፣ ባለሀብት / ድኃ፣ ባለትምህርት /መሀይም፣ ጴንጤቆስጤ / ኦርቶዶክስ...ወዘተ በማለት ለመበታተን የሚደረጉትን ቅስቀሳዎች ሁሉ እያሌ ማኅበራት ነቅተውበት እጅግ በሚያኮራ መንገድ ወገኖቻቸውን በእኩልነት ለመርዳት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው፤ የኛውም ከዚህ የተለየ አይደለም። እጅጉን የሚገርመውና የሚያሳዝነው ኢትዮጲያዊ ጥቁር እንዳልሆነ ሁሉ "እነዚህ የባርያ ፈንጋይ ርዝራዦች ናቸው" በማሰኘት በጥቁር አሜሪካ ወገኖቻችን ለማስጠላት የተደረገ ሙከራም ነበር። ኢቶዮስ በግሪክ የተቃጠለ ፊት፣ ጠቋራ ማለት ነው።



የሲንት ሉዊስ እህቶቻችን በአኩሪ ያገር ልብስ



በጥንት ዘመን ኢትዮጲያ የሚለው ቃል አብዛኛው የአፍሪቃ ንፍቀ ከበብ እንደሚያጠቃልል ዝነኛ የግሪክ ጸሐፊዎች እነሄሮዶቶስ በማይሞት ጽሑፋቸው ላይ ያሠፈሩት ነው። ከሰሜን ከደቡብ፣ ከምዕራብ ከምሥራቅ ጋር ተደባልቀናል፤ የኢትዮጲያውያን እሥራኤሎች ታሪክ ዋነኛ ምሥክር ነው። የኩሽ ዘሮች ከሴማውያን ጋር በረዥሙ የሀገራችን ታሪክ ከልዩ ልዩ የዐረብ፣ የፊንቃውያን አውሮጳውያን የፖርቹጋል፣ የስፓናሽ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝብ ጋር ተዛንቀናል። ለዚህም ነው ይህን በማብራራት አንድ የጥንት ግዕዝ ጸሐፊ "ኩሽ ወሊዶ ለኢቶጵስ ዘውዕቱ ወአበሆሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ" ያሉት። በጐንደር የኦሮሞ ደም እንደሌለ፣ የነአፄ ሱስንዮስና የነበካፋ ታሪክ ተረት እንደሆነ፤ በራያና ቆቦ/በወሎ የኦሮሞ ዘርና ሥልጣኔ እንዳልሠረገ፣ በጎጃም በሸዋና በደቡብ የትግራይና የኤርትራ የዘር ፍሬ እንዳልተስፋፋ፣ የብሔረሰቦችን ታሪክና ሒደት በመነጠል፣ እነአፄ ዮሐንስ ለኢትዮጲያ ባይተዋር እንደሆኑ ሁሉ ሕዝቡን ከሕዝብ ለማባላት የሚናፈሰው አዲስ የፈጠራ ታሪክ በየጊዜው ይሰማል።፤ ከዚህም ተያይዞ "ይህ ብሔር አይግዛ ነው የሚሉት" የሚል ቅስቀሳ በአሜሪካ በአንዳንድ ሥፍራዎች ተከስቶ ለማሳመን ባለመቻሉ ተቀባይነትን አጥቷል።

በርግጥም አንዳንድ ኢትዮጲያዊ ነኝ ከሚለውም ስህተቶች ተንፀባርቀዋል። ቅን የትግራይንና ኢትዮጲያዊ ኤርትራውያንን የማግለል ጭፍን ዝንባሌ አልፎ አልፎ ሊታይ ይችላል። ማኅበራችንም ይህንን ሳይታክት በማስተማር ለሁሉም በእኩልነት ርዳታ በመስጠት በውጭ ሀገር ሰዎችና በኢትዮጲያውያን አድናቆትን አትርፏል። ሁሉን አቀፍ ሰብዓዊ ድርጅት በመሆኑም ግልጋሎቱን ካለመድልዎ (Affirmative Action and Equal Opportunitiy) አበርክቷል። ኢትዮጲያችንም የበርካታ ብሔረሰቦች እናት እንደሆነች አስመስክሯል። ሌላው ደግሞ ከዚህ በፊት የታየው የራስን ባህል ማንቋሸሽ/መናውቅ፤ የፈረንጅ ባህል/ተቋም የሞራል የበላይነት የተጐናፀፈ ይመስል፣ አውሮፓዊያን ለጥቁር ሕዝቦች የሥልጣኔ መዳሸቅ አስተዋፅዖ እንዳላደረጉ ሁሉ በራስ ታሪክ ባለመኩራት የኮሚኒቲ ማኅበራትን እንደቀበሌ ጽሕፈት ቤት ጣልጣል የሚያደርጉም አልጠፉም። የጁዊሽ ኮሚኒቲ ሴንተር፣ ራሺያን ኮሚኒቲ ሴንተር፣ የላቲን አሜሪካ ሪሶርስ ሴንተር፣ የፖሊሽ ኮሚኒቲ ወዘተ... ሲባል ተአምር የሚመስላቸው የራስን ግን እንደመናኛ ልብስ አውልቀው የጣሉም አልታጡም።





ይህንንም በማጋለጥ በኢትዮጲያን ሪቪው (Ethiopian Review) በነዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ ስለሕዝባችንና ሀገራችን አስተዋፅዖ የወጡት ጽሑፎች ንቃተ-ሕሊናን በማጎልበስ በራሳችን እንድንመካ አድርገዋል። መሪጌታና ቀሲስ እንደዚሁም የአቋቋምና የቅኔ መምህራን ከከፍተኛ ሊቅ (Ph.D.) አንድ ወይም ተመሳሳይ መሆናቸው ለሰፊው አንባቢያን የተገለፁት እነዚህን በመሳሰሉት አኩሪ ጽሑፎች ነው። ስለሆነም ማህበራችን እርስ በርስ ከመረዳዳትና ግልጋሎት ከመስጠት አልፎ አኩሪ ባህላችንንና ታሪካችንን አስተዋውቋል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ የሚሰማ አባባል አለ። ኮሚኒቲ ማህበር ውስጥ መሥራትና ድርጅቱንም ማሳደግ አስቸጋሪ የሆነው ከፍያው ዝቅተኛ በመሆኑና ታክሲ ነጅነት ወይም ሌላ የሙያ ሥራን ትቶ ማደራጀት ሞኝነት ነው የሚሉ አሉ።

በርግጥም ይህ አባባል እውነት ሊመስል ቢችልም በአባላት ትብብር የተቀናጀ የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎች ከታቀዱ፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ዕርዳታ ከተጠየቀ አንዱን ግለሰብ እስከ $100,000 መቅጠር ይቻላል። እንዲሁም የኛ ድርጅት ለትርፍ የማይሠራ ቢሆንም የበለጠ ገንዘብ ባገኘ ቁጥር የሠራተኛ ደሞዝም በዛው መጠን ያድጋል። ይህ ለትርፍ የማይሠራ ልዩ ዓይነት ሥራ (Business) ሆኖ መታየት አለበት። ለምሳሌ በአሜሪካ ትርፍ አልባ ድርጅቶች የብዙ ቢሊዮን ሥራ በየዓመቱ ያካሂዳሉ (Multi-Billion Dollar Business)። ስለዚህ ይህ ዓይነት ሀሳብ የሚያራምዱ ግለሰቦች የምንጠይቀው ሀብታም ትርፍ አልባና ኢፖለቲካዊ ድርጅቶች በአሜሪካ ያደጉት ለምሳሌ አንዳንዶቹ በዓመት እስከ $50 ሚሊዮን ባጀት የሚተዳደሩት ከየት ተነስተው ነው? ከእኛ የተለየ ልዩ ጭንቅላት አላቸውን? አንድ ደግሞ ሌላ የተወጣነው ችግር አለ። የኢትዮጲያውያን መደራጀት እንደ ጦር የሚያስፈራቸው ወገኖች በጉን ያልሆነ የሆነውን በማራገብ የኢትዮጲያውያንን ማኅበር በመቆጣጠር ከመንግሥታት ችሮታ ለማግኘት ለሚቅበዘበዙና ለሚወዳደሩ ድርጅቶችችናግለሰቦች መሣሪያ በመሆንና በመከፋፈል እንደተራ የፖሊስ ሰላይ ለጥቁር ሕዝቦች በሚያሳፍር መንገድ ድርጅታችንን ለመጠናወት ሞክረው ነበር።



ከቦርዱ አባላት በከፊል

እንግዲህ እንደዚህ ባሉ ትንቅንቅ ትግሎች ነው ከተመከሮአችን በመማር ጐልብተን የተደራጀነው። ማኅበራችን እንደገና በዋነኛ ትርፍ አልባና ኢፖለቲካዊ ይዘቱ በመደራጀት አሜሪካ ደጋፊዎችና አባላትን በመጋበዝ እጅግ በደመቀና በተቀዳጀ መልክ በፌብሯሪ 13 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽሕፈት ቤቱን ወይም ማዕከሉን (Center) አስመርቆ ከፍቷል። በበዓሉም ላይ የታወቁ የሕግ ጠባቂዎች፣ የካቶሊክ የስደተኞች አስፋሪ ሥራ አስከያጅ፣ የሴንትሉዊስ ከንቲባ ልዑክ፣ በሴንትሉዊስ የአምስት አብያተ-ክርስትያን ቅንጅት ሥራ አስከያጅ፣ የሕክምና ዶክተሮች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የዚሮክስ ኮርፖሬሽን ተወካይ፣ የንግድ ተቋም ተወካዮች፣ የጂዊሽ ኮሚኒቲ ሪሌሽን ካውንስል (የሕዝብ ግንኙነት) ወኪል፣ ባልቴቶች/ሽማግሌዎችና ሌሎችም በተገኙበት በሚያኮራ መንገድ ተከብሯል። ይህም በሴንትሉዊስ ለምንገኝ ኢትዮጲያዊያን አድናቆትን በማበርከት ኩራትን አጐናፅፎናል። በተጨማሪም በዝግጅቱ የቅርሳቅርስ፣ የታሪክ መጽሐፍት የእጅ ሥራዎች በትርዒት መልክ ለሕዝብ ቀርበዋል። የሚያኮራ የሀገር ባህል ምግብም ነበር። እዚሁ ዝግጅት ላይ $10,000 የሚያወጣ የማባዣ መሣሪያ ላበረከተው የዜሮክስ ኮርፖሬሽን ለሌሎችም ለረዱን ድርጅቶች ተገቢውን ምሥጋና አቅርበናል።

በቅንነት ችግር ሳይበግረን የምንችለውን በማድረግ ወደፊት እንገሰግሳለን። ገና ብዙ ይጠበቅብናል።

እንድነት አሁኑኑ!

የሥደት ኑሮ በማኅበር ትብብር ይታነፅ!

ለግንኙነት:- Ethiopian Community Association of Missouri (ECAM)
3100 Sidney Street St.Louis, Mo 63104
Tel.(314)-776-7464 Fax (314)-776-7464

# « የመንበረ ሱራፌል ፋውንዴሽን »

በሴንት ሉስ ከተማ ነዋሪና በሀሪስ ስቶው እስቴት ኮሌጅ መምህር የነበረውና May 20 1993 ከዚህ ዓለም በሞት በተለየው ወንድማችን መንበረ ማርቆስ ስም የተቋቋሙትን ሁለት የእርዳታ ድርጅቶችን (Foundations) እናስተዋውቃችሁ። በዚህም ለተቋቋሙት ፈንዶች እጃችሁን እንድትዘረጉ እንጠይቃለን።

1ኛ. ለእስኮላርሺፕ ፈንድ (ለተማሪዎች የነፃ ትምህርት ዕድል) መላክ የምትፈልጉ ይህን አድራሻ ተጠቀሙ፤

Menbere Surafel Scholarship Fund
Harris-Stowe State College - 3026 Laclede Ave
St. Louis, MO 63103

2ኛ. ወደ አገር ቤት መጽሐፍት ለመላክ ለተቋቋመው ፈንድ አስተዋጽዖ ማድረግ ለምትፈልጉ ደግሞ ይህን ተጠቀሙ።

Menbere Foundation
c/o Woinishet Surafel
P.O.Box 242279 St. louis MO 63130

ስለዝርዝር ሁኔታውና ስለ መንበረ ሱራፌል ሕይወት ታሪክ የተዘጋጀውን መጽሔት በአድራሻው መጠየቅ ትችላላችሁ። ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲውን ከላይ ባለው ስልክ አነጋግሩ።

# በአትላንታ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ተከታዮች እንቅስቃሴ

ከመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል

አትላንታ ወደ አምስት ሺህ ኢትዮጵያውያን እንደሚኖሩበት ይነገራል። ኢትዮጵያውያን በጋራ የሚሰባሰቡባቸው ብዙ ሁኔታዎች አሉ። በቅርቡ በከፍተኛ ደረጃ እየተጠናከረ ያለው የኮሚኒቲው ማህበር፤ ታዋቂነት ያለው የእግር ኳስ ቡድን፣ በሃይማኖትም በኩል የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ተከታዮች፣ የወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ተከታዮች፣ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን፤ የሕጻናት ትምህርት ቤት በአበይትነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነኚህ ዘርንና ጐሳን ሳይለዩ ችግርን በጋራ ለመወጣትና እምነታቸውን ለመከተል የሚያስችላቸውን ሁኔታዎች ለማስፋፋት በየአቅጣጫው የሚጥሩትን ኢትዮጵያውያን በጋራ የሚያደርጉትን ጥረት በመደገፍ እንቅስቃሴያቸውን በመከታተል ለአንባብያን ለማቅረብ እንሞክራለን።



መንፈሳዊ አባት አባ ገብረ መስቀል

ሰሞኑን በአትላንታ በከፍተኛ ደረጃ ከሚወራላቸው አበይት የኢትዮጵያውያን ተግባራት አንዱ የቅድስት ማርያምን ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቤተ መቅደስ ለመግዛት የሚደረገው ጥረት ነው። ኢትዮጵያውያኖች በብዛት ተሳትፈውበት የታቀደውም ዓላማ ግቡን መምታት የቻለበት ይህ ተግባር በጋራ የሚደረግ ነገር ሁሉ ውጤት የሚያመጣ መሆኑን ስለሚያስረዳ በዛሬው እትማችን ይህንኑ እንቅስቃሴ በተመለከተ የዘገብነውን ለማቅረብ እንሞክራለን። ለዚሁ ታላቅ ተግባር ገንዘብ ማግኛ ከተዘጋጀው በዓል እንጀምር።

ዕለቱ የካቲት ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ነበር። አትላንታ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ተከታይ ምዕመናን ዘንድ የተለየ ዕለት ነበር። አንድ ትልቅ ተስፋ የጣሉበት ምሽት። በአትላንታ ከተማ የምትገኘው የቅድስት ማርያም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን የራሷን ቤተ መቅደስ ኖሯት ጽላቷ በራሷ ቤት በሥርዓት እንዲቀመጥ የማድረግ የተቀደሰ ዓላማቸውን በተግባር ለመተርጐም የሚያስችላቸውን ገንዘብ ለመሰብሰብ ያቀዱበት ዕለት ነበር። ለተቀደሰ ሥራ የሚደረግ ጥረት ሁሌ ቡራኬ አለውና ዕቅዳቸውና ዓላማቸው የለመለመበት ዕለት ነበር። መንፈሳዊ አባት አባ ገብረ መስቀል በቅርቡ ለአትላንታ አገረ ስብከት ሥራ ከመጡ ወዲህ በቤተክርስቲያኒቱ ዙሪያ በብዛት መሰባሰብ የጀመሩትን ምዕመናን ብቻ ሳይሆን በዕለቱ የተገኙትን የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታይ ኢትዮጵያውያንንም ጭምር ትንግርት ያሰኘ ምሽት ነበር። ቦታው አትላንታ ከተማ የሚገኘው የኒኮስ ክለብ ነበር። ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያውያን የምሽት ዝግጅቶች የሚቀርቡበት አዳራሽ ነው። የዝግጅትክፍላችን ጥቂት ዘግየት ብሎ በቦታው ሲደርስ በመጀመሪያ ያጋጠመው ነገር ቢኖር የመኪና



የአትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን መዘምራን



በምሽቱ ከተገኙ ምዕመናን በከፊል

ማቆሚያ ቦታ ማግኘት ችግር ነበር። በዚህ ቦታ ዝግጅት ሲኖር የመኪና ማቆሚያ ችግር ኖሮ አያውቅም ነበር። በዚህ ዕለት ግን በሰዓቱ በነቂስ የወጣው ኢትዮጵያዊ ብዛት የማቆሚያ ቦታውን ይዞት ስለ ነበር ገና ከመግባታችን ጉድ አሰኘን። ወትሮ በሚደረጉ ዝግጅቶች ፕራግራሙ የሚጀመረው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተብሎ በአምስት ሰዓት ይመጣ የነበረው ሕዝብ ዛሬ በሰዓቱ መጥቶ አዳራሹን ግጥም ብሎ ሞልቶ በማየታችን ተገረምን። የቤተክርስቲያኒቱ ቦርድና ለዚሁ ዝግጅት ቅንብር የተቋቋመው ኮሚቴ አባላት ከሌሎች በጐ ፈቃደኞች ጋር በመሆን አዳራሹን ፍጹም ኢትዮጵያዊ አድርገውት ቆዩን። በሰንደቅ ዓላማችን ያሸበረቀው አዳራሽ የተዘጋጀው ምግብ ሽታ ተጨምሮበት ልዩ ትዝታ ጣለብን። እኛም ካሜራችንንና ብዕራችንን ጠመድን።

ፕሮግራሙ በሰዓቱ ተጀመረ። የዕለቱም ፕሮግራም በዋና አስተናባሪው ከተገለጸ በኋላ አባታችን አባ ገብረ መስቀል ቤተ ክርስቲያኒቱን የማሠራት አስፈላጊነትን በተመለከተ አጭር መግለጫ አድርገው ጸሎት ካካሄዱ በኋላ ገበታው ተባርኮ በእህቶቻችን የተዘጋጀው ራት ቀረበ። ጣት የሚያስቆረጥመው ራት እንዳበቃ በአትላንታ የተቋቋመው ኢትዮጵያዊ ሕጻናት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሰንደቅ ዓላማችን ቀለማት ባሸበረቁ ልብሶች ተውበው መድረኩ ላይ ወጥተው መዝሙሮች አሰሙ። በዚህ በባዕድ አገር የተወለዱ እኚህ የዛሬው አበባዎቻችን ተራ በተራ እየወጡ ለአገራቸውና ለወገናቸው ያላቸውን ፍቅር በትምህርት ቤቱ በቀሰሙት የአማርኛ ቋንቋ ሲያሰሙ ሕዝቡ ጉድ አለ። የሕጻናቱ ግብረገብ የወገን ፍቅርና ተሳትፎ በዓሉን ልዩ ድምቀት ሰጠው።




ሕጻናትም መዝሙር አሰምተዋል

ከዚያም የቤተክርስቲያኒቱ መዘምራን ባማረና ባሸበረቀ ልብሳቸው ተውበው መድረኩን ይዘው ጣዕም ባለው ድምጻቸው መዝሙሮች አሰሙ። ከዳላስ የመጣችው ዘፋኝ ሒሩት ግርማና ባንዷ ሕዝቡን በማዝናናት ምሽቱን ልዩ ድምቀት ሰጥተውት ነበር። ለበዓሉ የተገኙት ኢትዮጵያውያን እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድርስ በመቆየት ለዝግጅቱና በተለይ ለዓላማው ያላቸውን አድናቆትና ድጋፍ ገልጸዋል። በዚህ ዝግጅት ላይ ወደ አምሳ ሺህ ብር ያህል ሊሰበሰብ መቻሉን ለማወቅ ተችሏል።

"በተለያዩ ምክንያቶች ከውድ አገሩ ተሰዶ በውጪ ለሚኖረው ወገናችን የዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ጽናት እንዳለው ስመለከት እኮራለሁ፣ በተጨማሪም ተስፋዬ ይለመልማል፤ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ እንዲገባን አድርገው ከዕለት ዕለት ኑሮአችንና የመረዳት ችሎታችን ጋር በማዋሃድ የሚያስተምሩ መንፈሳዊ አባት (አባ ገብረ መስቀልን) ማግኘታችን ዕድለኞች ነን። መንፋሳዊ ሕይወታችንን አድሰን፣ በፈጣሪ ቤት የሚያሰባስበንን ጥሩ አጋጣሚ ስናገኝ የማንጠቀምበት ከሆነ ሞኞች ያሰኘናል። ስለዚህም በዚህ በዓል ላይ መገኘቴ በጣም አስደስቶኛል። ለበለጠ መሰባሰብ የሚረዳን የቅድስት ቤተክርስቲያናችንን ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ለማዋጣት በመታደሌ ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ።" አሉን በበዓሉ ላይ ለተገኙ አንድ ኢትዮጵያዊ "ምን ይሰማዎታል?" ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ። ይህ በአብዛኛው ያነጋገርናቸውን ኢትዮጵያውያንን አባባል የሚወክል ነው።

የመንፈሳዊ ሕይወትን ጥማት ለማርካት በእግዚአብሔር ቤት የመሰባሰብ ፍላጐት በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዳለ ለመረዳት የቻልንበት ሁኔታ ነበር። ከዚህ ምሽት በፊትም ሆነ በኋላ ዘወትር እሁድ በሚደረገው የቅዳሴና የጸሎት ሥነ ሥርዓት ላይ በተከታታይ በመገኘት ያየነው የእግዚአብሔርን ቃል የመስማትና ከእግዚአብሔር በረከትን ለመቀበል የመፈለግ ከፍተኛ ስሜት እንዳለ ነው። በቤተ ክርስቲያኑ የሚከናወነው ሥርዓት ሁሉ መንፈሳዊ የሆነ፣ ሕዝብን በፍቅርና በሰላም የማገናኘት የማሰባሰብ ሁኔታ እንደሆነ ለማወቅ ችለናል። ■




# ጓደኛ ለሚፈልጉ

ጓደኛ ፈላጊዎች ራሳቸውን አስተዋውቀው፣ ሊተዋወቁ የሚፈልጉትን ሰው ዓይነት የሚጠቁሙበት አምድ ነው። ስምና ትክክለኛ አድራሻ በመጽሔቱ ላይ አይወጣም። በስምና አድራሻ ፋንታ የኮድ ቁጥር ይወጣል። የኮዱን ቁጥር የምንሰጠው እኛ ነን። በስምና አድራሻ ምትክ የኮዱ ቁጥር ይወጣል። ስምና አድራሻ እኛ ጋ በምስጢር ይቆያል። ትክክለኛ ስምና አድራሻ ግን እኛ ጋ መድረስ አለበት።በጣም አጠር ተደርጐ ቢጻፍ ዕድሉን ለብዙ ሰው ማዳረስ ይቻላል።

ለመተዋወቅ የምትፈልጉት ሰው ዓይነት ወጥቶ ካገኛችሁ ቁጥሩን በመጥቀስ ደብዳቤ ጽፋችሁለት/ጽፋችሁላት እንስ ያለ ኤንቨሎፕ ውስጥ አሽጋችሁ ኤንቨሎፑ ላይ የናንተን ሙሉ አድራሻ በቀለም፣ የሚላክለትን/የሚላክላትን ሰው ኮድ ቁጥር በእርሳስ ጥጉ ላይ ጽፋችሁ በሌላ ከፍ ባለ ኤንቨሎፕ ውስጥ ከታችሁ አሽጋችሁ በአድራሻችን ትልካላችሁ። እኛም የናንን ፖስታ በመክፈት ከውስጥ ያለውን ኤንቨሎፕ አውተተን የኮድ ቁጥር የተጠቀሰውን ግለሰብ ትክክለኛ አድራሻ ከመዝገባችን ኤንቬሎፑ ላይ በመሙላት እንልካለን። ከዚያ በኋላ እንደፍተርተራችሁ።

የሚከተሉትን መመሪያዎች በደምብ አጢኑ።

1ኛ. ለፖስታና ለአገልግሎት አከፋፈሉ በሚቀጥለው ዓይነት ይሆናል፣
 ከአሜሪካ - $5.00 (በmoney order)
 ከካናዳና አውሮፓ - $6.00 (በአሜሪካ ገንዘብ፣ money order)
 ከኢትዮጵያ - ምንም አይከፈልም።
 ለላንዳፍታ ቋሚ ደምበኞች (subscribers)
 (ላንዳፍታ ማዘዣ ቅጽ ሞልታችሁ ከፍያ የላካችሁ) $4.00 ብቻ ነው።
2ኛ. ዕድሜአቸው ከ18 በታች ለሆኑ ይህ አገልግሎት አይሰጥም።
3ኛ. ይህ አምድ ዓላማው መተዋወቂያ መድረክ ለመፍጠር ብቻ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።
4ኛ. እባካችሁ እንዲጻፍላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አሳጥሩት።
5ኛ. በመጀመሪያ የብዕር ጓደኝነትን በማጠንከር የበለጠ መተዋወቅን እንመክራለን።

አዲሱ አድራሻችን፣

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

## ጓደኛ የሚፈልጉ ሴቶች

ስም 1061፣ ዕድሜ 29፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ የትምህርት ደረጃ 12+2፣ ኦርቶዶክስ ክርስትያን፣ ሂሳብ ሰራተኛ፣ አላገባሁም፣ ልጅ የለኝም። መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፣- ኢትዮጵያዊ ሆኖ በዜግነቱ የሚያምን፣ ያላገባ ልጅ የሌለው፣ በትዳር የሚያምን፣ ሚስቱን የሚወድ ታማኝ፣ቢቻል መልከመልካም ቆንጆ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

ስም 1062፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ የምህንድስና ሙያ ያለኝ፣ አሁን በከፍተኛ ደረጃ በመማር ላይ ያለሁ፣ ላለሁበት ኑሮ በቂ ደመወዝ ያለኝ፣ ሙዚቃና መጽሐፍትን ተፈጥሮን (አበባ) እወዳለሁ።መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፣ በማንኛውም መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፣ ሃይማኖት አድቬንቲስት፣ በንግግር የመግባባትና የመስማማት ችሎታ ያለው፣ ገልጽ (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

ስም 1063፣ ዕድሜ 22፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ ኮምፒውተር ፕሮግራመር (ዲፕሎማ)፣ሙዚቃ (country song)፣ ማንበብ፣ ግራውንድ ቴኒስ እወዳለሁ።. መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፣ ዕድሜው ከ20-30፣ ከኢትዮጵያ ውጪ የሚኖር (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

ስም 1064፣ ዕድሜ 22፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ 12ኛ ክፍል ጨርሻለሁ፣ አላገባሁም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ እወዳለሁ፣ መተዋወቅ የምፈልገው ወንድ፣ የማይጠጣ፣ የማያጨስ ከማንኛውም ሱስ ነገር ነፃ የሆነ፣ዕድሜው ከ26-32 (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

ስም 1065፣ ዕድሜ 31፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት እሠራለሁ። አገሩና የአገሩ ልጅ የናፈቀው ጓደኛ ባገኝ ደስ ይለኛል።(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

ስም 1066፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ የቦሌ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ተማሪ ነኝ፣ ረጅምም አጭርም አይደለሁም፣ የደስ ደስ አለኝ፣ ቆንጆ ባልባልም ጥሩ ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ስለውጭ አገር የኑሮ ሁኔታ ማወቅ ስለምፈልግ ከኔ ጋር ለመጻጻፍ የሚፈልግ በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰህ ጻፍልኝ።)

## ጓደኛ የሚፈልጉ ወንዶች

ስም 1067፣ ዕድሜ 39፣ መኖርያ አዲስ አበባ፣ አየር መንገድ እሠራለሁ፣ጥሩ ደመወዝና የራሴ መኖሪያ ቤት አለኝ፣ ቁመቴ መካከለኛ የቀይ ዳማ ነኝ። መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት፣ በትዳር ሙሉ እምነት ያላት፣ ሥራ ወዳድ፣ ሙሉ የኢትዮጵያዊ ስሜት ያላት (ኤርትራዊ አልፈልግም)፣ ለችግርና ለማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ተስፋ የማትቆርጥ፣ መልከመልካም ዕድሜ እስከ 35፣ በኢትዮጵያም ሆነ በውጪ ልትረዳኝ የምትችል (በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

ስም 1068፣ ዕድሜ 34፣ መኖርያ ዩናይትድ ስቴትስ፣ትምህርት 2ኛ ዓመት ኮሌጅ፣ በሥራ ዓለም ያለሁ፣ ተወልጄ ያደግሁት አዲስ አበባ፣ መተዋወቅ የምፈልጋት ሴት፣ እንግሊዝኛ ማንበብና መጻፍ የምትሞክር ልጃገረድ የሆነች፣ ጠባይዋ ጥሩ ከሆነ አስቀያሚ ብትሆንም ግዴለኝም፣ አገሯን የምትወድ፣ ዕድሜዋ ከ23 በላይ የሆነ፣(በላንዳፍታ አድራሻ በኩል ቁጥረን ጠቅሰሽ ጻፊልኝ።)

አዳም

አዳም

# « አላለልኝ ይሆን!»

ከትዝታ አለብኝ (L.A.)

(ካለፈው የቀጠለ)

እቤቴ ይዤው ገባሁ። ዕቃውን ተሸክሞ ከኋላ ኋላዬ ተከተለኝ። በሁኔታዬ ምንቅር ምንቅር ማለቴ ይስማኝ እንጂ ይህንን ለማረም ያደረግሁት ነገር አልነበረም። ጠልቼውም ነው አልልም። በስልክ ይሁን እንጂ ብዙ አውርተናል። ስለኔ ሁሉን ነግሬዋለሁ። ስለሱም ብዙ አውርተናል። እንደዚያ ያነጋገርኩት፣ እንደዚያ የተጫዋወትነው እንደዚያ ብዙ ዕቅድ ያውጣሁለት ሰው አልመሰልህ አለኝ። ይሄ Moody መሆን ይሆን ወይስ ይቺ የድሮ ኩሩ ልቤ የምትፈልገው ረዘም፣ ሞላ፣ ቀላ ያለ ቆንጆ ጉረምሳ ስላልሆነ ይሆን? እኔ እንጃ ብቻ፤ የውስጣዊ መቅበጥበጤ ነፀብራቅ በውጪው ገጽታዬ መታየትም የጀመረ መሰለኝ። እቤት ውስጥ እንደገባን ቦርሳዬን ከወንበሩ ላይ አስቀምጬ ወደ ሽንት ቤት ገባሁ። "ዕቃህን እዚያ" አኑር፣ ቁጭ በል!" ቆይ መጣሁ" ማለት ያባት ነው። በሩን ከፍቼለት ብቻ እሱ መግባቱን ካረጋገጥኩ በኋላ ሽንት ቤት ገባሁ። ፊቴን ቀዝቃዛ ውሃ በእጄ ሞልቼ ካሻሸሁት በኋላ ቀና ብዬ መልኬን በመስታወት አየሁት። ዓይኔ ደፍርሷል። መልኬም አመድ መስሏል። ፊቴ ላይ የወጣችውን ማዲያት በእጄ ነካ አደረግሁት። "አሮጊት እመስለው ይሆን?" አለኝ ድንገት መንፈሴ። ለጥቂት ጊዜ መልኬን በመስታወት ሳየው ያ ጥንት የነበረኝ ውበት እየተሟጠጠ በደም ሥሮቼ የሚሯሯጠው ደም ፍጥነቱ እየቀነሰ የመጣም ዓይነት መሰለኝ። ትንሽ ብስጭት፣ ኩርፍ አልኩና ደግሞ ተጽናናሁ። ያቺ ስንቱን ስትጥል የነበረችው ፈገግታዬ ግን ያው ናት፣ መሰለኝ፤ ፈገግ አልኩና ተጽናንቼ ፊቴን ጠራርጌ ወደ ሳሎን ቤት ስገባ ዕቃውን እበሩ አካባቢ እንዳስቀመጠ ቅርቡ በነበረ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ጣራ ጣራውን ሲያይ አገኘሁት። ሀሳብ እንደገባው ያስታውቃል። "ምን ሆነሽ ነው?" ብሎ ቢጠይቀኝ እኔም መልሱን የማላውቀው መሆኔን እንዴት እንደምነግረው አላውቅም። ደግነቱ አልጠየቀኝም። ሻንጣውን ራሴ አንስቼ ሳሎን አጠገብ ካለው ክሎዜት ከተትኩና "እዚህ አይሻልህም?" አልኩትና ሶፋው ላይ እንዲቀመጥ ጋበዝኩት። የመጀመሪያው ግብዣዬ መሆኑ ነው መሰለኝ። ተነስቶ መጣና ቁጭ አለ።

"ቆንጆ ቤት አለሽ?" አለኝ። "አመሰግናለሁ" አልኩት። በሆዴ "ቆንጆ ሆነ አልሆነ ምን አባክ አገባህ?" አለ ደካማው መንፈሴ። ሰሞኑን የሱን መምጣት ምክንያት በማድረግ ስንት ነገር እንደለዋወጥኩ፣ ስንት የሚያማምሩ ነገሮች እንደገዛሁና ቤቴን እንዳጌጥኩ አላወቀም። ዝምታዬ መብዛቱ፤ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ቁርጥ ያሉ አጭር መልስ መስጠቴ የበለጠ የተሰማው መሰለኝ። አንዴ መኝታ ቤት፣ አንዴ ወጥ ቤት፣ አንዴ እዚህ አንዴ እዚያ እየተቁነጠነጥኩ ስመላለስ ሳይገርመው አልቀረም።

ቴሌቪዥኑን ከፈትኩና ቁጭ አልኩ። ከጥቂት የዝምታ ጊዜ በኋላ ያላሰብኩትን ነገር ተናገረ።

"እንዴት ነው፤ Relaxed የሆንሽ አትመስይም። Is there any problem? አለኝ በእንግሊዘኛ። የምለው ጠፋኝ።

"ምነው እንደዚህ አልህ?" አልኩት ምንም እንዳልተፈጠረ በማስመሰል፤

"አይ ዝምታ በዛ፣ ትንሽ የተጨነቅሽ መሰለኝ፤"

"አይ አልተጨነቅሁም፤ ይልቅስ ራት እንብላ " አልኩና ራት ለማዘጋጀት ብድግ አልኩ። እርዕስቱ እንዳይቀጥል ፈልጌ ነበር ይህን ሀሳብ ያቀረብኩት። "እባክሽ ውሃ በበረዶ ትሰጪኛለሽ?" አለ ብድግ ስል። ደነገጥኩ፤ አፈርኩ፤ እቤቴ እንግዳ ሆኖ መጥቶ ምንም ነገር ልጋብዝህ አላልኩትም። መቼም ምንም አሜሪካ ለዘመናት ብኖር የእንግዳ ተቀባይነት ኢትዮጲያዊ ባህሌ የጠፋብኝ አይመስለኝም፤

"እሺ" አልኩና ውሃ በብርጭቆ ቀድጄ አምጥቼ ሰጠሁት። ሌላ ነገር ይፈልግ እንደሆነ ግን አልጠየቅሁትም።

"አመሰግናለሁ" አለኝና ተቀበለኝ።

ራት ለማዘጋጀት ወደ ወጥ ቤት ስገባ የሃሳብ መዓት አዕምሮዬን ሞላው። "ምን ማድረጌ ነው?" አልኩ በሆዴ፤ ተጨንቄ የሰው ሰው የማስጨንቀው።" ቢሆን ይሆናል፣ ባይሆን አይሆንም፣ ምንድነው እንዲህ የሚያደርገኝ፤ ደግሞ ና ብዬ ነው የመጣው። ታዲያ ከመጣ በኋላ ምን መጣብኝ፤ እይ ፈጣሪዬ ምን አደረግሁ፣ ምነው መንፈሴን ብትሰበስብበው፤ በርግጥ ምን እንደሆንኩ ለራሴ እንኳ አላውቀውም። ሰውዬውን ቁመናውን አይቼ ጠልቼ ነው እንዳልል ይህ የመቅበጥበጥ ስሜቴ የጀመረኝ ልቀበለው ወደ አውሮፕላን ማረፍያ እየሄድኩ እያለሁ ነው። ገና ሳላገኘው ነው የጀመረኝ። ደግሞ በላከልኝ ፎቶግራፍ ብዙ አይቼዋለሁ። ከስልክ ውጭ ባለው አነጋገሩ ነው እንዳልልም ገና ሳንገናኝና ማውራት ሳልጀምር ነው የጀመረኝ። ምግቡን እያሞቅሁ አዕምሮዬ በየአቅጣጫው ተበታትኖ ለምን እንዲህ እንደሚያደርገኝ ያስብ ጀመር። እሱን ለመቀበል ያላዘጋጀሁት ነገር የለም። ምግብ፣ መጠጥ እዚህ በመቆያው ሦስት ቀን ምንም እንዳያስፈልገው ነበር ተዘጋጅቼ የጠበቅሁት። እንደዚሁ መንፈሴ እንደተበታተነ ምግቡን እያቀረብኩ ወደ ራት ገበታ

ጋበዝኩት። ከፊት ለፊቴ ቁጭ አለ። ጠረጴዛው መሀል ላይ ያዘጋጀሁትን ሻማ አየና ፈገግ አለ። የሲጋራ መለኮሻውን አውጥቶ አበራውና ፈገግ አለ። "አልጠየቅሁት፣ ምን አገባው" አለ ከውስጥ ደካማው መንፈሴ። እንደገና ሰይጣን መምጣት ሊጀምር ሲል ብድግ ብዬ ወደ ወጥ ቤት ገባሁ። እንደ ሰበብ እንዲሆን ያዘጋጀሁትን ጥሩ ወይን ጠጅ ይዤ መጣሁ። ጠረጴዛ ላይ ቁጭ አደረግሁ። ዝም ማለቴን አይቶ "መክፈቻ ሳምጣ" አለ። ገረመኝ "የማነው ደፋር" አለኝ ደካማው ጐኔ አሁን ደግሞ።

"ቆይ እኔ አመጣለሁ " አልኩና ሄጄ አመጣሁ። የቪኖ መክፈቻውን ተቀበለኝና ከፈተው። በተዘጋጁት ብርጭቆዎች ውስጥ ቀዳውና አንስቶ "ለጤናችን" አለ። "ለጤናችን" አልኩና ምንቅር አልኩ። "እንኳን ደህና መጣህ" ማለትም እንደነበረብኝ ኋላ ነው ትዝ ያለኝ። ራቱን እንደነገሩ ነበር የበላነው ሁለታችንም።

"በጣም ጣፋጭ ምግብ ነው የሰራሽው" አለኝ።

"አመሰግናለሁ" አልኩትና የወይን ጠጁን በሙሉ ጉንጩ ሞልቼ ጠጣሁት። ምናልባት መጠጡ መንፈሴን ያሰባስበው እንደሆን ብዬ። እጅሬ የኔ መቅበጥበጥ ያስጨነቀው ቢሆንም፣ መጨነቁን በሥርዓት የተቆጣጠረው መሰለኝ። አንዱን ብርጭቆ ወይን ጠጅ ጨርሼ ሌላ ቀዳሁ። በስልክ ስናወራ መጠጥ እንደማልወድ ነግሬው ነበር። አሁን ግን እሱ ገና የያዘውን አንድ ብርጭቆ ሳያጋምስ እኔ ሁለተኛውን ስደግም ምን ብሎ ይሆን? ብዬ አሰብኩ። "የፈለገውን ይበላ፣ ማነውሱና ነው?"

"ቆንጆ ቤት ነው ያለሽ ደግሞ አያያዝሽ Artistic ነው " አለ እንደገና ቀና ዘወር ብሎ አንዴ ጣራውን፣ አንዴ ግድግዳውን እያየ።

"Thank you" አልኩት። እንደበፊቱ መጥፎ መንፈሴ አልረበሸኝም። በፀጋ ተቀበልኩት ሙገሳውን። ብርጭቆዬን በሁለት እጆቼ እያሻሸሁ ትንሽ ፈገግ ማለቴ ተሰማኝ።

"ከተማችሁ ምንም ያየሁት ትንሽ ቢሆንም ደስ የሚል ይመስላል" አለኝ።

"አዎ ጥሩ ከተማ ነው።" ወይን ጠጄን ተጐነጨሁ። እሱም ተጐነጨ።

"ለምን ቲቪውን አትዘጊውም፣ የሚያየው የለም። ይልቅስ ሙዚቃ ብታደርጊልን አይሻልም።" አለና ከጠርሙሱ ወይን ጠጁ ለራሱ ቀዳና ለኔም ብርጭቆዬን ሞላው። ሥነሥርዓቱ፣ ሰውን ቀዝቀዝ የማድረጉ፣ ረጋ የማለቱ ሁኔታ ደስ ያሰኛል። ብድግ ብዬ ዘፈን ለማድረግ ወደ ቴፑ ሄድኩ። የሚፈልገውን ዘፈን አልጠየቅሁትም። በስልክ ጨዋታችን የሚወደውን የነገረኝ መሰለኝ። የጥላሁንን ዘፈኖች ይወዳል። ቴፑ ውስጥ አለ። ሰሞኑን ስሰማው ነበር። እሱን ከፈትኩና ተመልሼ ጭ አልኩ። ብርጭቆዬን አንስቼ ተጐነጨሁ። "ቡና ትፈልጋለህ" አልኩት። "Please," አለ። ሥነስርዓቱ ማስመሰል እንዳልሆነ ያስታውቃል። "ለምን እኔ አልጥደውም፣" አለ ብድግ ብሎ።

"እሺ ደስ ካለህ" አልኩትና ተከትዬው ወጥ ቤት ገባሁ።

የቡና ዕቃውን አሳየሁትና ተመልሼ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ አልኩ። ወይን ጠጄን በደንብ ተጐነጨሁ። መጠጡም ይሁን ሌላ አላውቅም ብቻ መንፈሴ ደስ ደስ ይለው ጀመር። ሲያቅበጠብጠኝ የነበረው ሁኔታ ቀስ በቀስ እየደበዘዘ ሄደ። ቡናውን ጥዶ ሲመለስ "ለምን ኮትህን አታወልቀውም?" አልኩትና ተነስቼ ወደሶፋው ሄጄ "እዚህ ይሻለናል አልኩት።" ኮቱን አወለቀና ወንበሩ ላይ ሰቅሎ የወይን ጠጅ ብርጭቆውን ይዞ መጣና ቁጭ አለ፣ ፊት ለፊቴ ካለው መቀመጫ ላይ። ጐኔ የሚቀመጥ መስሎኝ ነበር። መቼም እሱ እንግዳ ስለሆነ ጫወታውን እኔ መጀመር እንዳለብኝ ብረዳም በምን እንደምጀምር ግራ ገባኝ። "እዚህ ያለሽበት ሰፈር ሌሎች አበሾች አሉ?" አለና ፀጥታውን አጠፋው።

"በጣም ቅርብ ባይሆንም ወዲያ ማዶ ካለው ሕንፃ ላይ ብዙ አበሾች ይኖራሉ።" አልኩት እና በዚህ በሰው አገር ተበትኖ ስለቀረው ኢትዮጲያዊ፣ ስለኑሮው፣ ስለባህሪው የደራ ጨዋታ ጀመርን። እኔም የወይን ጠጄን ስደጋግም ጊዜ ጥላ ሰይጣኑ ለቀቀኝና መዝናናት ጀመርኩ። ከዚያም ስላለው "ምነው ራቅ ብለህ ቁጭ አልክ" አልኩት። ይታዘበኝ ይሆን፣ በአንድ የመጀመሪያ ቀን ምን ፈለገች ብሎ ይታዘበኝ ማለት ያባት። ምናደከማችሁ ብቻ ጐኔን በረደውና ጋበዝኩት። ከጐኔ ቁጭ አለና ጠጋ ሲለኝ የሰውነቱ ግለት ተሰማኝ። እሱም እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጐ ዓይኔን ትክ ብሎ ሲያይና ጠጋ ሲለኝ እኔም ጠጋ ብዬለት መሐል መንገድ ላይ በከንፈራችን ተገናኘን። ተሳሳምን። ከዚያ በኋላ የሆነውን መቼም ታውቁታላችሁ።

ረፈድፈድ ብሎ በነጋታው ስነሳ ከአልጋዬ ላይ ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዶት ፊቱን ወደኔ አዙሮ ተኝቶ አገኘሁት። ቀና ስል ለካ ሰውነቴ ድቅቅ ብሎ ኖሮ መነሳት አቃተኝ። ራሴን ይፈልጠኝ ጀመር። መለስ ብዬ አየሁት። ከዚያም እንደምንም ተነሳሁና ወደ ሽንት ቤት ሄድኩ ገላዬን እየታጠብኩ የሆነውን ሁሉ ማስታወስ ጀመርኩ። ያልሆነ ያልሆነ ነገር አዕምሮዬ ውስጥ መመላለስ ጀመረ። "እንዴት በተገናኘን በመጀመሪያ ቀን አልጋዬ ላይ ወጣ?" እንዴት ቢገምተኝ ነው? ነገር ነገር ይለኝ ጀመር። ታጥቤ ወደ መኝታ ክፍሉ ስገባ ተነስቶ አልጋው ዳር ቁጭ ብሎ አገኘሁት። ሳየው ንዳድ አለኝ። ቀና ብሎ በፈገግታ አየኝ። በንዴት ምንቅር አልኩበትና "እንዴት እንዲህ ይሆናል?" ብዬ ከመኝታ ቤት ወጥቼ ወደ ወጥ ቤቱ ሄድኩ። የቡና ጀበና ጥጄ የሚበላ ነገር ማዘገጃጀት ጀመርኩ። አዕምሮዬ እንደገና መረበሽ ጀመረ። በሆዴ እረግመው ጀመር። እልህ ውስጥ የገባሁም መሰለኝ።

"እንዴት ቢደፍረኝ ነው?" "እንዴት እኔ ልጅት በአንድ ቀን ተሸንፌ፤ ያውም ለዚህ ዓይነቱ፣ "ለአፍታ ያ የጥንቱ ሁኔታዬ ኩራቴ በዓይነ ሕሊናዬ ውልብ አለብኝ። በስንት ልመና፣ ስንቱን ሸበላ ደጅ የማስጠናዋ ጉብል እንዲህ ለማኝ ሆንኩ

ማለት ነው?" እልሂን የማነሳቸውን ዕቃዎች በማንኳኳት ሳስቀምጠው ወርወር በማድረግ ተወጣሁት ልበል። በዚህ ላይ ማታ የጠጣሁት የወይን ጠጅ የዞረ ድምር (Hangover) ራሴን ይፈላልጠዋል።

እልህና ቁጭት በሌላ በኩል ያተረማምሰኛል። ማታ የሆነውን ሁኔታ እንዲፈጽም የገፋፋሁት እኔ መሆኔን ብረዳም ያንን መቀበል አልፈለግሁም።

ከመጠጡ በኋላ ያደረግነው ነገር ሁሉ በወቅቱ በጣም ደስ እንዳሰኘኝ ባውቅም አሁን ግን ልቀበለው አልሻም። በወቅቱ ከሱ የምፈልገውን አገኘሁ። እንድፈልግም ያደረገኝ ሁኔታ ነበር። so what? ከዚያ በኋላ ግን አሁን ላየው አልሻም። የበዓሉ ግርማን የቀይ ኮኮብ ጥሪ ገጸ ባህሪ "ሂሩት"ን ሆንኩ ማለት ይሆን? የንብ ንግስት? የተገናኛት ወንድ ሁሉ መጥፋት አለበት?" "ኖ! ኖ! እንደዚያ ባልሆነ። ገላውን ተጣጥቦ ልብሱን ለባብሶ እኔ ቁርስ አዘጋጅቼ እጠብቀው ከነበረው ጠረጴዛ ላይ መጥቶ ተቀመጠ። ጠጋ አለኝና ጉንጬን ሊስም ሲሞክር "እረፍ" ብዬ ተቆጥቼ ተነሳሁ።

በፊቱ ላይ ያየሁት ድንጋጤ እስካሁን ዓይኔ ላይ አለ። ቁጭ አለ።

"ምነው?" አለ።

"በል ቡናህን አርፈህ ጠጣ።" አልኩት።

"እንዴ ምን ተፈጠረ?" አለኝ።

"ያደረግሽውን ታውቀዋለህ፤" አልኩና ብድግ።

ቡናውን ቀዳና ዝም አለ። ነገር ከረር ሲል ቀዝቀዝ ብሎ የመቀበል ችሎታው ይገርመኛል። ቡናውን ቀድቶ የቡና ሲኒውን እያማሰለ አንዴ እኔን፣ አንዴ ሲኒውን ያይ ገባ።

"ሳታውቂው ያደረግሁት ነገር ያለ አይመስለኝም?" አለ ለስለስ ባለ አነጋገር።

"ወንዶች ስትባሉ ይኸው ናችሁ?"

"እኔኑ እዚሁ ነጥለሽ የምትይውን ብትይ አይሻልም፤ወንዶቹን ሁሉ አልወክልም። ምን አጠፋሁ በሞቴ ንገሪኝ?" አለ ሰሜን እያቆላመጠ።

"You took advantage of me" አልኩት። በያ ሰሞን ካየሁዋት ፊልም ያገኘሁዋት አባባል።

"advantage!" አለ በመገረም?

ዓይኑን ያፈጠጠ መሰለኝ። "ምናባቱ ያፈጥብኛል። በ rape ፍርድ ቤት ልገትረው አልችልምና ነው? ሰሞኑን ደግሞ የsexual harrasment ጉዳይ መነሳቱን ረሳው?

"እዎ! ማታ ሞቅ እንዳለኝ አይተህ አይደል? አልኩት ፊቱ ሲለዋወጥ እየሁት።

በጣም እንደተናደደ ተሰማኝ። ታጋሽ ቢሆንም እዚህ ላይ ንዴቱን መቆጣጠር አለመቻሉ አየሁት። እንገቱን ደፋ አድርጎ ቁና ተነፈሰና " እንደውነቱ ከሆነ እኔ ፈልጌ አደረግሁት አላልም። You pushed me ከፈልግሽ፤ እኔ ልንግርሽና፤ I wasn't ready" አይለኝም መሰላችሁ።ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ። ወይኔ ልጅት ለዚህ በቃሁ? እኔው ሆንኩ ለማኝዋ፤ "You pushed me!!!"

የሚለው ቃል በጆሮዬ ይደውልብኝ ጀመር። ያች አላረጅ ያለችው ኩራቴና ትዕቢቴ በውስጤ እየጋየች ደሜን አፈላችው። ብድግ አልኩ በቁጣ፤ "You pushed me?" አልኩ።

"አዎ፣ ምን ልትይ ነው፣ ደግሞ ረጋ በይ፣ ቁጭ ብለን በርጋታ መነጋገር የምንችል መሰለኝ።""ብቀመጥ ባልቀመጥ የሚያገባህ የለም።"

"Ok! I am sorry አነጋገሬ እንደሁ ያናደደሽ፣" አለኝ።

"ቢገባህ እኔ እንዲህ በአንዴ የምገኝ ተራ አልምሰልህ" አልኩት። ይህን ያልኩት ምን ለማለት ፈልጌ እንደሆነ አላውቅም።

"እስቲ አሁን መመፃደቁ አርፎ ይቀመጥና Reality ይዘን እንነጋገር"

"የምናገረው የለኝም ደግሞ የምን መመፃደቅ?"

"ስሚ በመጀመሪያ ነገር እንግዳ ብለሽ ስትጋብዥኝ ለኔ ብለሽ ያዘጋጀሽውን የመኝታ ቤት አሳይኝ?

"የምን መኝታ?"

"ማለቴ ያው አንቺ አልጋ ላይ እንደምተኛ አውቀሽ አይደል። You were ready for it."

"Ready for what?" ደሜ ፈልቶ በውስጤ ሲሯሯጥ ተሰማኝ። ዓይኔን አፈጠጥኩበት።

"በጽሞና ለመነጋገር የምትችይ ዓይነት ሆነሽ ነበር የተዋወቅነው፤"

"I don't care what you feel?"

"ይቅርታ አድርጊልኝ እንግዲህ፤ I hope እኔም ቢሆን ለሚኖረኝ ትዕግስት ወሰን ያለው መሰለኝ።"

"ምን ልታደርግ? አገሩ የሕግ አገር ነው!"

"አውቃለሁ!" አለና ብድግ ብሎ ሄዶ ስልኩን አነሳ። የማስታወሻ ደብተሩን ከቦርሳው አውጥቶ ስልክ ደወለ። በዛሬው ዕለት በቅርቡ እሱ ወደ መጣበት ከተማ የሚሄድ አይሮፕላን ጠየቀ። ጥቂት አውርቶ 3:00 p m ሲል ብቻ ሰማሁት ሰዓቱን አየ። እኔም ቀና ብዬ ላይ ሰዓቱ 11:00 am ነው። ዝም አልኩት። እሱም ዝም አለ። ትንሽ ቆይቶ ተነሳና መኝታ ቤት ገብቶ ልብሶቹንና ሻንጣውን ይዞ " I hope አንድ ሶስት ሰዓት በቤትሽ ብቆይ የምትፈቅጂ መሰለኝ፤" አለኝ።

መልስ አልሰጠሁትም። ትንሽ ግን ድንግጥ አልኩ። ስልኩን አነሳና፤ 411 የታክሲ ኩባንያ ጠየቀ። ቁጥሩን ጻፈና ታክሲ ለመደወል ሲል "እኔ አደርስሃለሁ" አልኩት።

"Thank you ግዴለም" አለና መደወሉን ቀጠለ። ብድግ ብዬ ሄጄ ስልኩን ዘጋሁበት። ቀና ብሎ አየኝ።

"ምነው?" አለኝ።

"Please, don't do that?" አለኝ።

"Do what?" አልኩት።

"ሂድ ማለቴ እኮ አይደለም" አልኩት። በጀ የገባውን ወርቅ ላጣ?. . ወይስ ለምን?

(. . . በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል) ■

# ዕጣዬ

(ከአብረኽት)
. . . ከአለፈው የቀጠለ

## ክፍል ሶስት

የፔሌ ቡና ቤት ኑሮዬ ያከተመ መሰለኝ ብያችሁዋለሁ። የሰይፉ መምጣት ልቤን አጥፍቶት ነው እንጂ የሰው ገንዘብ ወስጄ ለመጥፋት ያላደረግሁት መሆኔን እወቁልኝ። ለሥራ ጓደኞቼ "ፍቅር ነው" ብላቸው "ደግሞ የቡና ቤት ፍቅር" ከማለት በቀር የሚሉኝ ሌላ ነገር ስለሌለ ዝም ማለትን መረጥኩ። እኔ ባደረግሁት ነገር በጅምላ "የፔሌ ቡና ቤት ሴቶች ገንዘብ ወስደው ይሸውዳሉ" መባላቸው ስለማይቀር ይሆናል "ዓይንሽ ላፈር" ያሉኝ። የነሱ እንኳ አላሳሰበኝም። የቡና ቤቷ ባለቤት ከሰማች፣ መቼም መስማቷ አይቀርም፣ ያ ነበር ያሰጋኝ። የት እገባለሁ ካባረረችኝ። ደመወዝ ከፍላ ባታሰራኝም እዚያ ውስጥ ባስተናጋጅነት መስራቴ ነው ጥቅም የሚሰጠኝ። እና በዚህ ፈርቼ ሳለሁ እሷም ሰማችና ያላሰብኩት ሁኔታ ሆነ። "ደግ አደረገች፣ ይህ እኮ ቡና ቤት ነው፣ እንደዚያ ቀልጣፋ ሆና ካላምታታች እንዴት ልትሆን ነው? ጉሽ!" አለችና አሳባቂዎቹን አሳፈረቻቸው። እኔንም አይዞሽ አለችኝ። የበለጠ ገንዘብ አግኝቼ እንደሆነ ዓይነት እንጂ በፍቅር ተጠምጄ እንደሆነ አድርጋ አልተቀበለችውም። መቼ እኔ ለማጭበርበር ወይም የበለጠ ለማግኘት ሆነና? መቼ የዚህ ዓይነቱን ጠባይ ነበረኝና?

የቅርብ ጓደኛዬ የሆነችው አበራሽ እንኳ እንደማኩረፍ ብላኝ በግድ አነጋገርኳት።

"ምን አድርጊ ትይኛለሽ?" አልኳት።

"ደግሞ እታፍሪም እንዴ? ያንቺን እንደፍጥርጥርሽ እኛ በአንቺ ምክንያት ለምንድነው ስማችን የሚጠፋው?" አለችኝ።

"ለመሆኑ ሰውዬው ሲመጣ ምን ተደረገ?" አልኳት።

"ታሪኩ ሌላ ነበር እባክሽ? እሱማ አንቺን ቆይ አገኛታለሁ ብሎ ዝቷል፣ ውጪ እንዳይሆን እንጂ እዚህ ምንም አይልሽም፤" አለቻት።

"እንዴት ውጪ?" አልኳት እንደገና በመገረም፤

"ለመሆኑ ሰውዬው የቡና ቤቷ ባለቤት ወዳጅ እንደሆነ አውቀሻል?"

"የእትዬ" አልኳት በመደንገጥ፤

"ታዲያስ ማታ አይደለም እንዴ ጉዱን ያወቅነው፣ ለካ እጅሬ እትዬ ያለፈው ሳምንት ከሌላ ጋር አድራ እሱ መጥቶ መሄዱን ሲሰማ በዚያ ተናዶ አይደል በአንቺ ብድሩን ሊመልስ የፈለገው?"

"ኸረ ባክሽ!" አልኳት የበለጠ ለመስማት በመጓጓት።

"እና አልጋ ይዞ ሲመለስ አንቺን በውጪ አስጠርቶ ለመሄድ ነበር ዕቅዱ፤ ውጪ ቆሞ ሲጠብቅሽ ታዲያ እትዬ ድንገት ውጪ ትወጣና ታየዋለች። ከዚያም ነቅታበት ትጮኽበትና ይዛው ገብታ ያድራሉ። በጠዋት ተነስቶ ሄደ። ዝቶብሻል።

"ብሩን እወረውርለታለሁ እንጂ ምን ሊያደርገኝ ይችላል፣" አልኳት።

"እንዲህ አትበይ? በአሁኑ ጊዜ ሰው ምን ይታመናል ብለሽ ነው፤" ለማንኛውም እሱን ስለሸወድሽው ደስ ብሏት እንጂ ገንዘብ ወስዳ የሸወደችው ስንት ሴት አባራለች መሰለሽ። እሱ ስለሆነ ነው የተረፍሽው።" አለች። መቼም ነገር ሲቆይ እንደመርሳት ይላልና "ጉዱ አንድ ሰሞን" ተወራና በቃ። እጅሬም ገንዘቡን መለስኩለት፣ አንድ ጥፊ አላሰኝ ሰው ሳያይ፤ በዚሁ ከተገላገልኩ በቃኝ ብዬ ጥፊዬን በፀጋ ተቀበልኩ። ይህን ሁሉ የምነግራችሁ ሰይፉን በመውደዴ የደረሰብኝን በመጠኑ ልነግራችሁ ነው፤

መቼም በሥራ የተሰማራ ሰው በየምሽቱ ቡና ቤት ሹልክ ለማለት ጊዜውም ገንዘቡም አያስችልምና ሰይፍዬ ሆዬ ሁለት ቀን ቢቆይ ሦስተኛው ቀን ላይ አይቀርም። ቀንም በሰጠኝ የመሥሪያ ቤት ስልክ እደውልለትና እናወራለን። ጓደኛዬ "ቆይና ትንሽ ታይዋለሽ ጠባዩ ሲለወጥ፤" ብትለኝም ጭራሽ በቆየሁ ቁጥር ጠባዩ እያማረ ለኔ ያለው ስሜት እየጠነከረ መምጣቱ ነበር የታየኝ። ስንገናኝ ቡና ቤት እንደምትሠራ ሴት ሳይሆን ት/ቤት እንዳለች ልጃገረድ እንዲሰማኝ ነበር የሚያደርገው። ያስብልኛል፤ እኔም ወደድኩት፣ በቃ ምናለፋችሁ ወደድኩት፤ ሰይፍዬን የወደድኩት በእሱነቱ ነው። ስለሚወደኝ፣ ስለሚያከብረኝ፣ ቡና ቤት አገኘኋት ብሎ ስለማይንቀኝ፣ ጥሩ ስለሚመክረኝ። በቃ ሌላ ምን እፈልጋለሁ።

ይህ በዚህ እንዳለ አንድ ቀን፣ ቅዳሜ ነበር ዕለቱ፣ በጠዋት ተቀጣጥረን ይዞኝ እቤቱ ወሰደኝ። የሚኖረው እንግሊዝ ት/ቤት አካባቢ ነው። እናቱና አንዲት ትንሽ እህቱ ናቸው አብረውት የሚኖሩት። በደምብ ተቀበሉኝ። ከእናቱም ጋር አስተዋወቀኝ ትንሽ እህቱን ውድድ አደረግሁዋት። ይህ ቀን ነበር የሰይፉን ማንነት የበለጠ እንዳውቅ ያደረገኝ። ቤተሰቦቹ እንደኔ ቤተሰቦች በኑሮአቸው ይህን ያህል የደላቸው አይደሉም። ሃብታም አይደሉም ለማለት ነው። አባቱ የጦር ሠራዊት አምሳ አለቃ ሆነው ኤርትራ ሄደው ሲዋጉ ይሞቱና እናቱን ለመጦር እህቱንም ለማሣደግ የአባቱ የጡረታ ገንዘብ አልበቃ ስላለ እሱ ከ2ኛ ዓመት ዩኒቨርስቲ ትምህርቱን አቋርጦ ሥራ እንደያዘ ነገረኝ። ምንም የአባቱ መሞት በቤተሰቡ ውስጥ ትልቅ ኀዘን ቢሆንም የተባረከ ልጅ መውለዳቸው በጃቸውና እናትየው ከሚያገኟት አነስተኛ የጡረታ ደመወዝ ጋር ሰይፉ እየሠራ የሚያመጣው ተጨምሮ ደስተኛ ኑሮ ይኖራሉ። ደስታ ማለት ለካ የሀብት ብዛት አይደለም። ሀብታም የሆኑ ቤተሰቦች ቢኖሩኝም ቤት ውስጥ ደስተኛ ስላልነበርኩ አይደል ጥዬ የጠፋሁት። እና ደግሞ እናትና ልጅ የነበራቸው መተሳሰብና ለሰው ያላቸው ፍቅር ሌላ ነበር። ገና ሲያዩኝ ትግሬ በመሆኔ ደስ ላይላቸው ይችላል ብዬ ፈርቼ ነበር።

እንደኔ ዘመዶች። የኔ ዘመዶች "አማራ ጓደኞቼን በሩቅ" ነበር የሚሉኝ። ያን ያህል የቅርብ ጓደኛዬ የነበረችውን በቀይ ሽብር የሞተችውን እምሳለን ብዙ ጊዜ ቤት እወስዳት ያልነበረው ለዚሁ ነው። ዘመዶቼ ፊት ይነሷት ነበር። በተለይ ወንድሜ። ታዲያ በሰይፍዬ እናትም ሆነ እህት ይህን የጥላቻ ወይም የማግለል ስሜት አላየሁባቸውም። ዓይኔ አካባቢ ያለችውን የትግርኛ ምልክቴን አይተው ይጠሉኝ ይሆን ብዬ ፈራሁ እንጂ እሳችውስ በፍቅር ነው የተቀበሉኝ። ያለውን ሰራርተው ነው "አፈር ልሁንልሽ ብይ ጠጪ" እያሉ ያስተናገዱኝ። ሌላው ፍርሃቴ ደግሞ "እኔ የመጣሁት ከቡና ቤት መሆኔን ያውቁ ይሆን?" የሚል ነበር። የሰይፉ ለኔ ያለው አቀራረብና ስሜት እንጂ ወሳኙ ከየት ልምጣ ከየት፣ ከማን ዘር ልምጣ ጉዳያቸው አልነበረም።

መንፈሴን ለተወሰነ ጊዜ የረበሸው በቤተሰቤ ውስጥ እያለሁ በልጅነቴ በቤት አካባቢ በተለይ በታላቅ ወንድሜ አማካይነት በአዕምሮዬ ውስጥ የተቀረፀው የሌላ ዘር ጥላቻ ነበር። አሁን እያደግሁ ስሄድ የዚህ ዓይነቱ ገጠመኞቼ ግን ብዙ እያስተማሩኝ መምጣታቸውን ሳላወሳ አላልፍም። እና ሰይፉ ስለ ቤተሰቦቹ ጠይቄው አባቱ በግማሽ ጐናቸው ኦሮሞ በሌላው ጐናቸው ደግሞ አማራ፣ እናቱ ሙሉ በሙሉ አማራ መሆናቸውን ነገረኝ። እኔው ከቤተሰቤ የወረስኩት "የማነህ ዘር?" ጥያቄ አሳፈረኝ። ለምን ጠየቅሁት አልኩ በሆዴ። እና እናቱ ያቀረቡልኝን ነገር ከበላሳን በኋላ ሁለታችን ለብቻችን ጥለው ሲወጡ ጨዋታ ጀምርን።

"እናትህን በጣም ወደድኳቸው" አልኩት።"የዋህና ደግ ናት፣ አይደለችም?" አለኝ።

"እንደቀናሁባቸው አታውቅም!" አልኩት አንገቴን ደፋ አድርጌ።

"እንዴት?" አለኝ ትክዝ ብሎ። ሰይፍዬን የምወደው እኔም ስተክዝ አብሮኝ ትክዝ ስለሚል ነው።

"ስለኔ ቤተሰብ እኮ አላጫወትኩህም።" አልኩት። "ሰይፉ ስለቤተሰቤ ብነግርህ ልትጠላኝ ትችል ይሆናል ብዬ ደግሞ እፈራለሁ።"

"እኔ የወደድኩት አንቺን፤" አለኝ ትክ ብሎ እያየኝ "ደግሞስ ለምን እጠላቸዋለሁ አንቺን ስለወለዱልኝ?"

ዓይኔ እምባ እንዳዘለ ሲያይ ጊዜ እቅፍ አድርጐ ሳመኝ። እቅፉ ውስጥ ሲከተኝ መከታነቱ ተሰማኝ። ትንሽ ዝም ካልኩ በኋላ ታሪኬን ሁሉ ነገርኩት፤ አንድም ሳልጨምር፣ አንድም ሳልቀንስ፣ ስለአባትና እናቴ፣ ስለወንድሜ፣ ከቤት ለምን እንደጠፋሁ፣ ስለጓደኛዬ አምሳልዬ፣ ፔሌ ስላለው አኗኗሬ፣ እሱን ሳገኝ ያገኘሁትን ደስታ፣ ምንም አልደበቅሁትም። ጸጥ ብሎ አዳመጠኝ። አልፎ አልፎ ብቻ አንዳንድ ነገሮች ግልፅ እንዲሆኑለት ከመጠየቅ በቀር ፍፁም አላቋረጠኝም።

አዳማጭ ማግኘት ምንኛ ደስ እንደሚል ታውቃላችሁ አይደል። የሆዴን ሁሉ ዝርግፍ አድርጌ ስነግርው እየቀለለኝ መጣ። ያለሁበት ችግር ሁሉ የተፈታልኝ መሰለኝ።
እንደጨረስኩ ለጥቂት ደቂቃ ፀጥ አለና፤

"ከቤት ከወጣሽ በኋላ ቤተሰቦችሽን ፍፁም አላገኘሻቸውም?"

"እየነገርኩህ፤ አባቴን አታውቀውም። ማጅራቴን ይዞ ነው አስመራ የሚልከኝ እኔ ደግሞ አስመራ መሄዱ እንደገና ለሌላ ችግር ራሴን መጋበዝ መስሎ ታየኝ፤"

"አይ አልማዝ፤ በጣም አሳዘንሽኝ" አለኝ።

"ደግሞ ያልነገርኩህ ሌላ፤ ደምበኛ ስሜ አልማዝ አይደለም። ይህን ለአንተ ብቻ ነው የምነግርህ" አልኩትና ደምበኛ ስሜን ነገርኩት።

"ይህ ሁሉ ቤተሰቦችሽ ፈልገው እንዳያገኙሽ ነው፣ አይደል።" አለኝ

"እሱም ነው፤ ደግሞ አብረኸት የሚለው ስም ለፒያሳ አይስማማም አይደል?" አልኩት።

"እሱ መቼስ እንደየሰዉ ይለያያል። አብረኸትም ተባልሽ፣ አልማዝ አንቺነትሽን አይቀይረውም" አለኝ።

"ልክ ነህ " አልኩት።

"እና አሁን ኑሮን እንዴት ልትገፊ አሰበሻል?" አለኝ።

"ይኸው ነው፣ በቃ፤ የዛሬን እንጂ የነገን አስቤ እንኳ አላውቅም" አልኩት። በርግጥ ከምሬ ነበር ይህን ያልኩት። ዛሬ የተገኘውን ዛሬውኑ አጠፋፍቶ መኖር፤ ለነገ ደግሞ ነገ ያስብ ማለት። ይህ ነበር በዚያ ዓይነት ኑሮ ላይ ያለን ሴቶች ሁኔታ።
"ትምህርት ቤት ለመመለስ፣ ሌላ ሥራ ለመፈለግ በፍጹም አላሰብሽም" አለኝ።
"ትቀልዳለህ መሰለኝ። ዛሬን ማደሬን እንጂ ነገ መኖሬን እንኳ የማላውቅ ሰው ነኝ ትምህርት ቤት የማስብ?"
"ቤተሰቦችሽን ከተለየሽ ይኸው አምስት ወር ሆነኝ አልሽ፣ ይኼኔ ናፍቀውሽ አገር ምድሩን እያተራመሱ ነው። ምናልባት ቢያንስ ለእናትሽ አዝነሽ ብትመለሺ።"
"አስመራ ሊልኩኝ ነው እያልኩህ፣"
"አስረጂያቸው፤ አሁን እዚህ ትንሽ ነገሩ በረድ ስላለ ትታሰሪያለሽ የሚል ስጋት ሊኖራቸው አይችልም። እዚሁ እንደፍላጐትሽ እንድትቀሪ እንደሚያደርጉሽ አትጠራጠሪ፤" አለኝ።
"ቤተሰቦቼ እኮ አታውቃቸውም።"
"ምንም ቢሆን ሁሉ አባትና እናት ለልጆቻቸው ያላቸው ስሜት አንድ ነው። ወንድምሽ ሄዷል አልሺኝ። እህትሽላ፤"
"እሷማ አለች። በቀደም ዕለት ከሰፈር አካባቢ የመጣ ወሬ እሷ እንዳትጠፋብን እያሉ ስለፈሩ አሜሪካን አገር ሊልኳት ቃል ገብተውላታል፤ አባቴ እየተዘጋጀ ነው።"

"በአሁኑ ጊዜ አሜሪካን አገር መሄድ ቀላል መሰለሽ?"

"አባቴን አታውቀውም። በገንዘቡ ኃይል የማያደርገው ነገር የለም። በዚህ ላይ ታውቃለህ የኛ ዘሮች መጠቃቀም ላይ በጣም ጉበዝ ስለሆኑ ሃላፊነት ላይ ያሉ ስንት ጓደኞች አሉት መሰለህ" አልኩት።

"አልምዬ እንደሱ እንኳን አትበይ፤ ያንቺ ዘር ሆነ የሌላ ዘር ሁሉ በመተዋወቅ ይረዳዳል።" አለኝ።

"የኔን ዘር ሆነህ አላየኸውምና ብነግርህ ሊገባህ አይችልም። መጠቃቀም መረዳዳት ስልህ እኮ የኛው እንዳው ተራው ዓይነት መረዳዳት አይመስልህ ሌላውን ይጉዳ አይጉዳ ግድ የሌለው ዓይን ያወጣ ዓይነት መጠቃቀም ነው ያለው። እንዳው ታዝበህ ይሆናል ትግሬ ሃላፊ የሆነበት መሥሪያ ቤት ብትሄድ በሥሩ የሚቀጥራቸው ሠራተኞች አብዛኞቹ ትግሬዎች ናቸው። የሌላውን ብታይ ግን እንዲህ አይደለም።" አልኩት።

"እሱን እንደመሰለሽ እይው፤ እኔ አሁን ያሳሰበኝ ያንቺ የኑሮ ሁኔታ ነው።" ስለዚህ ነው ቤተሰቦችሽ ጋ ብትመለሺ ይሻላል የምለው፤"

"ከእንግዲህ ቢያስገቡኝ አይደል፤"

"ግዴለሽም እንሞክር"

"እንሞክር ስትል?"

"ማለቴ እኔ ላስታርቃችሁ"

"በል ተወው! ያውም አንተ?"

"እንዴ ምን ይጉድለኛል፣ ሽማግሌ ስላልሆንኩ ነው?"

"ምኗ ነኝ ብለህ?"

"ጓደኛዋ"

"እኮ ምን ዓይነት ጓደኛ?"

"በቃ ጓደኛ አለ አይደለም"

"እነሱ የሚረዱት በሌላ ነው።"

"ታዲያ እሱንስ ቢሆን ማን ይፈራል፤ እወድሻለሁ፤ እጮኛነትሽም እንዲያጸድቁልኝ በዚያው እማለዳለሁ፣ አይመስልሽም" አለ

ፈገግ ብሎ።

"እኮ አንተ እኔን ለማግባት የቤተሰቦቼን ፈቃድ የምታገኝ ይመስልሃል?"

"ለምን አይፈቅዱልኝም? ምን ይጉድለኛል? ደግሞ ወሳኙ ያንቺ ፍቅር ነው። የነሱን ፈቃድ የምንሻው ለቡራኬአቸውና ለምርቃታቸው ነው።"

"እና ይፈቅዱልኛል ነው የምትለው?"

"ምን አይፈቅዱልኝም።"

"ስማ የኛ ዘሮች ከሌላ ዘር በጋብቻ መተሳሰር የሚፈልጉት ጥቅም ሲኖር ነው። ወይ ሹም ከሆነ ነው፤ እና አንተ ታዲያ ሹም ነህ?" ሳቅ እያልኩኝ፤

"ተይ እንጂ አልማዝዬ፣ እንዲህ አድርገሽ የመጣሽበትን ዘር አትኰንኚ። ደግሞ አንዳንዱ እንዲህ ቢሆን ሁሉን ሊወክል አይችልም ድፍን አድርጎ የመጣሽበትን ዘር በአጠቃላይ መኰነን ተገቢ አይደለም።"

"አባቴ እቤት ውስጥ አንዳንዴ የሚነግረኝን ታስታውሰኛለህ እንደዚህ ስትል፤" አልኩት።

እንዴት?" አለኝ።

"አማራና ጋላ ሞኞች ናቸው ይለኝ ነበር።"

"እና አንቺ ይህን እንዴት አየሽው?"

"እኔ ጓደኞቼ፣ ያገኘሁዋቸው አማሮችም ሆነ ኦሮሞዎች ከሰው አክባሪነታቸውና ከንፅህናቸው የመነጨ የዋህነት ነው እንጂ ያየሁባቸው ሞኝነት አላየሁባቸውም፤ እና ታዲያ እኔ ስለማውቀው ስላለሁበት ሁኔታ ስነግርህ አንተ ንፁህ በመሆንህ በየዋህነት መነፅር የምታየውን ብቻ ነው የምትነግረኝ። 'ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' ባክህ።

"እና ምናልሽ ታዲያ" አለኝ በጉጉት።

"ምኑን?" አልኩት።

"ወደ ቤተሰብ የመመለሱን ጉዳይ?" አለ። ተስፋ አልቆረጠም።

"አንተ እንድመለስ ትፈልጋለህ ወይ?" አልኩት።

"አጠያየቅሽ አልገባኝም" አለኝ።

"ማለቴ ቤተሰቦቼ ጋ ተመልሼ ብገባ ከአንተ ጋር የመገናኘት ዕድሌ የሚመነምን ይመስለኛል።"

"እሱን ግድየለሽም፤ ዘዴ ይኖረዋል"

"እኔ በበኩሌ ነግሬሃለሁ እንደማልፈልግ አንተ ካልክ ግን አስብበት ይሆናል"

"እኔ ካልኩ እንዴት?"

"ሰይፍዬ እኔ እወድሃለሁ። አንተ ያልከውን ነገር ከመፈፀም ወደኋላ የምል አይደለሁም። ይህ አሁን ያቀረብከው ሃሣብ ምንም ለእኔ ጥሩ አይደለም ብዬ የምገምተው ቢሆንም አንተን ደስ እንዲልህ ከማድረግ ወደኋላ ለማለት አቅሙ የለኝም።" አልኩት ዓይን ዓይኑን እያየሁ።

"ጉሽ የኔ ቆንጆ አየሽ በእንደዚህ ዓይነት ኑሮ እስከመቼ ትቀጥያለሽ። እና እንሞክረው ካልሆነ ደግሞ ሌላ ዘዴ እንፈልጋለን። በኔ በኩል ግን ከአንቺ የሚለየኝን ሁኔታ አንቺ ካልፈጠርሺው በቀር እኔ አላመጣውም።"

"ተው እንጂ ሰይፍዬ እንዲህ አትበል። እየነገርኩህ የሆዴን ሁሉ አውጥቼ ያጫወትኩህ ካንተ መለየት ስላልፈለግሁ አይደል፤ በኔ በኩል እኔና አንተን የሚለያየን ነገር እንደማልፈጥር ቃል ልግባልህ፤ አንተም ግባልኝ።"

"ገባሁልሽ" አለና ትንሹን ጣቱን ከትንሿ ጣቴ ጋር አቆላልፎ "ከዛሬ ጀምሮ ፍቅረኞች ብቻ ሳንሆን ሽርኮችም ነን" አለኝ።

ድምፄ ሰልል፣ ዓይኔ ፍዝዝ ማለቱ ይሰማኛል። ጣቴን በጣቱ እንደቆላለፍኩ "ሽርኮች ነን ሰይፍዬ" አልኩና ጣቴን አላቅቄ አንገቱ ላይ ተጠምጥሜ ሳምኩት። . . . (ይቀጥላል)

---

ታሪኩ እውነተኛ ታሪክ ነው። እንዲጥም አድርገን ከማቅረብ በቀር የጨመርነው ነገር የለም። ስሞች ተቀይረዋል። ባለታሪኳ የምትኖረው አሜሪካ ነው።

---

# « ላንዳፍታን በሞቅታ »

ከጣጤው (አትላንታ)

እያደር የመጠጥ ነገር እየገረመኝ መጥቷል። ጠጪ አይደለሁም። ያው እንደተለመደው ሁለትሦስቱን ኳ አደርጋለሁ (እኔ ልሙት ከዛ በላይ አልችልም)። የተዝናና ሰውነትና በሞቅታ የሚወናጨፍ አዕምሮን ይዞ ከብዕርና ከወረቀት ጋር መቀመጥን የመሰለ ፀጋ አጋጥሞኝ ቁጭ! ሆሆ!

እና ታዲያስ እንዴት ናችሁ ላንዳፍቶች? የኔማ ነገር ምን ልበላችሁ? የማገኘው ሁሉ የሚያወሩት ሌላ፤ እኔ ደግሞ የሚሰማኝ ሌላ ሆኖብኛል ነገሩ። ያለፈችውን ዕትም አንብቤ የተረዳሁት ነገሮች ቢኖሩ ፍቅርና ፖለቲካ ሕዝቡን አሁንም ግራ እያጋቡ መሆናችውን ነው። ችግሬ ፍቅርና ፖለቲካን በሚመለከት የሚሰማኝ ሰው ማጣቴ ነው። "በጄ በሉኝ እንጂ!

በመጀመሪያ ነገር ማሳወቅ የምፈልገው እዚህ አሜሪካ ውስጥ ፍቅር የሚባል ነገር አለመኖሩ ነው። የዚህ አገር ፈሊጥ እየተያያዙ መጠዛጠዝ ብቻ ነው። የጥዝጠዛው ተካፋይ መሆንም ተገቢ ነው። አለበለዚያ እንደሎተሪ አንድ ቀን ፍቅር ይደርሰኛል እያሉ ተስፈኛ መሆን የብቻ እንደሚያስቀር አትጠራጠሩ። ላስረዳ:-ሰውዬው ድህነቱ ሰልችቶት በየቀኑ እግዜርን "እባክህ አምላኬ ሎተሪ ይድረሰኝ" እያለ ይለምናል። የሰውዬው ልመና የሰለቸው እግዜር አንድ ቀን ምርር ብሎ "እኔን በባዶ ሜዳ ከመለመን በፊት መጀመሪያ ሎተሪ መግዛት ጀምር" አለው። አሁን የጥዝጠዛው ተካፋይ መሆን ግልፅ መሰለኝ።

ፍቅር! አይ ፍቅር እንዲህ ድራሽ አባቱ ማ እንዳጠፋው አላህ ይወቅ! ያኔ ድሮ ቆንጆዬ አይቶ የልቤ ትርታ የሚፈጥንበት፣ ተጋድሜ እንቅልፍ የማጣበት፣ በየሰዓቱ ወደስልክ የምሮጥበት- ያ ቆንጅዬ ንፁሕ ፍቅር ስሜት - ያ ፍቅር ጠፍቶብኛል። አሁን አሁን ደስ የምትለኝን ቆንጆዬ ባየሁ ቁጥር ከጭንቅላቴ በፊት ቱግ ብሎ የሚነሳው ያ ነገሬ ነው! አግብቼ ልጅ ወልጄ ቤት ሠርቼ ዘመዶቼን ጡሬ... ያ ያ ምኞት እንደ ኢትዮጲያ አብዮት ተቀልብሶብኛል። ሆሊውድና ዲሞክራሲ ያመጡት ጣጣ!

የኔ ብጤዋ ወ/ት ትዝታም ባለፈው ዕትም ላይ "አላለልኝ ይሆን..." በማለት የፍቅር ሐተታ አቅርባለች። እርግጥ አላለላት ይሆናል። ሴትየዋ ግን የምትገርም ናት። "ቁመናው ዘለግ ያለ የቀይ ዳማ በቃ ምን አለፋችሁ ሴቶች የምንወደው ዓይነት..." እያለች እንደእኔ ዓይነቱን አጭር መልከመልካም ኩሩ አበሳጭታለች። በዚች ገጠሬ አባባል ያን ያልመሰለ ወንድ ያገቡ ሴቶች ሁሉ የማይወዱትን አግብተዋል ማለት መሆኑ ነው! "ሴቶች የምንወደው ዓይነት..." የሚለው ገለፃ እርሷና ጓደኞችዋ የሚወዱትን ማለቷ መሰለኝ። ጠባብ ዓለም ውስጥ የምትኖር መሆኗን ጠርጥሬ ነው ገጠሬ ያልኳት። እና ያዲያ ሴትየዋ ሐሙስ ሐሙስ የብርታት መርፌዋን እያገኘች ከከረመች በኋላ`"ይሄንን

ባልአጣች የሚል ወሬኛ ህዝብ አፉን ለማስያዝ" ብላ ትዳር ፍለጋ ተሰማራች። የሐሙስ ሐሙስ ደንበኛዋን ባለትዳር ሆኖ ብታገኘው "ሁለተኛ አጠገቤ እንዳትደርስ" ብላ አባረረችው። ሴትየዋ ተጭበረበርኩ ባይ ናት። ካጭበረበረሽም ደግ አድርጓል! ሴት ልጅን በመጀመሪያ ወስለት-ቀጠፍ ካላደረጓት እሷስ መቼ እሺ ትልና? ይሄ እንግዲህ የትም ያለ ነው። እኔ እንኳ ባቅሜ ለስንቱ ሴት ወስልቻለሁ መሰለሽ! ታዲያ ይሄ ይሄንን ወንጀል ልታደርጊው ፈለግሽ? አንድ ፈረንጅ "Tell me lies- Tell me sweet little lies" ብላ የዘፈነችውን አልሰማሽም ወይ? ዘፈኑ እንኳ የቆየ ነበር ብቻ የአንቺ ትኩረት አፍ ማዘጋት ላይ ነበር መሰል። ከዛ በኋላማ አንቺም በተራሽ እንደለመደብሽ ባለትዳር ካለወጣሁ ባይ ሆነሽ አረፍሽው! ይቺ ናት ግብረገብ! የባለትዳር የባለትዳር ያው የበፊቱ አይሻልሽም ነበር? ቢያንስ ሐሙስ ሐሙስ ፔኒሲሊሽን ያለማቋረጥ ታገኚ ነበር። ሌላ ባለትዳር ማውጣት ጀመርሽና ከሞቀ ትዳሩ ልታፋርሺው ስትሞክሪ ነገረ ሥራሽን ተመልክቶ "ሰኪውውውውዝ ሚ" ብሎ ትቶሻል። እሱም ደግ አደረገ። ይቺ ያበጠችውን ልብሽን ትንሽ ተንፈስ አድርጐልሻል። አሁን በመጨረሻ የቴሌፎን ፍቅረኛ ይዘሽ ካበቃሽ በኋላ ሰውዬው በውን ሊጠይቅሽ ቢመጣ "ቁመናው ደህና... መልኩ ግን እንደነገሩ" ሆኖብሻል። ስገምትሽ ብዙ ተረረም ተረረም ለምደሻል። እና ሴትዮ ታሪክ ዝባዝንኬ ማብዛቱን ትተሽ ቢያንስ የሐሙሱን ፔኒሲሊን የምታገኚበትን ዘዴ አስቢ። ከአቶ "እንደነገሩ" ጋር ብዙ እንደማትጓዢ ስለጠረጠርኩ ካሁኑ ቀደም ብዬ ሐሙስን OFF የምሆንበትን መንገድ እያዘጋጀሁ ነውና ብትጠይቂኝ ጥሩ ነው። "አንድ ማሳሰቢያ አለኝ፤ ከመልክ ይልቅ የሚማርከኝ መቀመጫ ስለሆነ እዚያ አካባቢ 'እንደነገሩ' ከሆንሽ እኔም ሰኪውውዝ ሚ እንደምልሽ እወቂው። ሌላው የፍቅር ጉዳይ "ምን ትመከሩኛላችሁ?" ያለችን የባለትዳር ነገር ነው። "ባሌ ፖለቲከኛ ሆነብኝ...ጥዬው መሄዴ ነው" ብላ አማርራለች። የኔ እህት! ጣጣ ሳታበዢ የልጅሽን አባት መለየት ፈልገሽ ከሆነ የራስሽ ጉዳይ! የምሥሽን (የድርሻሽን ማለቴ ነው አቦ!) ኋላ ታገኛለሽ። አንድ ፈረንጅ (ጄፍሪ ዳመር) የሰው ሥጋ እየቆረጠ መብላቱን ሰምተን ጉድ! ጉድ! ስንል አንቺ ግን የባልሽ መቦትለክ ጉድ ጉድ አሰኘሽ! የትኛው ዘመን ላይ ይሆን ያለሽው? የልጅሽ አባት ፖለቲካ መውድዱ አንቺን እንዲህ ሊያሾር መብቃቱ ገርሞኛል። አልፈሽ ተርፈሽ አደባባይ መሃል ወገብሽን ቀስረሽ "አለበለዚያ ጥዬው መሄዴ ነው!" አልሽ። ችግርሽ ምንድነው በሞቴ? የልጅሽ አባት ተነገወዲያ ባስኬት ቦል ቢወስድስ? በሳምንቱ ሥጋ አስጠልቶኛል ቬጂተሪያን ሆኛለው ቢልሽስ?ማነው አንቺን የሰው ስሜት ተቆጣጣሪ ያደረገሽ? እያደረ ሳስበው ለሰውዬው ደንታ የሚሰጥሽ አልመሰለኝም። በነገር ላይ ነገር ገምደሽ ሰውዬውን እንደ ሀጢያተኛ ወቅሰሽና አስወቅሰሽ ሌላ ወንድ ፍለጋ

ተፍ ተፍ ለማለት የተሰናዳሽ ሴት መስለሽኛል። "ባሌ ፖለቲካ ወደደ" ብሎ አካኪ ዘራፍ! ሆሆ!"እኔ ጥሩ የቤተሰብ ባል እንጂ ፖለቲከኛ አልፈልግም" ብለሽናል። ፖለቲከኛ ባል አይሆንም ለማለት ፈልገሽ እንደሆነ ነገሩን ብታስቢበት ይሻላል። ሰውዬው ቦትልኮ ቦትልኮ ጠቅላይ ሚኒስቴር ወይም ፕሬዚዳንት ቢሆንስ? አልፈልገውም ትያለሽ ወይስ ሽቶና ቅባት በአየር መንገዳችን ታመላልሺያለሽ? ችግርሽ ፖለቲካ ሳይሆን ገንዘብ መሰለኝ። "ጠብሽ (ደሀ) ነንና ፖለቲካህን ጥለህ ገንዘብ ብታሳድድ ይሻለኛል" ነው የምትይው ሰውዬውን። አንቺ "ጥሩ የቤተሰብ ባል" ፈላጊ ከሆንሽ መጀመሪያ ጥሩ የቤተሰብ ሚስት መሆን ይገባሻል። ይሄ የሚያስለፈልፍሽና የሚቀረቁርሽ የቤተሰብ ጉዳይማ (ግብረገቡ) እስከምተለቱ ድረስ ባልሽ ጋር ሁኚ ይል የለ እንዴ? በሥርግ ሆነ በሰማንያ፣ በሰማንያ ሆነ በአርባ፣ ጋብቻ የሚያዘው እሱኑ ነበር። ወይንስ አንቺ አዲስ የፈጠርሺው የሀያ ጋብቻ "ፖለቲከኞችን አታግቡ"ይላል?ሴትዮ! የሦስት ሰው ሕይወት ከመበጥበጥሽ በፊት ቤተሰብሽን በደንቡ ማስተዳደር የምትፈልጊ ከሆነ ዮዲት ጉዲትነትሽን ትተሽ ትዳርሽን ገንቢ፣ አይ አሻፈረኝ የምትይ ከሆነ የሰውዬውን ስቃይ ሳታበዚ እንዳው ቶሎ ወደምትሄጂበት ሂጂና እንደተለመደው ከሩቅ ሆነሽ የስም ማጥፋት ዘመቻሽን ቀጥይ።

ሌላው የፖለቲካ ጉዳይ የካይሮ ደርሶ መልስ ነገር ነው። አዲስ አበባ ተካሂዶ ለነበረው ኮንፍረንስ ላይ ለመገኘት ከፈረንጅ ከተማዎች ጉዞ ጀምረው ካይሮ ላይ ሲደርሱ 'ቀፈፈን' ብለው የተመለሱትን ማለቴ ነው። እንዳው ለነገሩ እስራት ማንን ገደለ? እንደኔ ከሆነ ግጥም አድርገው ቦሌ ድረስ ሄደው የሚሆነውን ማየት ነበረባቸው። እሥራትና ግርፋትን ሸሽቶ ሥልጣንና ሀላፊነት የሚገኝ ከሆነማ እኔም የማልገባበት ምክንያት አይታየኝም። አለበለዚያ እኔን ከመሰለው መንገደኛ ሰዎቹን ምን ሊለያቸው ነው? ይቅርታ አድርጉልኝና ከካይሮ ከመመለስ ይልቅ ቦሌ ገብተው ቢታሰሩ ይሻለኝ ነበር። ይሄኔ በዛም በዚህም ብለን ባስፈታናቸው ነበር። ያ ባይሆን እንኳ ማታገያ ባሆኑን ነበር። ለዚህ አለመታደላቸው አሳዝኖኛል። በነገራችን ላይ የኛ አገር ፖለቲከኞች ከፈረንጅ ቂጥ ሥር ላለመውጣት ቃለ መሀላ ገብተው ይሆን? ሥልጣን ላይ ያሉትም ሆኑ ተቀናቃኞቻቸው ፈረንጅ ሥር ቱስ ቱስ የሚሉት ለምን ይሆን? ያለፈረንጅ መቦትለክ አይቻልም ያለው ማነው? ስብሰባ ሲጠሩ ፈረንጅ፣ እርቅ ሲደራደሩ ፈረንጅ፣ ጭቅጭቅ ሲመጣ ፈረንጅ፣ ረሀብ ሲመጣ ፈረንጅ፣ መንግሥት ሲገለበጥ ፈረንጅ፣ መንግሥት ሲቋቋም ፈረንጅ፤ ለምን ይሆን?አንድ ጥቁር አሜሪካዊ ምሁር " በፈረንጅ ቋንቋ የሚቦተልክ አፍሪቃዊ ህዝብ ራሱን ነፃ ለማውጣት አይቻለውም" ያሉትን ያስታውሰኛል።

መቼም የኔ ነገር ያው እንደነገርኳችሁ የማገኘው ሰው ሁሉ የሚያወሩት ሌላ፤ እኔ ደግሞ የሚሰማኝ ሌላ ሆኖብኛል ነገሩ! በሉ ቻው! ■





# የአበው ቅርስ



## ዋሽቶ የሚያስታርቅ ሽማግሌ

ከአብዩ

ባገራችን ባህል መሠረት በሕዝቡ መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን በሠላም ለመፍታት ባላንጣዎችን ተቆጥቶ በማቀራረብና ዋሽቶ በማስማማት የሽማጋሌዎች ስልጣን እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለዛሬው ችግራችን ምሳሌነቱ ታላቅ ነው። ብላቴን ጌታ ማህተመ ሥላሴ ስለቡልጋ ሕዝብ በጻፉት መጽሀፋቸው እንደገለጡት ማንኛውም ችግር ሲፈጠር ሽማግሌዎች ይመረጡና በሸንጎ ተቀምጠው የተጣላ በማስታረቅ የተበደለን በማስካስ ለተጎዳ ችግሩን በማስወገድ ጉዳዩ ወደ ዳኛ ከመቅረቡ በፊት እንዲያልቅ ሕዝብ በፀጥታና በሰላም እንዲኖር ያደርጋሉ።

የነፍስ ግዳይ በሚሆንበት ጊዜ ነፍስ ያጠፋው ሰው ሸሽቶ ገዳም ይደበቃል። የገዳይ ወገኖች ቤተክርስቲያን ሄደው የቤተክርስቲያኑን ደወል ይደውላሉ። ካህናቱም ነገሩን ከተረዱ በኋላ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀል ይዘው ብዙ ህዝብ አስከትለው ከሟቹ ወገኖች ቤት አጠገብ ሄደው እግዚኦ በማለት ታላቅ ድምፅ ያሰማሉ። መልስ እስኪያገኙ ድረስ ባለመሰልቸት ተደርድረው ቆመው ጩኸታቸውን ይቀጥላሉ። ከሟቹ ወገኖች ቤት ሰው ብቅ ብሎ ሲታያቸው መስቀል የያዙት ካህናትና ሁለት ሽማግሌዎች ወደቤት ይሄዱና የምልጃውን ቃል ያመለክታሉ። የሟቹ ወገኖች መክረን መልሱን እናስታውቃለን ብለው ቀጠሮ ይሰጧቸውና በተወሰነ ጊዜ ሲሄዱ ዕርቁን መፍቀዳቸውን ከገለጹላቸው እቤተክርስቲያን የሚገኙበትን ቀን ይቀጥሯቸውና ይመለሳሉ።

ከዚህ በኋላ በተባለው ቀን ከአጥቢያው ቤተክርስቲያን ዕርቁን ለመወሰን ካህናቱም ያገር ሽማግሌዎችም የገዳዩና የሟቹም ወገኖች ይሰበሰባሉ። የዘመድ ዳኛ አድርገው የገዳይ ወገን ስድስት እማኞች አንስተው ሰባተኛ የፈጠማ ዋስ ካደረጉ በኋላ የሟቹ ወገኖች ገዳዩ ከእርስታችን ከደጃችን እንዳይገባ ከዚህ እስከዚህ ባለው ቦታ እንዳይደርሱ ብለው ወስነው ይናገራሉ። የገዳይ ወገኖችም ከተወሰነው ቦታ እንዳይደርሱ ይፈጠማሉ። ገደብ ይደረግባቸዋል። የስምምነቱም ገደብ ከቤተክርስቲያኑ ትልቅ መጽሀፍ (ገድል ወይም ድርሳን) ላይ ያስታራቂዎቹ የቄሶቹ የእማኞቹና የዋሶቹ ስም ገደቡና የዕርቁ ቃል ጭምር ይጻፋል።

የገደቡም ጊዜ ከተጻፈ በኋላ የሟቹም ደም ደረቀ ሲሉ ባለደሙንና ገዳዩን የሸንጥ ሥጋ ያቆራርጧቸዋል። የጉማ ገንዘብ መቀበልና መብላት ፈፅሞ ክልክል ነው። እርም ይባላል።

ይህ ሁሉ ሲሆን ገዳይ በአደባባይ አይታይም። ዘመዶቹም የዕርቁን ቃል ከፈፀሙ በኋላ እሱ ለሸንጥ መቋረጥ ጊዜ ብቻ ይቀርባል። የገዳይ ወገኖች ለሽማግሌ ምሣ አብልተው ለመንግስት ሃያ (20) ብር ከፍለው ይለያያሉ። እንግዲህ ከዚያን ቀን ጀምሮ መስጋት የለም።

እንዲህ እያደረጉ ነበር አበው ከአባት ገዳይ ጋር የሚያስተራርቁና የሚያኗኑሩት። ዋሽቶ የሚያስታርቅ ሽማግሌ አያሳጣን!!

---

## ታላላቅ ጥቅሶች

"በድሀ ሕዝብ ላይ የሚገዛ ክፉ መኰንን እንደሚያገሳ አንበሳና እንደ ተራበ ድብ ነው። አዕምሮ የጐደለው መኰንን ትልቅ ግፈኛ ነው። ግፍን የሚጠላ ብዙ ዘመን ይኖራል። የሰው ደም ያለበት ሰው እስከ ጉድጓድ ይሸሻል፤ ማንም አያስጠጋውም። በቅንነት የሚሄድ ይድናል፤ በጠማማነት የሚሄድ ግን ወዲያው ይወድቃል።"

መጽሐፈ ምሳሌ፤ ም.፳፰(፫) ቁ.፲፭–፲፰

"ለሰው ልጅ አስፈላጊ ቁምነገሮች ሥራ፤ ፍቅርና ተስፋ ናቸው።"

(ጆሴፍ ኤድሰን)

"ሌሎችን ድል የሚያደርግ በርግጥ ጉበዝ ነው። በራሱ ላይ ድል የሚቀዳጅ ግን በኃይልነቱ ከማንም ይልቃል።" (ላዎ)

# TASTE OF ETHIOPIA

## ETHIOPIAN CUSINE

197 Auburn Av.
Atlanta, GA 30303
(404)681-9406

## ባህላዊ የኢትዮጵያ ምግብ ቤት

በንጹህ ጤፍ እንጀራ

ምሳና ራት

ምሳ - ከ$4 እስከ $6 ብቻ

ራት - ከ$4 እስከ $6 ብቻ

(ለልዩ ዝግጅት ዋጋችን ለየት ሊል ይችላል)

የምግባችንን ጣዕም ይወዱታል!

ዋጋችንም ርካሽ ነው!

ብቅ ይበሉ!

LUNCH $4.00 TO $6.00
DINNER $4.00 TO $6.00

*(Special order price may vary from the above.)*

Open 11:00 A.M. to 11:00 P.M. 7 days a week






**ውብሸት ገሠሠ** **መኩሪያ በቀለ**

ከአዲስ አበባ ቤታቸው በ ፲፱፻፸፯
እንደወጡ የጠፉ
ያሉበት ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው
በትልቅ ጭንቅ ላይ ናቸው።
ስለነሱ የምታውቁ
ለላንዳፍታ አስታውቁልን።

ቤተሰቦቻቸው


‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡

## የምሥራች በምስራቅ አትላንታ ለምትኖሩ

በዘመናዊ ዕቅድ ተመርታችሁ፣
ገንዘብ የሚሸምተውን ሁሉ ሞክራችሁ፣
ደስታንና ሰላምን የመንፈስ ዕረፍት ላጣችሁ፣
የምሥራች አለን የምናበስራችሁ።
በምሥራቅ አትላንታ በአቅራቢያችሁ፣
አዲስ ቤተክርስቲያን ተከፈተላችሁ።
ስለዚህ ኑ ተጋበዙ የሕይወትን ሕብስት፤
የሚያዘጋጀንን ለሰማዩ መንግሥት፤
ለምድራዊውም ቢሆን ፍፁም በረከት፤
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሚገኝ ኅብረት፤
ለተግሣፅ፣ ለምክር፤ ለጸሎት፣ ለትምህርት፣
እንሰብሰብ ለአምልኮ በክርስቶስ አንድነት።

ቦታው ፤ - 3895 Church St.
North Indian Creek/Church St.
Clarkston, GA.

ሰዓቱ ፤- 4:30 6:00 pm

ለተጨማሪ መረጃ-ስልክ -(404)299-8277

‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡ ‡


## « ድ ብ ር ት »

DEPRESSION

ድብርት ዕድሜንና ጾታን እንዲሁም ዘርን ሳይለይ ማንንም ሰው ሊያጠቃ የሚችል የአዕምሮ ጭንቀት ውጤት ነው። በአሜሪካ 40 ሚሊዮን ሰው በዚህ ችግር ውስጥ እንዳለ ይነገራል። ከበድ ያለ ድብርት የያዘው ሰው ወደ ተስፋ መቁረጥ፣ ከመጠን የላቀ ፍርሃት (እርዳት)፣ ዝለት፣ ራስን መጣል፣ ተስፋ ቢስነት ይደርስና ለራሱም ሆነ ለሌላው አደገኛ ሁኔታ ላይ ሊደርስ ይችላል። የእንቅልፍ ችግር ካለቦት፤ በአጭር ጊዜ ክብደት ቢጨምሩ ወይም ቢቀንሱ፤. ጭንቀት ወይም ባዶነት ቢሰማዎት፤ ከለመዱት ውጪ በሌላ መንገድ ደስታ የመፈለግ ጉጉት ካሎት፤ አካላትዎ፤ አስተሳሰብዎ፤ አነጋገርዎ ከወትሮው ዝግ ያለ ከመሰሎት፤ ድካም፣ ሕመም፣ ጉሮሮዎ ውስጥ እንደ እብጠት ከተሰማዎት፤ አብዛኛው ነገር ወይም ሁኔታ ከንቱ፣ አሸባሪ ወይም ፋይዳ ቢስ እየመሰለ ካስቸገርዎ - እስቲ ያነጋግሩን!


መምህር ተጋ ሌንዳዶ

የሥነ መለኮትና የተመክሮ ባለሞያ
ቢሮው የሚገኘው በክላርክስተን ባፕቲስት
ቤተክርስቲያን የESL (የእንግሊዝኛ ት/ ቤት)
በስ ቁ (404)296-6483 ወይም 299-8277
ደውላችሁ ማነጋገር ትችላላችሁ።
አድራሻው፤- 3895 Church St.
Clarkston ነው።

# የግጥም ጉባኤ

## የጉላግ አርችፔላጎ

መሪጌታ ልሳኑ ስምረት (ከሴንትሉዊስ)

ዛሬ እንኳን ይመርብን ኩታ ለብሰን እናድምቀው፣
ማገር ማገረን ውል ሳይጠፋ
ተንጨፋሮ የቆመውን፣ ባንድ ረድፍ እንክውነው፣
ድር በድር አጠላልፈን፣ እንደጋቢ እንቋጨው።
ጥልፍ በጥልፍ አመሳስለን፣
እንደቀስተ ዳመና ሰንደቅ
በኅብረ-ቀለም እንዘውረው።
ሐር ለብሰን ሱፍ አጥልቀን፣
ምርኩዝ ይዘን ጭራ ረጭተን
በዕድምታ ከመቅፀበት፣ ደቦውን እናድምቀው።
ቤት ፈርሶ ሲመሰረት፣
የቱ ላይ ነው በግለሰብ
ምሶሶው የቆመው።
ባንድ እጅ ተጨብጭቦ፣ ሆታ ዘፈኑ የሚደምቀው፣
የእስክስታው የዘፈኑ፣ አገር አቋርጦ የሚሰማው፣
የሲቃ ድምፅ ተበራክቶ፣ ወገን የሚቀሰቅሰው።
ላንድ ዓላማ ላንድ ልሳን
ያገር ያለህ ኡኡ ብሎ ኅበዝ ጀግና የሚጣራው፣
ታዲያ እንዴት አልፎ ነው፣
ይህ ፅልመት የሚያበቃው።
ምፅት ጭነት ኃይል ነገር፣
መቶ ኩንታል ከባድ ፋርጐ፣
በደቦ ካልተገፋ፣ የጉላግ አርችፔላጎ።
የነባንቱስታን ሆምላንድ፣
የባልካን የንጀራ ልጅ፣
የጂንጂስካን ጡት ተጣቢ፣
የጎርደንዲኖስ ነገር-ፈጅ።
ታዲያ እንዴት ይፈረከሳል፣ ይህ ጠማማ ምኅኅ፣
በደቦ ካልተገፋ፣ የጉላግ አርችፔላጎ።

## « አዝናለሁ፣ እኔ ለኔና ለኛ!»

ከጌታቸው አድማሱ (ከአትላንታ)

አዝናለሁ እኔ ለኔና ላንቺ ለሁላችን፣
በጠቅላላው ለከንቱ ትውልዳችን።
በደፈናው ብኩን ለሆነው፣
የገዛ ቅርሳችንን እኛው ለቦረቦርነው፣
ክቡር ታሪካችንን አንገቱን ለገዘገዝነው፣
ደብዛችን ይጥፋ ብለን መጥፈያችንን ለምናጤነው።
እንደችፍርግ፣ እንደጭጐጐት፣
ተመንግለን እንጥፋ ለምንለው።
"ዋርካዬ" ብለው ሲጠጉን
ቁጥቋጦ ነን የምንለው።
"ዛፍ ሁኑን" "መጠለያ" ስንባል፣
አረም ነን ብለን የምንሻ መነቀል፣
እንውደም፣ እንጥፋ ባዮች
ከሥራችን እንመንገል።
ሌላው የሃምሣ ዓመት ታሪክ ሲያወድስ፣
እኛ አብረን ስናሞግስ፣
የራሳችንን ታሪክ ግን፣ ስናጐድፍ ስናንኳስስ፣
የነርሱን "ሆያሆዬ" በሆይታ! ስናከብር ስናሞግስ፣
የራሳችንን፣ በራሳችን፣
በምራት ተስኖን ስናነክስ
ሳያስፈልገን ተናቁረን፣
አስታርቁን ብለን ስናለቅስ።
አጐንብሰን እንደመቆፈር፣
ስናሳዝን፣ ስናነባ፣
እርጥባን ስንለምን
ከፋህፋህ ሆዱ ከሚባባ
ራርቶ የሚቸር ስንፈልግ፣
ቁርሶ መጉረስ እያቃተን፣
የሚያጐርሰን ስንሻ፣
መሶባችን ሞልቶ አይቀርብ፣
አጠገበን በጉርሻ።
ምድሩም ሰብል አይሰጥ፣
ዕዳሪ ሆኖ አያፈራ የኛ ድርሻ።
በፍርፋሪ ረክተናል በቃጤ ለበሳናት ቅምሻ፣
ገበታም መቅረብ አይገባንም፣
ይቅርብን መሶብም አያሻ፣
ኩቸሮ ብጤ ከቀመሰን፣ ከዚያም በላይ አንሻ።
አዝናለሁ እኔ ከልቤ ለኔና ለኛ ለሁላችን
ሳይገባን ቀርቶ ይሆን፣ ጥድፊያው ለጥፋታችን።
ምኑ ሥውር ሆኖብን ነው?
እንጥፋ ብለን የምንፋንነው?
ወይስ ከፉኛ ደንዝዘን ሳይታወቀን ቀርቶ ነው
የራሳችንን ውድመት፣ በራሳችን የምንፈትነው፣
ተገጣጥሞ የነበረውን፣ የምንንድ የምንነጥለው፤
ተጐንጉኖ የነበረውን፣ የምንፈታ፣ የምንበትነው፣
ተገንብቶ የነበረውን፣ እየደረመስን የምንንደው፣
በወግ የኖረ ጓዳ ገብተን አጉል የምናጐዳጉደው፣
አክርማ፣ አለላውን፣ ከስንደዶው ፈታተነው፣
ድፋን ከማግ እየለየን ለአቧራ የምንበትነው።
አዝናለሁ ለመሆን ስለበቃን፣
እኛው፣ የገዛ ራሳችን ጠስ
ታሪካችንን አዋርደን ያባቶቻችን ደም ለማርከስ
እጅግ አዝናለሁ እኔ፣ ለኔ ለኛም ለሁላችን
ታሪክን ሳጐደፍን፣ ቀርቶ ማስከበራችን
ያስጠይቀናል በኋላ፣ መቼ ያልፈናል ተራችን።

■

## የዘፈን ግጥሞች

አማርኛችን ብዙ ውስጠ ወይራ አነጋገሮች አሉት። ጥንት የሚፈልጉትን መልዕክት በቀጥታ ከመግለጽ በውስጠ ወይራ አነጋገር መግለጽ በሳልነት፣ አዋቂነትን ያሳያል። በተለይማ በግጥም ሆኖ በመሰንቆ ወይም በክራር የታጀበ ግጥም ከሆነማ ውበቱ ሌላ ነው። ቀደም ባሉ እትሞቻችን ብዙ ቅኔ አዘል የሆኑ የዘፈን ግጥሞች እየሰበሰብን አቅርበንላችሁዋል። የቋንቋችንን በሳልነት ከመግለጹም በላይ በዚህ ዘዴ የሚተላለፈው መልዕክት ተደማጭነት ስለአለው ያዝናናችሁዋል፤ ያወያያችሁዋል፣ ያኮራችሁዋል በሚል ነው። እስቲ እነኚህን ግጥሞች እናቅርብላችሁ።

እንደ መጀመሪያው አታስጨንቀኝ፤
እንደመጨረሻው ጣል ጣል አታርገኝ፤
ያንተ አልቆብህ እንደሁ እኔ ገና ነኝ።

ወይ አገሬ አትሄድ ወይ ባል አታገባ፣
እንደ ጠፍ በተስኪያን ከዚህ ተደርባ፣
አካላቴ አለቀ ስትገባ ስትወጣ።

ምነው ባደረገኝ ያባትሽን አራሽ፣
ዘር አለቀ ብዬ ቀን እንድጠራሽ።

ትፈትላለች አሉ ዘኃና ማጉን፣
ዘኃዋን አስትቶ እሷንስ ማኀን።

ጠጉሬ ለወለባ፣ አንገቷ ለድሪ
ታማረልኝ እኔ፤
እግጣት ይመስል አጥንቷ ለምኔ።

አንቺ ታቦት ሆነሽ እኔ ለምኜሽ፣
ስለቴ ደርሶልኝ መጥቼ ስሜሽ።

በምስር ወጥ መብላት፣
በክክም ወጥ መብላት፣
እህል በህል ነው፤
ራቴን ሳማ አድርገሽ ብትሰጪኝ ምነው።


በሉ እንግዲህ እናንተም መዘክሮቻችሁን ቃኙና አባባና እማማ የተውት ግጥሞች ካላችሁ ላኩልን።

---

## ልዩ ልዩ የሠርግ ግጥሞች

ከታደሰ ሙላት
(በሰርግ ዘፈኖች ውስጥ
ስለሚታዩ የአማርኛ ግጥሞች ከጻፉት የተወሰደ)

ብርሌው ብርጭቆው ዋንጫው ተለቅልቆ
እርስዎ አባት ሆነው የአሸከር ባል ተገኝቶ
ለምን ይቆጣሉ በሆነ ባልሆነው
ያስቀሯት ይመስል እርስዎ ባል ሆነው።
ሌሊቱ እንዳይነጋ በቁስ ተገዝቶ
ዶሮውም እንዳይጮህ ቁና ጥሬ ሰጥቶ
አብሬሽ ተኝቼ ልቤ ሲዘነጋ
ያ የማታ ሌሊት ከምንጊዜው ነጋ።
እንደሽማግሌ እንደሰው ፈራጅ
ያየውን የበላ ቁንጫ ነው እንጂ።
በስማም ብሎ ዕህፈት ብዕር ይዞ ቀለም
እንዳንቺ ያቈለኝ ያሞኘኝ ሰው የለም
ከወዲህ የመጣች ከእየሩሳሌም።
ጉልት አርጋኝ ሄደች ከባቡሩ መንገድ
የረከሰ ነገር አይቀር ሳይወደድ።
እኔ እየወድኳት እሷ እየጠላችኝ
ዛሬስ ይብላው ብላ ጅብ አስራ ቀየችኝ
አታም ሲመታ ይላል ናደው ናደው
እኔስ እሄዳለሁ ይብላኝ ለለመደው።
መስከረም ሲጠባ ይገባል አደዩ
ጉልት አርጋኝ ሄደች መናጢ ሴትዮ
እስቲ ሸዋ ልሂድ ቢሻኝ መርሃቤቴ
ጅምሬን ማን ነክቶሽ ሳይሰማ ሞቴ።
አባይ ወዲያ ማዶ ተከዜ በረኛ
በሞቱ ቆርጦ ነው አንቺን የሚተኛ።
ፈንካቲት ባስጠይቅ ደረሰች ጠይሞ
መሳም ነበር እንጂ አንገቷን ቆልምሞ።
ጠይሞ ባስጠይቅ ደረሰች ከምጣ
የመውደድን ነገር ጠይቃ ልትመጣ።
ምጣ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉ እነሴ
ሳዱላዋን ትታ ሆናለች ፈሰሴ።
እነሴ ባስጠይቅ ገባች አሉ ወሎ
እንደልጅነቴ አልብሳኝ ደበሎ።
ወሎ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉ ትግሬ
እከተላታለሁ በለመደው እግሬ።
ትግሬ ላይ ባስጠይቅ ገባች አሉ አድዋ
አልተጠቃለለም ገና ነው እዳዋ።
ይህን ሁሉ ለፍቼ ታክቼ ደክሜ ብመጣ
አላስገባኝ አለች ሚስቴ ወዝ ለውጣ።
የኔ አለም አንቺንጂ እረፊ
እያልኩ በጥፊ
ስጡኝ ክስንክሴን ደርቤ ልልበሰው።
እቻውን እስቲያገኝ
እብድ አይደለም ወይ ሰው።



# እ ስ ፖ ር ት



## የአትላንታው የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ቡድን የጆርጂያ ሻምፒዮን ሊሆን ነው!!

በአትላንታ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቡድን 34 ቡድኖች በ1993-94 በተካፈሉበት የአትላንታ ክፍለ ግዛት አማተር የእግር ኳስ ሊግ ( Atlanta District Amateur Soccer League) ውድድር ለመጨረሻው ዙር (ለሻምፒዮና ግጥሚያ) እንዳለፈ ለማወቅ ተችሏል።

ከ35 ጨዋታዎች በላይ ከተለያዩ ቡድኖች ጋር በመጫወት ለመጨረሻው ዙር የቀረበው ይህ የአትላንታ ኢትዮጵያውያን ቡድን ቀደም ሲል ለሁለት ዓመታት ያህል ሻምፒዮናነቱን በመያዝ የቆየውን የባካርዲ ብሪዘርስን ቡድን 4 ለ 1 በማሸነፍ ነው። በዕለቱ በቦታው የተገኘው የዝግጅት ክፍላችን ጨዋታውን በመመልከት የቡድኑን ጠንካራነት፣ የጨዋታ ጥበብና እስፖርታዊ ስነ ምግባር በመመልከት ለመደነቅ ችሏል። የመጨረሻው የሻምፒዮናው ጨዋታ የሚካሄደው May 1 1994 ሲሆን ቡድኑም የሚጫወተው እንዲሁ ብዙዎች ቡድኖችን አሸንፎ ለዚህ ከበቃው የዳታ ግራፊክስ ቡድን ጋር ነው።

ኢትዮጵያዊው ቡድን ይህን ግጥሚያካሸነፈ የጆርጂያ የሶከር ሻምፒዮና በመሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በቴክሳስ ተካሂዶ ሻምፒዮን ከሆነው ቡድን ጋር ጆርጂያን በመወከል ሂውስተን ላይ ይጫወታል። ሂውስተን ላይ ካሸነፈ የሪጅኑ (Southern Region) ሻምፒዮና ይሆናል ማለት ነው።

ቡድኑ ለዘንድሮው የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያን የእግር ኮስ ፌዴሬሽን በሜሪላንድ ለሚያዘጋጀው ውድድር በከፍተኛ ደረጃ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በመጨረሻው ጨዋታ ላይ ብዙ ኢትዮጵያውያን በሚዳው እንደሚገኙ ከአሁኑ ለማወቅ ተችሏል።



የአትላንታው ቡድን



ከጨዋታው በከፊል



# ቢስቁም ባይስቁም



## ግራ የገባት ሚስት
ከኃይሉ ሮበሌ (ከአትላንታ)

ባልዬዋ ውጭ እያመሸና እየሰከረ ያስቸገራት ሚስት እንዴት አድርጋ ከዚህ መጥፎ ፀባዩ እንደምታላቅቀው ስታሰላስል አንድ ሀሳብ ይመጣላታል። ይኸውም እሱ ከሥራ መጥቶ ወደቤት ከገባ በኋላ መውጣቱ ልምዱ ስለሆነ እቤቷ ውስጥ የተለያዩ መጠጦችን ገዝታ መደርደርና ግሮሰሪ ማስመሰል ነበር። እንደተለመደው ባል ሆዬ ሲመጣ "እቤታችን በጣም ደስ የሚል ግሮሰሪ ሆነ" በማለት ቁጭ ብሎ መኮምኮሙን ይያያዘዋል። በመጨረሻም ይሰክርና ብድግ ብሎ "ሂሳብ ስንት ነው?" ይላታል። እሷም "አስራ አምስት ብር" ትለዋለች። እሱም አስራ አምስቱን ብር ይሰጣትና ሲወጣ "ታዲያ የት ነው የምትሄደው?" ብትለው "ይቅርታ የኔ እህት እኔ መጠጥ የጠጣሁበት ቤት አድሬ አላውቅም" አላት ይባላል።

---

## "ገላገልከን ነበር!"
ከኃይሉ ሮበሌ (ከአትላንታ)

አንድ ሥራ አጥቶ የተበሳጨ ወጣት አንድ ቀን ብስጭትጭት ይልና "አቦ ይህ የመንግሥት መሪ እኮ ተጫወተብን" ሲል ወዲያውኑ የመንግሥት ደህንነቶች ይሰሙና የፍጥኝ አስረውት ፍርድ ቤት ያቀርቡታል። ዳኛውም ብዙ የሚመራመሩት ነገር ስለሌላቸው ወደ ወጣቱ ዞር ብለው "እንግዲህ የኔ ወንድም የሀገሪቷን ርዕሰ ብሔር መሳደብ ከባድ ወንጀል ስለሆነ በ25 ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ ወስኜብሃለሁ፤" ቢሉት ወጣቱም መልሶ "ጌታዬ! ሰድቤው ይሄን ያህል የፈረዱብኝ ብገለው ኖሮ ምን ይፈረድብኝ ነበር?" ቢላቸው እሳቸውም መነፅራቸውን እያስተካከሉ "እሱማ ገላገልከን ነበር1" አሉት ይባላል።

---

## "እራሷ ትዞረኛለች"
ከእሸቱ እሼቴ (ዋሽንግተን ዲ ሲ)

አንዱ በጣም አልኮል የሚጠጣ ጓደኛውን ሲመክር "ለምንድነው ገንዘብህን በመጠጥ የምታጠፋው? አጠራቅመህ ዓለምን ብትዞርበት አይሻልም?" ይለዋል። ሰካራሙም " ምን በወጣኝ አገር ለአገር የምዞረው፤ ግጥም አድርጌ አረቄዬን ብጠጣ ዓለም ራሷ ትዞረኝ የለም?" አለው ይባላል።

---

## ከደጋጉ እንስሳት ዕማኝ ትቁጠርብኝ

በቅኔያዊ ለዛ ፈጥነው መልስ በመስጠት የታወቁት አለቃ ገብረሃና በምስጢር እንዲት ወዳጅ ይይዛሉ። አየር የሚቀበሉ በመምሰል አዘውትረው ወደዚህች ወዳጃቸው ቤት በቅሎአቸውን ጭነው ብቅ ማለታቸው አልቀረም። ይህን የለመደች በቅሎአቸው ወዳጃቸው ቤት አካባቢ ስትደርስ ሁልጊዜም ትቆም ጀመረች። ይህን የተገነዘቡት ባለቤታቸው ወ/ሮ ማዘንጊያም "እኔን የሕግ ሚስታቸውን ትተው ይማግጣሉ" ሲሉ በሽማግሌ ይጠይቋቸዋል። ሽማግሌዎቹም ምንድነው ማስረጃሽ ብለው ይጠይቃሉ። "ለዚህም ማስረጃዬ በቅሎይቱ ናት። ሂዳ ሂዳ ከሴትዮዋ ቤት ስትደርስ ትቆማለች። ማስረጃዬ ናት" ይላሉ። አለቃም ተጠይቀው ሲመልሱ "በቅሎይቱ ተሸከማኝ አቀበት ቁልቁለት የምትወርድ የማደክማትና የማሰቃያት ስለሆንኩ አትመሰክርብኝም። ከሆነ ከሆነ ከበሬዎቹና ከላሞቹ ከደጋጉ እንስሳት እማኝ ትቁጠርብኝ" ብለው የባለቤታቸውን ቁጣ አበረዱ ይባላል።

---


ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

የላንዳፍታን መጽሔት ባላችሁበት ቦታ ለማከፋፈል የምትፈልጉ የአከፋፋይ ኮሚሽን ከ20 - 25 በመቶ የምንከፍል ስለሆነ በአድራሻችን ደውሉልን ወይም ጻፉልን።


አድራሻችን፤-
LANDAFTA
P.O. Box 493Q1
Atlanta, GA 30359
(404)728-9122


# ጨዋታና ሰንጠረዥ

## የአለፈትን የሰንጠረዥ

## ጥያቄዎች በትክክል የመለሱ፤

የጥርን ሰንጠረዥ የመለሱ
እናት ወንድይራድ (ከቺካጎ)
የመጋቢትን ሰንጠዥ የመለሱ
ዓለም ደነቀው አበበ (ላስ ቬጋስ)
የጥርንና የመጋቢትን ሰንጠረዦች የመለሱ
ሙሉ ተሰፋዬ (ከአትላንታ)
አየለ ገብሩ (ከአትላንታ)





**ወደ ጎን**

1. his face
5. to collect
11. greedy
16. a small can
19. heart
21.
24. advocate
31. we have forgotten
37. but
52. she spoiled
58. to give an oath
61. to be shy
65. we drank Ethiopian Beer
71. terrace
76. your sweat
83. rooms
88. pen
98. whiteness

**ወደ ታች**

1. First month (Eth.)
2. smooth
3. Eth. national dress
6. if he shows effort
7. to embarass
9. a worm
14. to be a monk/nun
20. it's getting worse with us
25. a gadget used to burn insence on
28. hyena
33. kneel down
39. curse
46. you can do it (plural)
52. soil
55. he sold
58. you came to us
61. mineral
67. a quarrel
74. cooked cereal
80. production
89. chance

# የላንዳፍታ መጽሔት ደምበኛ ይሁኑ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለ6 ተከታታይ እትሞች | U.S. | $16.00 | (including postage & handling) |
| | Canada | $22.00 | (including postage & handling) |
| | Europe & Asia | $30.00 | (including postage & handling) |

የሚላክሎት በመጀመሪያ ደረጃ ፓስታ አገልግሎት ነው።
በአካባቢዎ ገበያ ላይ ከመዋሉ በፊት ይደርስዎታል።

## የላንዳፍታ መጽሔት የደምበኝነት ቅጽ
## LANDAFTA SUBSCRIPTION FORM

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________

PHONE ( ______ ) ______________

<u>ያለፉትን እትሞች</u> ማዘዝ ከፈለጉ ይህንኑ ይጥቀሱ
ክፍያው ከነመላኪያው ለእያንዳንዱ እትም $ 2.50 ነው።

ለጓደኛዎ በሽልማት መልክ ለመላክ ከፈለጉ ከዚህ በታች ያለውን ይሙሉ።
Please, send my gift subscription to the following person.

NAME ______________________________

ADDRESS ______________________________

CITY ______________ STATE ______ ZIP ______________


PHONE ( ______ ) ______________

አባክዎን ክፍያዎን በመኒ ኦርደር ወይም በቸክ በአድራሻችን ይላኩ።
*Please, send money order or check payable to LANDAFTA.*

LANDAFTA
P.O.BOX 49301
ATLANTA, GA 30359

# ADVERTISE ON LANDAFTA

# በላንዳፍታ ላይ ድርጅቶን ያስተዋውቁ




**ADVERTISMENT ORDER FORM**

I would like to place an advertisment on LANDAFTA.

Name: ____________________

Address: ____________________

City: ____________________

St. ___ Zip: __________

Phone: ____________________

PLEASE, MARK THE SPACE BELOW TO INDICATE YOUR CHIOCE LIKE THIS (X)

**SINGLE ISSUE RATES**

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $200.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $175.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $140.00 |
| ◯ HALF PAGE | $90.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $65.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $50.00 |

**TWO CONSECUTIVE ISSUES RATE**

| | |
|---|---|
| ◯ BACK COVER | $350.00 |
| FULL PAGE | |
| ◯ INSIDE COVERS | $300.00 |
| ◯ INSIDE PAGES | $250.00 |
| ◯ HALF PAGE | $150.00 |
| ◯ 1/4 PAGE | $110.00 |
| ◯ 1/8 PAGE | $90.00 |

ላ
ን
ዳ
ፍ
ታ

Enclosed, please find: 1. A copy of the advertisment to be placed.
2. A check for the amount marked above.

Please, send a copy of the proof before printing. ☐

I Want my ad Translated in Amharic ☐
(no extra fee - please indicate words or phrases to be translated)

For Information, Please Call Advertisment Department:
Publisher at: Phone/Fax (404)728-9122

Please, Send check or money order payable to LANDAFTA along with your order.
LANDAFTA, P.O.Box 49301, Atlanta GA 30359

# MRA'G TRAVEL

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

ለአለም አቀፍና
ለአገር ወሰጥ ጉዞዎ አለንልዎ!

Excellent Service!
Special Fare!
Group Fare!

ገነት ፈቀደ
ፕሬዚዳንት
Genet Fekede
*President*

አስተማማኝ ጉዞ ወደ

አዲስ አበባ
አስመራ
ጆሀንስ በርግ
ቴላቪቭ
ኢየሩሳሌም
ፍራንክፈርት
ለንደን



92 Piedmont Ave N.E
Atlanta, GA. 30303
(404)577-4404 Fax (404)222-9305

ዋ
ይ
ል
ድ

ሄ
ር




(312) 327 - Hare